# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ዓርብ

83ኛ ዓመት ቁጥር 095 ታኅሣሥ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10:00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!






ፀደይ ባንክ (አ.ማ)
TSEDEY BANK (S.C)

የሁሉም ባንክ
Bank for all !

የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ!

በፋይናንስ አቅርቦት በተግባር የተፈተነ እንዲሁም ሰፊና ጽኑ መሰረት ያለው ባንክ በአነስተኛ የፋይናንስ አገልግሎት ዘርፍ በአገለገለባቸው 25 ዓመታት አለም አቀፍ ዕውቅናዎችን ሲያገኝ የቆየው አማራ ብድርና ቁጠባ ተቋም ወደ ፀደይ ባንክ ተሸጋግሮ የተሟላ አገልግሎት በመስጠት ላይ ይገኛል።

Tel: +251 115 58 12 70/011 551 73 48/011 558 99 98
P.O.Box: 9630
E-mail: mekonnenyelewemwessen@tsedeybank-sc.com
Web: www.tsedeybank.org.et
Addis Ababa, Ethiopia




ፎቶ፡ ዳኜ አበራ

# የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም በቢሾፍቱ ተካሄደ

## - አፍሪካውያን ችግሮችን ለመቋቋም በትብብር መሥራት ይጠበቅባቸዋል

ሳሙኤል ወንደሰን

ቢሾፍቱ፡- ከተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የተውጣጡ የአየር ኃይል አዛዦች የተሳተፉበት የመጀመሪያው የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም ትናንት በቢሾፍቱ ከተማ አየር ኃይል ግቢ ተካሂዷል፡፡ አፍሪካውያን የሚያጋጥሟቸውን ችግሮች ለመከላከልና ለመቋቋም በትብብርና በአጋርነት መሥራት እንደሚገባቸውም ተገልጿል፡፡

የኢትዮጵያ አየር ኃይል 88ኛ ዓመት የምሥረታ በዓል "በመስዋዕትነት ሀገርን የዋጀ የኢትዮጵያ አየር ኃይል" በሚል ከኅዳር 20 ቀን 2016 ዓ.ም ጀምሮ እየተከበረ ይገኛል።

88ኛውን የኢትዮጵያ አየር ኃይል የምሥረታ በዓልን ምክንያት በማድረግ የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም ትናንት በቢሾፍቱ ሲካሄድ የመከላከያ ሚኒስትሩ አብርሃም በላይ (ዶ/ር)፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በፓን-አፍሪካኒዝም እሳቤ ከአፍሪካ ሀገራት ጋር


የአፍሪካ አየር ኃይል ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




ዳዊት ሀየሶ (ዶ/ር)

## የብድር

### መክፈያ እፎይታ መፈቀዱ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ይረዳል


ገጽ 4




## ኮሚሽኑ በኦሮሚያ

### ክልል ተሳታፊዎችን ለሚለዩ አካላት ሥልጠና መስጠት ጀመረ


ገጽ 4


# ኢትዮጵያ የስደተኞችን ደህንነት ለመጠበቅና ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኛ ናት

## • በስደተኞች ላይ የሚያተኩር ዓለም አቀፍ ጉባኤ ትናንት በሲዊዘርላንድ ጄኔቭ ተከፍቷል

መዓዛ ማሞ

አዲስ አበባ፡ ኢትዮጵያ የስደተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ እና ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆንዋን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን መግለጻቸውን የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ተናገሩ፡፡

በስደተኞች ላይ የሚያተኩር ሁለተኛው ዓለም ዓቀፍ ጉባኤ በትናንትናው እለት በሲዊዘርላንድ ጄኔቭ መከፈቱንም ጠቁመዋል፡፡

አምባሳደር መለስ ዓለም እንደተናገሩት በምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን የተመራ ከፍተኛ የመንግሥት ልዑክ በጉባኤው




ኢትዮጵያ የስደተኞችን ደህንነት ... ወደ ገጽ 4ሯል








ጤና ሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
MINISTRY OF HEALTH-ETHIOPIA
የዜጎች ጤና ለሃገር ብልጽግና!
HEALTHIER CITIZENS FOR PROSPEROUS NATION!

# ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ ተጋላጭ በሆኑ 300 ወረዳዎች ላይ የመከላከል ሥራ እየተሠራ ነው

**- ከ610 ሺህ 350 በላይ ዜጎች ላይ ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል**

**ሄለን ወንድምነው**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በሀገሪቱ ለኤች.አይ.ቪ ኤድስ ይበልጥ ተጋላጭ በሆኑ 300 ወረዳዎች ላይ የመከላከል ሥራው እየተሠራ እንደሚገኝ ጤና ሚኒስቴር አስታወቀ። በሀገሪቱ ከ610 ሺህ 350 በላይ ወገኖች ቫይረሱ በደማቸው እንደሚገኝ ተመላክቷል።

በጤና ሚኒስቴር የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከልና መቆጣጠር መሪ ሥራ አስፈጻሚ የዘርፈ ብዙ ኤች.አይ.ቪ ኤድስ ምላሽ ዴስክ ኃላፊ አቶ ሀብታሙ ካሳ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሀገሪቱ በሁሉም ክልሎች ከፍተኛ የቫይረሱ ስርጭት ያለባቸው አካባቢዎች አሉ።

አቶ ሀብታሙ እንዳሉት፤ በአማራ ክልል 74፣ በኦሮሚያ ክልል 54፣ በደቡብ ኢትዮጵያ ሰባት እና በሌሎች የክልል ወረዳዎችም ከፍተኛ የስርጭት ምጣኔ ይታያል።

በሀገሪቱ ለቫይረሱ ይበልጥ ተጋላጭ የሆኑ የማኅበረሰብ ክፍሎች የሚኖሩባቸውና የስርጭት ምጣኔያቸው ከፍተኛ የሆነ 300 ወረዳዎች ተለይተው የመከላከል ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

ሴተኛ አዳሪዎች፤ አደንዛዥ እፅ ተጠቃሚዎች፣ የሕግ ታራሚዎች፣ የሀገር አቋራጭ አሽከርካሪዎች፤ ትዳር የፈቱ ግለሰቦች፤ ወጣቶችና ሴቶች ይበልጥ የስርጭቱ ተጋላጭ መሆናቸውን ኃላፊው አብራርተዋል።

ለሴተኛ አዳሪዎች የቅድመ መጋለጥ መድኃኒት፣ የድህረ መጋለጥ ሕክምና እና የአቻ ለአቻ ውይይት እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን አስገንዝበዋል።

የተማሪዎችን ተጋላጭነት ለመቀነስ የባሕሪ ለውጥና የሕይወት ክህሎት ሥልጠና እንዲያገኙ እየተደረገ መሆኑን ጨምረው ገልጸዋል።

የወጣቶችን ተጋላጭነት ለመቀነስ በራሳቸው መመርመር የሚችሉበት መተግበሪያ በማበልጸግ ወደሥራ ለማስገባት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ተመርምሮ ራስን አለማወቅ ተጋላጭነትን እንደሚጨምር የጠቀሱት አቶ ሀብታሙ፤ ዜጎች ተመርምረው ራሳቸውን እንዲያውቁ እና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰዋል።

እ.አ.አ. የ2022 ሀገራዊ የኤች አይቪ ስርጭት ግምት እንደሚያሳየው በሀገሪቱ በአጠቃላይ ከ610 ሺህ 350 በላይ ወገኖች ላይ ቫይረሱ በደማቸው እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ከነዚህም ውስጥ ተመርምረው እራሳቸውን ያወቁት 84 በመቶ የሚሆኑት ናቸው። ራሳቸውን ያላወቁትን ዜጎች እንዲያውቁ ማድረግ በትኩረት የሚሠራበት ዋና ተግባር ነው ብለዋል።

የቫይረሱ የስርጭት ምጣኔው ከቦታ ቦታ እና ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ በተለያየ ደረጃ ላይ የሚገኝ መሆኑን ጠቅሰው፤ በሀገር አቀፍ ደረጃ ያለው የስርጭት መጠን ከአንድ በመቶ በታች መሆኑን ጠቁመዋል።

ጋምቤላ 3 ነጥብ 69፣ አዲስ አበባ ሦስት ነጥብ 47 በመቶ፣ ሐረሪ 2 ነጥብ 97 እና ድሬዳዋ 2 ነጥብ ዘጠኝ በመቶ ከፍተኛ የስርጭት ምጣኔ የሚታይባቸው መሆኑን አብራርተዋል።

በአንጻሩ በሶማሌ ክልል ዜሮ ነጥብ 18 በመቶ ዝቅተኛ የስርጭት ምጣኔ መኖሩን አመላክተዋል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ በከተሞች ሁለት ነጥብ ዘጠኝ በመቶ በገጠር ዜሮ ነጥብ አራት በመቶ የስርጭት ምጣኔ እንደሚታይ ጨምረው ገልጸዋል።

እንደ ሥራ አስፈጻሚው ገለጻ፣ በሀገሪቱ ከ610 ሺህ 350 በላይ ወገኖች ቫይረሱ በደማቸው ይገኛል። በዓመት ስምንት ሺህ 257 ሰዎች በቫይረሱ ይያዛሉ። 11 ሺህ 322 ዜጎች ደግሞ በዓመት ሕይወታቸውን በቫይረሱ ምክንያት ያጣሉ።

# በክልሉ ከ300 ሺህ ኩንታል በላይ የበርበሬ ምርት ይጠበቃል

**አማን ረሺድ**



<u>አዲስ አበባ</u>፡- በክልሉ በ2015/16 የምርት ዘመን ከ300 ሺህ ኩንታል በላይ የበርበሬ ምርት እንደሚጠበቅ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል አስታወቀ።

በክልሉ የቡናና ቅመማቅመም ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር አቶ ሬድዋን ከድር ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በምርት ዘመኑ 27 ሺህ 733 ሔክታር መሬት ላይ ከለማው የበርበሬ ሰብል ከ300 ሺህ ኩንታል በላይ ምርት ይጠበቃል።

እንደ አቶ ሬድዋን ገለጻ፤ የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል በኢትዮጵያ ከፍተኛ የበርበሬ ምርት ከሚመረትባቸው አካባቢዎች ቀዳሚው ነው። የበርበሬ ምርት በክልሉ በሚገኙ የስልጤ፣ ጉራጌ፣ ምሥራቅ ጉራጌ፣ ከንባታ፣ ሃድያ፣ ሃላባና የም ዞኖች እንዲሁም የተለያዩ ልዩ ወረዳዎች በስፋት እየተመረተ ይገኛል።

አሁን ላይ በክልሉ የተለያዩ አካባቢዎች የበርበሬ ምርት እየተሰበሰበ መሆኑን ገልጸው፤ ወደ ሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ለገበያ እየቀረበ መሆኑን ተናግረዋል።

ምርቱን ዩኒየኖችና የባልትና ዘርፍ ነጋዴዎች ከአርሶ አደሩ ጋር ትስስር እንዲፈጥሩ በማድረግ ነው ለገበያ እየቀረበ የሚገኘው ብለዋል።

በተለይም በተጠቃሚው ዘንድ ከፍተኛ ተፈላጊነት ያለው የማረቆ ፋና በርበሬ ዝርያ ላይ እሴት ጨምሮ ለተጠቃሚዎች እንዲደርስ በትኩረት እየተሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ለአርሶ አደሩ የገበያ ትስስርን በመፍጠርና የወቅቱን የገበያ መረጃ በማቅረብ ከምርት ላኪዎች ጋር በጋራ እየተሠራ ይገኛል ያሉት አቶ ሬድዋን አርሶ አደሩን በመሠረታዊ የኅብረት ሥራ ማኅበራት በማደራጀት ውጤታማ ሥራዎች እየተከናወኑ መሆናቸውን አመልክተዋል።

በምርት ዘመኑ በተወሰኑ አካባቢዎች በበርበሬ ሰብል ላይ የስር አበስብስ በሽታ መከሰቱን ጠቅሰው፤ በሽታው በሰብሉ ላይ የከፋ ጉዳት ሳያደርስ መቆጣጠር መቻሉን ገልጸዋል።

በአሁኑ ወቅት የበርበሬ ምርት እየተሰበሰበ መሆኑን ጠቅሰው ከምርት አሰባሰብ ጋር በተገናኘ የሚያጋጥሙ ብክነቶችን ለመቅረፍ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና መሰጠቱን አቶ ሬድዋን አስረድተዋል።

የገበያ ትስስሩን በመላ ሀገሪቱ ለማሳለጥ እና ጥራቱን የጠበቀ በርበሬ ለገበያ ለማቅረብ በትኩረት እየተሠራ መሆኑን አስረድተዋል።

ምርቱን በስፋት ለማምረት የሚያስችሉ ግብዓቶችን ለአርሶ አደሩ ለማቅረብ ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ጋር እየሠሩ መሆናቸውን ገልጸው፤ ለዘርፉ ውጤታማነት የሁሉም አካላት ተሳትፎ ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል።



# የግብርና ምርቶች ብክነትን ለመቀነስ እየተሠራ ነው

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

<u>አዲስ አበባ</u>፡- በግብርና ምርቶች ላይ የሚደርሰውን ብክነት ለመቀነስ የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ንግድ ቢሮ አስታወቀ።

የቢሮው የኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር አቶ ሰውነት አየለ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንዳስታወቁት፤ በተለይም በአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ የሚደርሰውን ከፍተኛ ብክነት ለመቀነስና፣ የተመረተ ምርት ሁሉ በቀጥታ ወደ ሸማቹ እንዲደርስ የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ ይገኛል።

ገበሬው ጊዜውንና ጉልበቱን አውጥቶ ያመረተው ምርት በአግባቡ ተጓጉዞ ወደ ኅብረተሰቡ መድረስ ይኖርበታል፤ ይህ አሠራር ካልተዘረጋለት ለምርት ዋጋ መጨመርና ለኑሮ ውድነት አንዱ መንስዔ ይሆናል ብለዋል።

በተጨማሪም ከግብርና ምርቶች ማጓጓዣና ማቆያ ጋር የተያያዙ ችግሮች መኖር የምርት ብክነት እንዲፈጠር በር እየከፈቱ መሆኑን ተናግረዋል።

እንደ አቶ ሰውነት ገለፃ፤ በተለይ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶችን ወደ ሸማቹ ለማድረስ ምቹ የሆነ የትራንስፖርት ሥርዓት የለም። የግብርና ምርት ማጓጓዣዎች ለምርቶቹ ታስበው የተዘጋጁ አይደሉም። ይህ ደግሞ ምርቶችን ለመበላሸት ይዳርጋል።

በተመሳሳይም የአትክልትና ፍራፍሬ መገበያያ ስፍራዎች የምርቶቹን ደህንነት ጠብቀው እንዲያቆዩ ታስበው የሚዘጋጁ አለመሆናቸውን የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ ይህም ፍራፍሬና አትክልቶች በሙቀት ሳቢያ እንዲበላሹና የምርት ብክነት እንዲኖር አድርጓል ብለዋል።

በመሆኑም ከግብርና ምርቶች ማጓጓዣና ማቆያ ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለመቅረፍ እና የግብይት ሥርዓቱን ለማዘመን ቢሮው ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ቢሮው፣ የግብርና ምርቶችን ደህንነት ጠብቀው የሚያደርሱ ማጓጓዣዎች እንዲኖሩ እየሠራ መሆኑን የጠቀሱት ኃላፊው፤ አትክልትና ፍራፍሬ ማቆየት የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ዘመናዊ የገበያ ማዕከላትን ማስገንባቱንም ተናግረዋል።

የንግድ ማዕከላቱ በአዲስ አበባ በአምስቱም መግቢያ በሮች የተገነቡ ሲሆን፣ የአቅራቢዎች ጨረታ ሂደት ተጠናቆ በቅርቡ ወደ ሥራ እንደሚገቡ ዳይሬክተሩ አስታውቀዋል።

ዳይሬክተሩ እንዳሉት፤ የገበያ ማዕከላቱ በቅዝቃዜ የሚበላሹ ምርቶችን ለማሞቅ፣ በሙቀት የሚበላሹ ምርቶችን ደግሞ ለማቀዝቀዝ የሚያስችል ቴክኖሎጂ የተገጠመላቸው ናቸው።

ቢሮው፣ በዋናነት የንግድ ሥርዓቱ ፍትሐዊ፣ ፈጣን፣ ቀልጣፋና ተደራሽ እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን እያከናወነ እንደሚገኝ ኃላፊው ጠቁመዋል።

በተለይም የንግድ ሥርዓቱ ዘመናዊነትን ካለመላበሱ የተነሳ የሚደርሱ የምርት ብክነቶችን ለመቅረፍ ከሚሠራቸው ሥራዎች በተጨማሪ፤ በሌሎች አካላት የሚሠሩ መሰል ተግባራትንም እየደገፈ እንደሚገኝም አብራርተዋል።



ወይዘሮ ሲዲያ ግርማ

## በመዲናዋ ሕገ ወጥ የመሬት ወረራን መቅረፍ ተችሏል

ታደሠ ብናልፈው

አዲስ አበባ፡- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ የማስከበር ባለሥልጣን በመዲናዋ እያከናወነው ባለው ደንብ የማስከበር ሥራ ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ ወንጀልን ማስቆም ተችሏል ሲል የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ አስታወቀ።

ማኅበረሰቡ የሚያነሳቸውን የመልካም አስተዳደርና የአገልግሎት አሰጣጥ ችግሮችን ለመቅረፍ ከደንብ አስከባሪዎች ጋር በትናትናው ዕለት ውይይት ተካሂዷል።

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የሰላምና ፀጥታ ቢሮ ኃላፊ ወይዘሮ ሊዲያ ግርማ ከውይይቱ በኋላ ለጋዜጠኞች በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ደንብ የማስከበር ባለሥልጣን በሕገ ወጥ የመሬት ወረራ ላይ በሠራው ደንብና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ሥራ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ ችሏል።

በመዲናዋ ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ ሥራ እንዳይከናወን የቅድመ መከላከል ሥራ እየተሠራ ነው ያሉት ኃላፊዋ፤ እየተሠራ ያለውም ሥራ ማንኛውም ሰው መሬት በዘፈቀደ ወርሮ የሚይዝበት እድል እንዳይፈጠር እያደረገ ይገኛል ብለዋል።

በሕገ ወጥ መሬት ወረራ ላይ እየተሠራ ያለው ደንብና የሕግ የበላይነትን የማስከበር ሥራ ሕገ ወጦች መሬትን ከሕግ አግባብ ውጪ በሆነ መንገድ ለማግኘት የሚያደርጉትን ጥረት የሚያመክን ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ባለሥልጣን መሥሪያ ቤቱ ሕገ ወጥ የመሬት ወረራን ለመከላከል እተየወሰደ ባለው የደንብ ማስከበር ሥራና በሕገ ወጦች እየተወሰደ ባለው እርምጃ ወንጀሉን መቆጣጠር ተችሏል ብለዋል።

አልፎው አልፎው የሚታዩ መሬትን በሕገ ወጥ መንገድ የመውረር የደንብ ጥሰቶችንም ለመቅረፍ የተጠናከረ ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

የደንብ ማስከበር ተቋም በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ሕገ ወጥ የመሬት ወረራን የመቆጣጠር ሥራ በተገቢው መንገድ እየሠራ ይገኛል፤ እየሠራ ባለው ሥራም ትልቅ ለውጥ አሳይቷል ብለዋል።

ሕገ ወጥ የመሬት ወረራ በመከላከል የታየውን ትልቅ ለውጥ ለማስቀጠል ከባለድርሻ አካላት ጋር በተጠናከረ መልኩ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

ወይዘሮ ሊዲያ አያይዘውም፤ ተቋሙ ሕገ ወጥ ማስታወቂያንና ግንባታን የመከላከል ሥራ እየሠራ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሕገወጥ ማስታወቂያ ሥራ ላይ ተሠማርተው በሺህዎች የሚቆጠሩ ዜጎችን ሕጋዊ በማድረግ መንግሥት ማግኘት የሚገባውን ግብር እንዲያገኝ ተድርጓል ሲሉ ገልጸዋል።

ሕገወጥ ግንባታን የመከላከል ሥራ እየተሠራ ዜጎች ፍቃድ አውጥተው በሕጋዊ መንገድ እንዲቀሳቀሱ የማድረግ ሥራ ለመሥራት ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል።

# ኢትዮጵያ፣ በኢንቨስትመንት ለሚሰማሩ የኳታር ባለሃብቶች ተገቢውን ድጋፍ ታደርጋለች

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፎች መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ የኳታር ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ የምታደርግ መሆኑን የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ምስጋኑ አርጋ ገለፁ።

በውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ምስጋኑ አርጋ የተመራ የኢትዮጵያ ልዑክ ከኳታር የኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ጋር ተወያይተዋል።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ምስጋኑ አርጋ በዶሃ በተካሄደውን ውይይት ዙሪያ በሰጡት ማብራሪያ እንደገለጹት፤ ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፎች መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ የኳታር ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ የምታደርግ መሆኑን ገልጻለች።

እንደ አቶ ምስጋኑ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከኳታር ጋር ያላትን የኢንቨስትመንት ትብብር አጠናክራ ትቀጥላለች።

ኢትዮጵያ በኢንቨስትመንትና የንግድ ዘርፎች መዋዕለ ንዋያቸውን ለሚያፈሱ የኳታር ኢንተርፕራይዞች ድጋፍ እንደምታደርግ ገልጻለች ያሉት አቶ ምስጋኑ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት ለባለሀብቶች ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ዝግጁ ነው ብለዋል።

ኢትዮጵያና ኳታር በተለያዩ የኢንቨስትመንት ጉዳዮች ላይ መወያየታቸውን ገልጸዋል።

በተለይም በግብርና፣ በማኑፋክቸሪንግ፣ በፋርማሲዩቲካልስ እና በቴሌኮም ዘርፍ ትብብራቸውን ለማሳደግ መወያየታቸውን ጠቅሰዋል።

በተመሳሳይ ሎጂስቲክስና ትራንስፖርትን ጨምሮ፣ በማዕድንና ቱሪዝም ዘርፎች ትብብራቸውን ለማሳደግ መምከራቸውን አቶ ምስጋኑ አብራርተዋል።



የኳታር ባለሃብቶች በኢትዮጵያ መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ በኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽን ጥሪ መቅረቡን ገልጸው፤ ኢትዮጵያ ከኳታር ጋር ያላትን የኢንቨስትመንት ትብብር አጠናክራ እንደምትቀጥልም ገልጸዋል።

በኢትዮጵያና ኳታር መካከል ባለው የሁለትዮሽ ትብብር ኢኮኖሚያዊ አጋርነት ማጠናከር በሚቻልበት ሁኔታ መምከራቸውንም ተናግረዋል።

በውይይቱ ላይ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ምስጋኑ አርጋን ጨምሮ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ኮሚሽነር ሌሊሴ ነሜ እና በኳታር የኢትዮጵያ አምባሳደር ፈይሰል አሊ፣ ከኳታር ኢንቨስትመንት ባለሥልጣን ዋና ሥራ አስፈፃሚ ማንሱር ቢን ኢብራሂም አል ማሕሙድ ጋር በዶሃ ተወያይተዋል።

# "ፕሮግራሙ በደን ልማት ዘርፍ አመርቂ ውጤት እያስገኘ ነው"

## - የኦሮሚያና አማራ ክልሎች

ቃልኪዳን አሳዬ



አዲስ አበባ፡- የሬድ ፕላስ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም በደን ልማት ዘርፍ አመርቂ ውጤት እያስገኘ መሆኑን የኦሮሚያ እና የአማራ ክልሎች ገለጹ።

የኦሮሚያ ክልል ሬድ ፕላስ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ደበላ ተስፋዬ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት፤ የሬድ ፕላስ ፕሮግራም በ11 ዞኖች ውስጥ በሚገኙ 41 ወረዳዎች ተግባራዊ እየተደረገ ነው።

እንደ አቶ ደበላ ገለጻ፤ በክልሉ መሬትን መልሶ እንዲያገግም ከማድረግ አንጻር በተሠራው ሥራ ከ25 ሺህ ሄክታር በላይ መሬት በደን መሸፈን ተችሏል።

እንዲሁም እየጠፋ ያለን ደን በመከለል ከሰውና ከእንስሳት ንክኪ በመጠበቅ እንዲያገግም በማድረግ ረገድ ከ270 ሺህ ሄክታር በላይ ደን መጠበቅ መቻሉን አብራርተዋል።

ክልሉ ያለውን አቅም ከግምት ውስጥ በማስገባት ፕሮግራሙ በሁለት አይነት መንገድ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ ያነሱት አቶ ደበላ፤ በሐረርጌ፣ አርሲና ሸዋ አካባቢዎች በሚገኙ በ17 ወረዳዎች ውስጥ የአዲስና የነባር ደን ልማት ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን ጠቅሰዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ በጅማ፣ በኢሉ አባቦራ፣ ቡኖ በደሌ፣ ምሥራቅ ወለጋ እና ሆሮ ጉድሩ አካባቢዎች የሚገኘውን የተፈጥሮ ደን በመከለል ኅብረተሰቡ በራሱ እንዲያስተዳድር የማድረግ ተግባር ተከናውኗል ብለዋል።

በዚህም በክልሉ በአጠቃላይ ከ400 ሺህ ሄክታር በላይ ደን ማልማት መቻሉን አቶ ደበላ ጠቁመዋል።

ኅብረተሰቡን በማሳተፍ በከብት እርባታ፣ በንብ ማነብና በሌሎች ትናንሽ የገቢ ምንጮች ውስጥ ገብቶ እንዲሠራ በማድረግ የኑሮ ማሻሻያ ድጋፍ እየተደረገ እንደሆነ አንስተዋል።

ባለፈው ዓመት ከዓለም ባንክ ጋር የ40 ሚሊዮን ዶላር የካርበን ሽያጭ ውል ተደርጓል ያሉት አቶ ደበላ፤ ይህንን እንደ ጅማሬ በመውሰድ በቀጣይ የተለያዩ ተግባራት እንደሚከናወኑ አመላክተዋል።

የአማራ ክልል የሬድ ፕላስ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም አስተባባሪ አቶ ስንታየሁ ደረሰ በበኩላቸው እንደተናገሩት፤ የሬድ ፕላስ ፕሮግራም በክልሉ የሚገኙ ነባርና ጉዳት የደረሰባቸውን ደኖች እንዲያገግሙ እያስቻለ ነው።

በተጨማሪም ሰፋፊ ሰው ሠራሽ ደኖች እንዲፈጠሩና የውሃ አካላትም ጭምር ወደነበሩበት እንዲመጡ እድል የሰጠ ነው ብለዋል።

እንደ አቶ ስንታየሁ ገለጻ፤ እስካሁን በተሠራው ሥራ በክልሉ ከአራት ሺህ ሄክታር በላይ አዲስ ደን ለምቷል። እንዲሁም ከ403 ሺህ ሄክታር በላይ ነባር ደኖች ተከልለው እንዲጠበቁ አስችሏል።

ማኅበረሰቡ አደረጃጀት ተፈጥሮለት ደንን ጠብቆ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኝ የሚያደርጉ ተግባራት በመከናወን ላይ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል።

ፕሮግራሙ በክልሉ በሚገኙ 28 ወረዳዎች ላይ ተግባራዊ እየተደረገ ነው ያሉት ኃላፊው፤ በሁሉም ወረዳዎች እንደየ አካባቢው ሥነ ምሕዳራዊ ሁኔታ የተሻሉ ተግባራት መከናወናቸውን አንስተዋል።

በክልሉ በተሠራው ሥራ 27 ሚሊዮን ሜትሪክ ቶን የካርበን ልቀት መቀነስ የተቻለ መሆኑን ጠቁመዋል።

በተለይም በወሎ አካባቢ እና በደላንታ ወረዳ የተሠራው ሥራ ከሁሉም የተሻለ እንደሆን አንስተዋል።

ፕሮግራሙ ተዛማጅ ጥቅሞችን እያስገኘ መሆኑን ያነሱት አቶ ስንታየሁ፤ በንብ ማነብ፣ በወጣቶች የሥራ ዕድል ፈጠራና በኑሮ ማሻሻያ ዘርፎች ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝ ጠቅሰዋል።

በክልሉ በደን ልማትና በኑሮ ማሻሻያ በየተፋሰሱ ከ60 ሺህ በላይ አርሶ አደሮችን ተጠቃሚ ማድረግ መቻሉን ተናግረዋል።

የደን ልማት ሥራውን በአዳዲስ ወረዳዎች ላይም የማስፋፋት ሥራ እንደሚሠራ አቶ ስንታየሁ አመላክተዋል።

የሬድ ፕላስ ኢንቨስትመንት ፕሮግራም ምዕራፍ ሁለት ማስተግበሪያ ከኖርዌይ መንግሥት በተገኘ ሃያ አምስት ሚሊዮን ዶላር ተግባራዊ መደረግ መጀመሩ የሚታወስ ነው።

# ኮሚሽኑ በኦሮሚያ ክልል ተሳታፊዎችን ለሚለዩ አካላት ሥልጠና መስጠት ጀመረ

**አዲሱ ገረመው**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ሀሳቦችን የሚሰጡ ተሳታፊዎችን ለመለየት ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር ለሚሠሩ አካላት የመጀመሪያውን ዙር ሥልጠና መስጠት ጀመረ።

በትናንትናው ዕለት በኦሮሚያ ክልል የአጀንዳ ሀሳቦችን የሚሰጡ ተሳታፊዎችን ለመለየት ከኮሚሽኑ ጋር በትብብር የሚሠሩ አካላትን በማሠልጠን ወደ ተግባራዊ እንቅስቃሴ ለመግባት የሚያስችል የመጀመሪያው ዙር ሥልጠና የተጀመረ ሲሆን፤ ሥልጠናው በክልሉ በተለያዩ ክላስተሮች የሚካሄደው የተሳታፊ ልየታ ሥራን ውጤታማ እንዲሆን ከፍተኛ ሚና እንዳለው ተገልጿል።

የምክክር ሂደቱ ተሳታፊዎችን ኮሚሽኑ ለመለየት በሚያደርገው ጥረት በተባባሪነት የተለዩትና ሥልጠናው የሚሰጣቸው ከሃይማኖት ተቋማት፣ ከሲቪክ ማኅበራት፣ ከእድሮች፣ ከመምህራን ማኅበር፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከፍርድ ቤቶች እንዲሁም ከወረዳ አስተዳደር የተወከሉ እንደሆነም ተጠቅሷል።

ኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ዋና ኮሚሽነር ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ በሥልጠናው መክፈቻ ወቅት እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ በሚገኙ የተለያዩ የፖለቲካ እና የሃሳብ መሪዎች እንዲሁም የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል መሠረታዊ በሆኑ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ የሃሳብ ልዩነት እና አለመግባባት የሚታይ ሲሆን ይህም በሀገሪቱ ለሚታዩ በርካታ ችግሮች መነሻ ምክንያት ሲሆን ይስተዋላል።



ፕሮፌሰር መስፍን አርዓያ

ይህንን ልዩነት እና አለመግባባት ለመፍታት ሰፋፊ ሀገራዊ የሕዝብ ምክክሮችን አካታችና አሳታፊ በሆነ መንገድ በማካሄድ ሀገራዊ መግባባት መፍጠር አስፈላጊ በመሆኑ ይህንኑ ሂደት እንዲመራ የኢትዮጵያ ሀገራዊ ኮሚሽን በአዋጅ ተቋቁሞ የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል ብለዋል።

እንደ ዋና ኮሚሽነሩ ገለጻ፤ ሀገራዊ ምክክሩ በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች መካከል እንዲሁም በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ያለውን ግንኙነት የማሻሻል፣ መተማመን የሰፈነበት አዲስ የፖለቲካ ሥርዓት ለመፍጠር በሚያስችል አግባብ ውይይቶቹ እንዲካሄዱ ሥርዓት የመዘርጋት፤ ከምክክሮቹ የተገኙ የመፍትሔ ምክረ ሃሳቦች በሥራ ላይ እንዲውሉ ድጋፍ በማድረግ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ እንዲገነባ እንዲሁም ወቅታዊ ችግሮች ዘላቂ በሆነ መንገድ ተፈተው አስተማማኝ ሰላም የሚረጋገጥበትን የፖለቲካ እና የማኅበራዊ መደላድል የማመቻቸት ታላላቅ ሀገራዊ ግቦችን ለማሳካት የሚካሄድ ነው።

እዚህ ውጤት ላይ ለመድረስ መከናወን ካለባቸው በርካታ ተግባራት መካከል አንደኛው የምክክሩ ተሳታፊዎችን ከፖለቲካና ሃሳብ መሪዎች፣ ከሲቪክ ማኅበራት፣ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች እና ተቋማት መካከል ግልጽ፣ ፍትሐዊ፣ አካታችና አሳታፊ በሆነ መንገድ በመለየት በምክክር ሂደቱ እንዲሳተፉ ማድረግ መሆኑን ዋና ኮሚሽነሩ ገልጸዋል።

ኮሚሽኑ ይህን ወሳኝ ተግባር በአግባቡ ለመፈጸም የሚረዳ የተሳታፊ ልየታ የአሠራር ሥርዓት በማዘጋጀት ሥራውን በማከናወን ላይ ይገኛል ያሉት ዋና ኮሚሽነሩ፤ እስካሁንም ባለው ሂደት በሲዳማ፣ በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፣ በቤኒሻንጉል፣ በጋምቤላ፣ በሐረሪ ክልሎች እንዲሁም በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ስኬታማ የሆነ የተሳታፊዎች ልየታ እንደተከናወነ አስታውቀዋል።

በሶማሌ፣ በአፋር፣ እንዲሁም በማዕከላዊ እና ደቡብ ኢትዮጵያ ክልሎችም ተሳታፊዎችን የመለየቱ ሥራ እየተከናወነ እንዳለም ጠቅሰው፤ በነዚህ ሂደቶች ሁሉ ተባባሪ አካላት ከፍተኛ አስተዋፅዖ ማበርከታቸውንም ተናግረዋል።

የተሳታፊ ልየታውን በገለልተኝነት፣ ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍል በሚያሳትፍና በሚያካትት መልኩ ለማከናወን ሠልጣኞቹ ታላቅ ሀገራዊ ኃላፊነት እንደተጣለባቸው ጠቅሰው፤ ለዚህም እንዲረዳቸው ኮሚሽኑ የቅርብ እገዛና ክትትል እንደሚያደርግ ተናግረዋል። ሥልጠናው በዋናነት በሀገራዊ ምክክር ምንነት፣ አካሄድና የሚጠበቁ ውጤቶች እንዲሁም ተሳታፊዎች የሚለየበት ሥነ ዘዴ ላይ ግንዛቤ የሚሰጥ እንደሆነም አመላክተዋል።

# የብድር መክፈያ

## እፎይታ መፈቀዱ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት ይረዳል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- አበዳሪ ሀገራት ለኢትዮጵያ የብድር መክፈያ እፎይታ ጊዜ መፍቀዳቸው ኢኮኖሚያዊ መነቃቃትና የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት እንደሚረዳ የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ዳዊት ሀየሶ አስታወቁ።

አበዳሪ ሀገራት ለኢትዮጵያ የ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የብድር መክፈያ የእፎይታ ጊዜ መፍቀዳቸውን የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ ለሕዝብ ተወካዮች የሩብ ዓመት አፈጻጸም ሲያቀርቡ መናገራቸው ይታወሳል።

የምጣኔ ሀብት ባለሙያው ዶክተር ዳዊት ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ ለአበዳሪዎች ሊከፈል የነበረውን 1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የዕዳ አከፋፈል ላይ እፎይታ መሰጠቱ ለውስጣዊ የልማት ፍላጎት እና ለትላልቅ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ማስጨረሻ ለማዋል ይረዳል።

የዕዳ ክፍያው ጊዜ መሸጋሸጉ ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ እንዳለው የገለጹት ዶክተር ዳዊት፤ ኢኮኖሚው በተወሰነ ደረጃ እንዲንቀሳቀስና እየተባባሰ የመጣውን የኑሮ ውድነት በተወሰነ መንገድ እንዲረጋጋ ሚና ይኖረዋል።

ሊከፈል የነበረ ዕዳ ምርትና ምርታማነትን ሊጨምር በሚችል ዘርፍ ላይ በማዋል ለነገ አዎንታዊ ሁኔታን መፍጠር ይገባል ያሉት ዶክተር ዳዊት፤ የኢኮኖሚ ፋይዳ በሚፈጥር ሁኔታ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንደሚገባ ጠቁመዋል።

ሆኖም ምርትና ምርታማነትን በማይጨምሩ የሥራ ዘርፎች ላይ ከዋለ ተጨማሪ ጫና ይዞ ይመጣል ሲሉም ስጋታቸውን ገልጸዋል።

ዶክተር ዳዊት እንደገለጹት፤ ሊከፈል የነበረውን ገንዘብ የውጭ ምንዛሪ ሊያስገኙ በሚችሉ በተለይ በማዕድን ልማትና የወጭ ንግድ ሊያስፋፉ የሚችሉ ጉዳዮች ላይ ማዋል ያስፈልጋል። ይህም ብድሮችን ለመክፈል የሚያስችል አቅም ለመገንባት ይረዳል።

የዕዳ እፎይታው መገኘቱ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ለሚገቡ ቁሳቁሶች፣ ለተለያዩ አገልግሎት የሚውሉ ግብዓቶች በሀገር ውስጥ ለማምረት የሚያስችል አጋጣሚን ለመፍጠር ጥሩ እድል መሆኑን የገለጹት ዶክተር ዳዊት፤ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግም ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር ይጠቅማል ብለዋል።

ዕዳዎች በሕዝብ ስም የሚመጡና የሚከፈሉ ናቸው የሚሉት ዶክተር ዳዊት፤ የዕዳ ክምችት እንዳይኖር የተገኙ ብድሮች የሕዝብ ኑሮን በሚያሻሽሉ የሥራ ዘርፎች ላይ ኢንቨስት መደረግ አለባቸው ብለዋል።

"የሕዝብ ኑሮ ከተሻሻለና የዜጎች ጤንነት ተለውጦ አምራች ዜጋ ከተፈጠረ ብድሩን የምንከፍልበትን አቅም መፍጠር ይቻላል። በሌላ በኩል መንግሥት በሕዝብ ስም የሚበደራቸውን ብድሮች አትራፊ በሆኑ ፕሮጀክቶች ላይ በማዋል ዕዳዎች በወቅቱ እንዲከፈሉ ማድረግ አለበት። ከውጭ የምናስገባቸውን እቃዎች መተካት በሚችሉና የውጭ ምንዛሪ የሚያስገኙ ፕሮጀክቶች ላይ መዋል አለባቸው" ሲሉም አሳስበዋል።

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ ብድር በተገቢው ቦታ ካልዋለ ተደራራቢ ችግሮችን ይዞ በመምጣት የፖለቲካ ሉዓላዊነት ያሳጣል። ይህም አበዳሪ ሀገራት ገቢ ሊያመነጩ የሚችሉ የኢኮኖሚ አውታር የሆኑ ተቋማትን የመግዛት እድል ይፈጥርላቸዋል።

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ ማሞ ምሕረቱ በሕዝብ ተወካዮች ፊት ቀርበው የሩብ ዓመት አፈጻጸም ባቀረቡበት ወቅት እንደገለጹት፤ አበዳሪ ሀገራት የ1 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ለኢትዮጵያ የብድር መክፈያ እፎይታ ፈቅደዋል። ይህም በኢትዮጵያ የተረጋጋ የውጭ ምንዛሪ አስተዳደር እንዲኖር ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል ብለዋል።

# ኢትዮጵያ የስደተኞችን ደህንነት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ተሳታፊ ሆኗል።

አምባሳደር መለስ እንዳሉት በኢትዮጵያ በኩል ክቡር ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በጉባኤው ላይ ባደረጉት ንግግር ኢትዮጵያ የስደተኞችን ደህንነት ለመጠበቅ እና ተገቢውን ድጋፍ ለማድረግ ቁርጠኛ መሆኑዋን አስረድተዋል።

የስደተኞችን ሕግ ከማሻሻል፣ ከትምህርት፣ እና ከጤና አንጻር በጎ እርምጃዎች መወሰዳቸውና በሚቀጥሉት ጥቂት ዓመታት የሚከናወኑ የሥራ መስኮችን በተመለከተ እንደዚሁ ክቡር አቶ ደመቀ መኮንን ማቅረባቸውን ተናግረዋል።

በስደተኞች ካምፖች አካባቢ ተገቢውን ችግኝ የመትከል ሥራ ለመሥራት ከመግባባት መደረሱን እና ኢትዮጵያ የስደተኞች ካምፕ ላይ የአካባቢ ጥበቃን ትኩረት ሰጥታ እንደምትሠራ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መግለጻቸውን አምባሳደሩ ጠቁመዋል።

በሁለት ስደተኞች ካምፕ ላይ ወደ ከተማነት ለማሸጋገር የሚያስችል ፍላጎት እንዳለ እና በስደተኞችና አስተናጋጅ ሕዝቦች አካባቢ ባለሀብቶች ሄደው መዋዕለ ንዋዮቻቸውን እንዲያፈሱ የማበረታቻ ሥራ ለመሥራት እንቅስቃሴ እንደሚደረግ መግለጻቸውንም አምባሳደሩ አመላክተዋል።

አምባሳደሩ እንዳሉት በትምህርትና በጤና በኩልም በኢትዮጵያ መንግሥት በኩል ስደተኛ ተኮር ሥራዎችን ለመሥራት ዝግጁነት መኖሩን ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ በንግግራቸው ጠቁመዋል።

የመጀመሪያው ጉባኤ ከአራት ዓመት በፊት ጄኔቭ ውስጥ ተካሂዶ እንደነበር ያስታወሱት አምባሳደር መለስ በወቅቱ ሀገራት የደረሱባቸው መግባባቶች እንደነበሩና በኢትዮጵያ በኩል ከአራት ዓመት በፊት የገባችውን ቃል ከመፈጸም አንጻር የሄደችበት ርቀት በጉባኤው በበጎ መታየቱን ጠቁመዋል።

ጉባኤው በሲዊዘርላንድ እየተካሄደ ያለ የበርካታ ሀገራት መሪዎች የተሳተፉበት ትልቅ ጉባኤ መሆኑን ተናግረው በስደተኞች ጉዳይ ጥልቅ ውይይት የተካሄደበት ስብሰባ መሆኑን ገልጸዋል። የስደተኞች ጉዳይ የትልቁም የትንሹም ሀገር ችግር በመሆኑ ይህንን ችግር በጋራ እንዴት መፍታት ይቻላል በሚል ሀሳብ ላይ በጣም ጠቃሚ ውይይት መካሄዱንም ተናግረዋል።

በዓለማችን 114 ሚሊዮን የሚሆኑ በተለያዩ ሀገራት ተሰራጭተው የሚኖሩ ስደተኞች መኖራቸውን የጠቆሙት አምባሳደር መለስ፤ ከነዚህ ውስጥ 75 በመቶ የሚሆኑት በአዳጊ ሀገራት የሚገኙ መሆናቸውን ገልጸዋል። ኢትዮጵያ ውስጥ ከአንድ ሚሊዮን በላይ ስደተኞች መኖራቸውንም ጠቁመዋል።

አምባሳደሩ እንደተናገሩት የአሁኑ ጉባኤ ዋነኛ ዓላማ ባለፈው አራት ዓመት የተደረሱ መግባባቶች ያሉበትን ደረጃ መገምገም ያስቻለ ነው። ይሄ ዓለም አቀፍ የስደተኞች ጉባኤ እያንዳንዱ ሀገር የሄደበትን ርቀት ለማየት፣ ጠንካራና ደካማ ጎኖቹን ለማግኘት፣ ለመለየት እና እርስ በእርስ ለመማማርም እንዲሁ እድል የፈጠረ ተደርጎ ሊወሰድ እንደሚችልም ጠቁመዋል።

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከስብሰባው ጎን ለጎን ከዓለም አቀፉ የቀይ መስቀል ኮሚቴ ፕሬዚዳንት ጋር ጠቃሚ ውይይት ማድረጋቸውን የጠቆሙት አምባሳደር መለስ የቀይ መስቀል ኮሚቴው ኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ ያላቸውን አድናቆትና አክብሮት በመግለጽ ከዚህ ተቋም ጋር የተሻለ ግንኙነት እንዲኖር ለመሥራት በኢትዮጵያ በኩል ፍላጎት እንዳለ መግለጻቸውን ተናግረዋል።

አምባሳደር መለስ እንደተናገሩት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ ከዓለም የምግብ ፕሮግራም ምክትል ዋና ጸሐፊ ጋርም ጠቃሚ ውይይት አድርገዋል።

በውይይታቸውም በኢትዮጵያ ስደተኞች እንዲሁም የምግብ ዋስትና ችግር ለገጠማቸው ወገኖች የሚደረገው ድጋፍ እንዲቀጥል በዓለም የምግብ ፕሮግራም ለተደረሰው ውሳኔ አድናቆትና ምስጋና ማቅረባቸውንም አምባሳደሩ ተናግረዋል።

# የአፍሪካ አየር ኃይል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በትብብር ሲሠራ መቆየቱን አንስተው፤ የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም አህጉራዊ ተልዕኮን ለማሳካት እና የጋራ ተጠቃሚነትን ለማረጋገጥ ያስችላል ብለዋል።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል የአፍሪካ ኩራት የሆነው የኢትዮጵያ አየር መንገድ አካል መሆኑን ጠቅሰው፤ የፓን አፍሪካኒዝም ሀሳብም በአየር ኃይል ሊደገም ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ከአፍሪካ ቀዳሚው የአየር ኃይል እንደሆነ ገልፀው፣ በአፍሪካ ሀገራት አየር ኃይል አዛዦች ፎረም የተሳተፉ የዘርፉ አካላት ከኢትዮጵያ አየር ኃይል ጋር በትብብር ለመሥራት ቁርጠኛ መሆናቸውን ጠቁመዋል።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ዋና አዛዥ ሌተናል ጄኔራል ይልማ መርዳሳ በበኩላቸው፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል ካለፉት አምሥት ዓመታት ወዲህ አመርቂ ውጤቶችን እያስመዘገበ እንደሚገኝ ጠቁመው፤ ይህንን ለማጠናከር ከአፍሪካ ሀገራት ጋር በትብብር መሥራት ይገባል ብለዋል።

በአፍሪካ የሚያጋጥሙ የደኅንነት ሥጋቶችን ለመቀልበስ የጋራ ትብብር ያስፈልጋል ያሉት ሌተናል ጄኔራል ይልማ፤ ለዚህም የአፍሪካ አየር ኃይል አዛዦች ፎረም መካሄዱ ወሳኝ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በፎረሙ የአፍሪካ ሀገራት አየር ኃይል አዛዦች፣ የተለያዩ ሀገራት የአቪዬሽን ተቋማት ኃላፊዎችና ወታደራዊ አታሼዎች እንደተገኙም አንስተው፤ የኢትዮጵያ አየር ኃይል በርካታ የአፍሪካ ሀገራትን በአየር ኃይል፣ በልምምድና በአየር ትራንስፖርት ዘርፎች እገዛ እንደሚያደርግ ተናግረዋል፡፡ ይህም ተጠናክሮ እንደሚቀጥል አስታውቀዋል።

አሁን ላይ የአፍሪካ ሀገራት የተለያዩ ችግሮች እያጋጠማቸው መሆኑን ጠቅሰው፤ እነዚህን ችግሮች ለመከላከልና ለመቋቋም በትብብርና በአጋርነት መሥራት እንደሚገባ ነው ያሳሰቡት።

የኢትዮጵያ አየር ኃይል ያዘጋጀው ፎረምም የአፍሪካ ሀገራት የአየር ኃይሎቻቸውን አቅም በጋራ ለማስተባበርና ቅንጅታዊ አሠራርን ለማጠናከር አስተዋፅዖ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

ይህም አፍሪካ አሁን ላይ እያጋጠማት ያለውን የጋራ የደኅንነት ሥጋቶች ለመከላከል እንደሚያስችል ጠቁመው፤ ፎረሙ በተለይም የልምድ ልውውጥ ለማጠናከርና የባለሙያዎች ልውውጥ ለማድረግ እንደሚያስችልም ተናግረዋል።

በፎረሙ ለተሳተፉ የተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት የአየር ኃይል አዛዦች ዕውቅና ተሰጥቷል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስመከላከያ ሠራዊት ክብር እንስጥ!

የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከአንድ ምዕተ ዓመት በላይ ዕድሜ ያለው የሀገርና ሕዝብ አለኝታ የሆነ ተቋም ነው። በረጅም ዘመን ታሪኩ ሀገርን እና ሕዝብን ከቅኝ ገዥዎች ከመታደግ ጀምሮ፤ ከውስጥ እና ከውጭ ከሚቃጡ የትኛውም አይነት ጥቃቶች በመከላከል ሉዓላዊነቷ እና ነፃነቷ የተጠበቀች ሀገር ከትውልድ ትውልድ በማስተላለፍ ተጠቃሽ ነው።

ከፍ ባለ የሀገር ፍቅር እና የነፃነት መሻት የተመሠረተው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት፤ በየዘመኑ በዚሁ የሀገር ፍቅር እና ከፍ ባለ የሕዝባችን የነፃነት መሻት እየተመራ፤ በብዙ የጀብዱና የተጋድሎ ትርክቶች ታጅቦ ዛሬ ላይ ደርሷል። በየዘመኑም በተሰለፈባቸው የግዳጅ ተልዕኮዎች አንቱታን ያተረፉ ብሔራዊ ጀግኖችን በመፍጠር በግንባር ቀደምትነት ተጠቃሽ ሆኗል።

ሠራዊቱ ከሀገር ውስጥ የግዳጅ ተልዕኮም ባለፈ በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ተልዕኮዎች በመሳተፍ ሀገርና ሕዝብን ያስጠሩ ገድሎችን በመፈጸም፤ የኢትዮጵያውያንን ጀግንነት በዓለም አቀፍ ደረጃ በማስተዋወቅ የማይተካ አስተዋፅዖ ያበረከተና እያበረከተ ያለ ተቋም ነው። ከ1950 ዓ.ም አንስቶ እስከ ዛሬ ድረስ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት እና በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ስር ሰላም በማስከበር ተልዕኮ ግንባር ቀደም ነው፡፡

ተቋሙ እንደ አንድ በለውጥ ውስጥ ያለች ሀገር ተቋም፤ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በተለያዩ የሪፎርም ሥርዓት ውስጥ በማለፍ ላይ ይገኛል። ይህንንም ተከትሎ እያስመዘገበ ያለው ስኬት፤ ለሀገርና ለሕዝብ የበለጠ ኩራት የሚሆንበትን ዕድል እየፈጠረለት ነው፤ ግዳጅ የማስፈጸም አቅሙንም ከፍ ባለ ደረጃ እያሳደገለት ይገኛል ።

ለዚህም መከላከያ ሠራዊቱ ላለፉት ሦስት ዓመታት ሀገሪቱ በየአቅጣጫው ያጋጠማትን የሕልውና አደጋ ከፍ ባለ የተጋድሎ መስዋዕትነት ፊት ለፊት በመጋፈጥ ሀገር እንደ ሀገር ጸንታ መቆም እንድትችል አድርጓል። ብዙ የጥፋት ትርክቶችን በመቀልበስ ሀገር ከሕልውና አደጋ ስጋት ነፃ የሆነችበትን ተጨባጭ ሁኔታ ፈጥሯል።

በጦርነት ውስጥ ራሱን እያበቃ፤ በብዙ ፈተናዎች ውስጥ ጸንቶ እየተራመደ፤ ሀገርና ሕዝብ የሰጡትን ተልዕኮ በብዙ መስዋዕትነት በመወጣት ላይ ያለው የመከላከያ ሠራዊታችን፤ ሠላማችን እና ልማታችን የሚያስጨንቃቸው ታሪካዊ ጠላቶቻችንና የእነርሱ ቅጥረኛ የሆኑ ባንዳዎች በተለይም ባለፉት ሦስት ዓመታት በብዙ ተስፋ የተንቀሳቀሱባቸውን የጥፋት ተልዕኮዎች በማምከን በታሪክ መዝገብ አዲስ ታሪክ መጻፍ የቻለ ነው።

ከጀርባው ሳይቀር እየተመታ፤ ከፍ ባለ ሕዝባዊነት፤ በብዙ ትዕግስትና ሆደ ሰፊነት የተሰጠውን ሕገ-መንግሥታዊ ኃላፊነት በመወጣት አሁን ላይ እንደ ሀገር፤ ጠላቶቻችን አስበው እና በብዙ መክረው የተረባረቡባቸው የጥፋት ተልዕኮዎች እንዲከስሙ አድርጓል። በዚህም ጠላቶቻችን ስለ ሠራዊቱ ደግመው፤ ደጋግመው እንዲያስቡ አስገድዷቸዋል ።

በግንባር በባንዳዎቻችው በኩል ገጥመው ያጡትን ድል፤ የሠራዊቱን ስም በማጥፋት በእጃቸው ለማስገባት የሞከሩትም ጥረት ቢሆን፤ ሠራዊቱ ከሕዝቡ ውስጥ የወጣ፤ የሕዝብ ልጅ ከመሆኑ ባለፈ፤ በተላበሰው ከፍተኛ ወታደራዊ ዲሲፕሊን ሳይሳካላቸው ቀርቷል። ይህም ለሠራዊቱ የተጨማሪ ኩራትና ሞገስ ምንጭ ሆኖለታል ።

መከላከያ ሠራዊቱ ትናንት ሆነ ዛሬ የተሰጠውን የሀገርና የሕዝብ ኃላፊነት በብቃት ስለመወጣቱም ሆነ አሁንም እየተወጣ ስለመሆኑ፤ ሀገር እንደ ሀገር ከነበረችበት የሕልውና ስጋት ወጥታ አሁን ላይ ያለችበት ቁመና ተጨባጭ ማሳያ ነው ። ከትናንት ዛሬ ላይ ሆነን የምንተነፍሰው የሰላም አየርም በራሱ ተናጋሪ ነው።

ይህንን እውነታ መካድ የሚቻል አይደለም ፤ይህንን የመከላከያን አዲስ ሀገርን የመታደግ በብዙ ገድል የተሞላ ትርክት ላለመስማት መሞከር አይቻልም። ሠራዊቱ ዘመኑን በሚዋጅ መንገድ በሁለንተናዊ መንገድ ራሱን እያበቃ የሚሄድበት አሁነኛ የለውጥ ጉዞም፤ የጀመርነውን ልማት በማስቀጠል ድህነትን ታሪክ ለማድረግ ለጀመርነው አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ዋነኛ ስትራቴጂክ አቅም ነው!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ስጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ስኬት እንደ ተሞክሮ !!

አስናቀ ፀጋዬ

እስካሁን ድረስ አንገብጋቢ ከሆኑና በቅጡ ካልተፈቱ የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪ ችግሮች ውስጥ የመኖሪያ ቤት በዋናነት ይጠቀሳል። ከዛሬ ሀያና ሠላሳ ዓመት በፊት በአዲስ አበባ ከተማ መኖሪያ ቤት ትልቅ ጉዳይ አልነበረም። ኅብረተሰቡ ከየትም ይምጣ ከየትም በቀላሉ የመኖሪያ ቤት ፍላጎቱን በተለያዩ አማራጮች ማሳካት ይችል ነበር።

በርግጥ በግዜው የነበረው የከተማዋ ነዋሪ ቁጥር እንደአሁኑ የበዛ አለመሆን፤ በግዜው ከነበረው በቂ የመሬት አቅርቦት ጋር ተዳምሮ የመኖሪያ ቤት ጥያቄ በቀላሉ እንዲመለስ አስተዋፅዖ ማድረጉ የሚካድ ሐቅ አይደለም። ሁኔታው በጊዜ ሂደት እየተቀየረ አሁን ላይ የከተማዋን ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ፍላጎት ለማርካት አስቸጋሪ ሆኗል ።

ችግሩን ለመፍታት ከተደረጉ ጥረቶችና እስካሁን በተለያዩ ችግሮች የተጠበቀውን ያህል መጓዝ ያልቻለው የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ አንዱ ነው። ግንባታው ሲጀምር ብዙ የከተማዋ ነዋሪዎች ከፍ ያለ ተስፋ ጥለውበት እንደነበረም የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው። በዚህም ከሁለት እስከ ሦስት መቶ ሺ የሚጠጉ የከተማዋ ነዋሪዎች ተመዝግበው በየወሩ በመቆጠብ በእጣ የቤት ባለዕድል ለመሆን በቅተዋል። እንዲያም ሆኖ ግን አሁንም በመርሐ ግብሩ ተመዝግበው በመቆጠብ ላይ የሚገኙ ነዋሪዎች ቁጥር ቀላል አይደለም ።

ከዚህ በተጨማሪም አቅም ያላቸው የከተማዋ ነዋሪዎች ከመንግሥት መሬት በሊዝ በመውሰድ በራሳቸው ቤት ገንብተው የቤት ባለቤት የሚሆኑባቸው አማራጮችም ነበሩ። በዚህም ጥቂት የማይባሉት የከተማዋ ነዋሪዎች የቤት ባለቤት ለመሆን በቅተዋል። በአስር ዘጠና የቤት ፕሮግራም በርካታ አነስተኛ ገቢ ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች የቤት ባለቤት ለመሆን ችለዋል። በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ለሚገኙና ጎዳና ላይ ለወደቁትም ቢሆን ‹‹የደሃ ደሃ›› ለተሰኙ ኅብረተሰብ ክፍሎችም የቀበሌ ቤት የሚያገኙበት ሁኔታ በግዜው እንደተመቻቸ ይታወሳል።

እንግዲህ የጋራ መኖሪያ ቤት ግንባታን ጨምሮ በልዩ ልዩ አማራጮች ቤት አልባዎችን የቤት ባለቤት እንዲሆኑ የማድረግ እንቅስቃሴ ጥሩ ጅምር የነበረ ቢሆንም፤ ካለው የከተማዋ ነዋሪ የቤት ፍላጎት ቁጥር ጋር ሊመጣጠን ግን አልቻለም። የቤት ፈላጊውን ፍላጎትም በሚገባ ማርካት አልተቻለም።

ይህንን ተከትሎም በ2005 ዓ.ም አዲስ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ምዝገባ ተካሂዷል። በዚህ ሁለተኛው ዙር መርሐ ግብር ከ700 ሺ የሚልቁ ቤት ፈላጊዎች ተመዝግበዋል። እስከ 2008 ዓ.ም ድረስ መንግሥት በ1997 ዓ.ም ተመዝግበው ቤት ሲጠባበቁ ለነበሩት የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት በዕጣ ሲያስተላልፍ ቆይቷል።

ከ2008 ዓ.ም በኋላ በአዲስ አበባ ዙሪያ በርካታ የጋራ መኖሪያ ቤቶች በግንባታ ላይ የነበሩ ቢሆንም፤ በግዜው ኦሮሚያንና አዲስ አበባን በልማት ያስተሳስራል የተባለለት የተቀናጀ ማስተር ፕላን ይፋ ይሆናል መባሉን ተከትሎ በአዲስ አበባ ዙሪያ በተነሱ አመፆች ግንባታዎቹ ቆሙ። የተጠናቀቁትንም ለባለ ዕድለኞች የማስተላለፉ ሃሳብም እዚህ ላይ ተገታ።

ኢሕአዴግ በአዲሱ የለውጥ መንግሥት ከተተካ በኋላ የከተማዋ ነዋሪዎች የቤት ጥያቄ ፍላጎት ይበልጥ ጨምሮ ታይቷል። አዲሱ የለውጥ መንግሥትም ገና ወደ ሥልጣን እንደመጣም የጋራ መኖሪያ ቤቶች ዙሪያ ያለው ችግር ውስብስብ ከመሆኑ አንጻር ጊዜ ሊፈጅበት እንደሚችል የብዙዎች እምነት ነበር ።

የለውጡ መንግሥት ወደ ሥልጣን ከመጣ በኋላ ተጀምረው የነበሩ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ በማፋጠን ለባለዕድለኞች ለማስተላለፍ ጥረት ማድረጉ አልቀረም። ችግሮቹን በመቅረፍ ስኬታማ ሥራዎችን ለመሥራትም ሲንቀሳቀስ ተስተውሏል ። ይህም ሆኖ ግን ችግሩ አሁንም የተጠበቀውን ያህል መፍትሔ እያገኘ አይደለም።

በለውጡ ማግስት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል የተቀሰቀሰው ጦርነት ለችግሩ በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ በመሆን፤ በመንግሥት የተጀመሩ ጥረቶች እንዲቀዛቀዙ አድርጓል። ቤት ፈላጊው ኅብረተሰብም ከቤት ይልቅ

> **ቤት ፈላጊው ኅብረተሰብም ከቤት ይልቅ የሀገር ሕልውና ጉዳይ ይቀድማል ብሎ የመንግሥትን አቋም ደግፎ፤ ቤቱን ረስቶ ፊቱን ወደጦርነቱ አዙሯል፡፡ መንግሥትንም በተለያየ መልኩ ደግፏል**

የሀገር ሕልውና ጉዳይ ይቀድማል ብሎ የመንግሥትን አቋም ደግፎ፤ ቤቱን ረስቶ ፊቱን ወደጦርነቱ አዙሯል። መንግሥትንም በተለያየ መልኩ ደግፏል።

የከተማው አስተዳደር በጦርነቱ መሐል ቤት ፈላጊውን በአጭር ግዜ ተጠቃሚ ሊያደርግ የሚችል የቤት ግንባታ ፕሮጀክት አቅዶ ተግባራዊ ለማድረግ ረጅም ርቀት ተጉዟል። ከነዚህ ውስጥ አንዱ ከአንድ የደቡብ አፍሪካ የቤቶች ግንባታ ኩባንያ ጋር የተደረሰው ስምምነት ተጠቃሽ ነው። በፍጥነት የሚጠናቀቁ ተገጣጣሚ ቤቶች በሙከራ ደረጃ ተሠርተው ታይተዋል ። የመንግሥት ሠራተኞች በፈለጉት አማራጭ የራሳቸውን ሥራ ተቋራጭ ቀጥረው ከመንግሥት ቦታ ተረክበው በማኅበር ቤት እንዲገነቡ ምዝገባ ተካሂዶም ነበር ።

በርግጥ እየጨመረ ከመጣው የከተማዋ ነዋሪዎች የመኖሪያ ፍላጎት አንፃር የመኖሪያ ቤት ችግሩን እንዲህ በቀላሉ መፍታት ይቻላል ተብሎ መገመት የሚቻል አይደለም። ችግሩ ጊዜና ሀብት የሚፈልግ ነው። ይህም ሆኖ ግን አሁን ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከሚታየው ፕሮጀክት አፈጻጸም አንጻር ተስፋ ሊጣልባቸው የሚችሉ ነገሮች እንዳሉ መገመት አያዳግትም።

የአንድነትና እንጦጦ ፓርክ፣ የወዳጅነት አደባባይ፣ የአብርኆት ቤተ መጽሐፍት፣ የመስቀል አደባባይና ሌሎችም የተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች ላይ የታየው፤ ፕሮጀክቶችን በጥራትና በፍጥነት የማጠናቀቅ አዲስ ልምድ፤ ለጋራ ቤቶች ግንባታ ስኬት/ውጤታማነት ትልቅ ተጨባጭ ተሞክሮ ተደርጎ ሊወሰድ የሚገባ ነው ።

ከነዚህ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በመነሳትም የጋራ መኖሪያ ቤቶችን ግንባታ በፍጥነት እና በጥራት በመገንባት ለነዋሪዎች ማስተላለፍ የሚቻልበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው። በተለይም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሆነ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ግንባታ ጽሕፈት ቤት ከዚህ ተጨባጭ ተሞክሮ ተገቢውን ትምህርት ሊወስድ ይገባል።

# ነፃ ሃሳብ

## የግብርናውን የተለወጠ መንገድ የተከተለው የማዳበሪያ አቅርቦት

ዘካርያስ

በሀገሪቱ የግብርና ምርትና ምርታማነት እያደገ መጥቷል፤ ለእዚህም በዋና ዋና ምክንያትነት ሊጠቀሱ ከሚችሉት መካከል መንግሥት ለአርሶ አደሩ ማደበሪያ በድጎማ እያቀረበ ያለበት ሁኔታ አንዱ ነው። ይህንንም መንግሥት ከሶስት ዓመት በፊት 15 ቢሊዮን ብር፣ ባለፈው ዓመት ደግሞ 21 ቢሊዮን ብር ለማዳበሪያ መድቦ ከሠራበት ሁኔታ መረዳት ይቻላል።

ዘንድሮም ከእስከ አሁኑም የሚልቅ ገንዘብ ለማዳበሪያ ተመድቦ ግዥ እየተፈጸመ ነው። የዘንድሮው የማዳበሪያ ወጪ 930 ሚሊዮን ዶላር መጠየቁን የግብር ሚኒስቴር መረጃ ያመለክታል። እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም የ 14 ነጥብ 79 ሚሊዮን ኩንታል ማዳበሪያ ግዥ ተፈጽሟል። አስቀድሞ የተገዛው ማዳበሪያም በከፍተኛ ርብርብ ሀገር ውስጥ መግባት ከጀመረ ቆይቷል።

ማዳበሪያ መግዛት አንዱ ከፍተኛ ሥራን የሚጠይቅ ተግባር ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ማዳበሪያውን ወደ መሀል ሀገር ከዚያም አርሶ አደሩ ዘንድ በፍጥነት ማድረስ ነው። የቱንም ያህል ገንዘብ ለማዳበሪያ ቢመደብ ማዳበሪያው በወቅቱ ከወቅቱም ቀደም ብሎ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አርሶ አደሩ እጅ መድረስ ይኖርበታል።

ማዳበሪያ ከወደብ በማንሳትና ወደ ክልል በማሰራጨት በኩል ቀደም ሲልም ጥሩ ተሞክሮ አለ። እንዳለፉት ዘመናት ሁሉ ማዳበሪያ ወደብ በደረሰ ቁጥር ከባድ መኪኖችና የባቡር አገልገሎት ማዳበሪያ ማጓጓዝን የሥራቸው ሁሉ ቅድሚያ እንዲያደርጉት ሆኖ የማጓጓዙ ሥራ ይካሄዳል፤ ዘንድሮም ይኸው በከፍተኛ ርብርብ እየተፈጸመ ነው።

በዚህ ሁሉ ድካም ሀገር ውስጥ የገባው ማዳበሪያ አርሶ አደሩ እጅ እንዲገባ ከማድረግ አኳያ ባለፉት ዓመታት ክፍተቶች ተስተውለዋል፤ ይህንንም በአንዳንድ ክልሎች አርሶ አደሮች ሲያነሱ የነበረው ቅሬታም ይህንኑ ይጠቁማል፤ የባለፈው ዓመት ቅሬታ ግን ሞቅ ያለ ነበር። ይህ የሆነው ደግሞ መንግሥት ከመቼውም ጊዜ የላቀ ገንዘብ ለማዳበሪያ መድቦ እየሠራ ባለበት ሁኔታ ነው።

ለእዚህ ቅሬታ ከተለያዩ የመንግሥት አካላት ይሰጡ የነበሩ ምላሾችም የአርሶ አደሩን ቅሬታ ያጤኑ ነበሩ ማለት ያስቸግራል። ማዳበሪያው ማህበራት መጋዘን ውስጥ እንዳለ በመጠቆም (የሌለውን ማዳበሪያ) መጋዘን ውስጥ ያስቀመጡ አካላት በአስቸኳይ ለአርሶ አደሩ እንዲያደርሱ ማሳሰቢያ የሚሰጡ አካላትም ነበሩ። ማዳበሪያ ላይ ለተነሳው ቅሬታ አንዱ ችግር ግዥ ሂደት ላይ ከተፈጠረ ችግር የመነጨ ቢሆንም፣ በወቅቱ ግን አልተነገረም።

እንደሚታወቀው ያለፈው ዓመት የማዳበሪያ ግዥ የዘገየበት አንዱ ምክንያት በሩሲያና ዩክሬን መካከል የተቀሰቀሰው ጦርነት ነው። እነዚህ በግብርና ግብዓቶችና ምርቶች አቅርቦት የሚታወቁ ሁለት ሀገሮች ጦርነት ውስጥ ሲገቡ ኢትዮጵያ ብቻ አልነበረችም የታወከችው ። ከእነዚህ ሀገሮች ስንዴ ፣ ማዳበሪያና የመሳሰሉትን ግብዓቶችና ምርቶች

> **ማዳበሪያ መግዛት አንዱ ከፍተኛ ሥራን የሚጠይቅ ተግባር ነው፤ ሁለተኛው ደግሞ ማዳበሪያውን ወደ መሀል ሀገር ከዚያም አርሶ አደሩ ዘንድ በፍጥነት ማድረስ ነው። የቱንም ያህል ገንዘብ ለማዳበሪያ ቢመደብ ማዳበሪያው በወቅቱ ከወቅቱም ቀደም ብሎ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ አርሶ አደሩ እጅ መድረስ ይኖርበታል**

የሚገዙ የዓለም ሀገሮችም ናቸው። ኢትዮጵያ በወቅቱ ኤልሲ ከመክፈትና ከመሳሰሉት ጋር ተያይዘው የተፈጠሩ ችግሮችም ነበሩባት፤ በዚህ ላይ ወደ ዝርዝሩ አልገባም፤ በወቅቱ መንግሥት ሰፊ መግለጫዎችን ሰጥቷልና።

ብዙ ፈተና አልፎ ሀገር ውስጥ ገብቶ ክልሎች እጅ የደረሰው ማደበሪያ ለሕገወጦች ሲሳይ የሆነበት ሁኔታ ታይቷል። በክልሎች ማዳበሪያ በሕገወጥ መንገድ ይዘዋወር ነበር፤ አርሶ አደሩ የማዳበሪያ ያለህ ሲል በነበረበት ወቅት እነዚህ ሕገወጦች በድጎማ ለአርሶ አደሩ መቅረብ ያለበትን ማዳበሪያ በውድ ዋጋ ሲቸበችቡት ነበር።

በአንዳንድ ክልሎች አርሶ አደሩ የማዳበሪያ ያለህ እያለ ሲጮህ ማደበሪያ በአደባባይ በሕገወጦች መቸብቸቡ ተጠቁሟል፤ በዚህ ሕገወጥ ተግባር ውስጥ ደግሞ የመንግሥት ባለሥልጣናትም /አመራሮች/ ተሳትፈውበታል።

በሲዳማ ክልል በርካታ ባለሥልጣናት በዚህ ወንጀል ተጠርጥረው ጉዳያቸው በፍርድ ሂደት ላይ ስለመሆኑ መረጃዎች ይጠቁማሉ። በማደበሪያ ላይ በዚህ ልክ ሕገወጥነት ሲፈጸም ይህ የመጀመሪያ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም፤ ትልቅ ቀውስ ነበር።

ያለፈው ዓመት የማዳበሪያ ጉዳይ ብዙ ያነጋገረበት ወቅት ነበር። የግብርናው ሥራ ቆሞ በማይጠብቅበት በዚያ የዘር ወቅት የማዳበሪያው አቅርቦት ዘግይቷል፤ ለቀበኞች ተዳርጓል። ከዚህ ውጪም የመኸር ወቅት የዘር ሥራ እየተጠናቀቀ ባለበት ነሀሴ ወር መጨረሻ አካባቢ ማዳበሪያ ወደ ሀገሪቱ ቢገባ ብዙም የሚፈይደው የለም። ምን አልባት ዘግይተው ለሚዘሩ ሰብሎች፣ ለመስኖ እርሻ ሊጠቀም ይችላል።

መንግሥት ዘንድሮ ያ ችግር እንዳይመለስ የሚያስችል ርምጃ ወስዷል። በማዳበሪያ ግዥ ላይ በርካታ ማሻሻያዎችን አድርጎም ማዳበሪያ ለማቅረብ እየሠራ ነው። ከችግር መማር ይሏል ይሄ ነው። መረጃዎች እንዳመለከቱት፤ ዓምና የመጀመሪያዋ ማዳበሪያ የጫነች መርከብ ጅቡቲ የደረሰችው ታህሳሰ 18 ቀን 2015 ነበር፤ ዘንድሮ የመጀመሪያውን ማዳበሪያ የጫነችው መርከብ ጅቡቲ ወደብ የደረሰችው በጥቅምት ነው። ከዚያም በመቀባበል ወደ መሀል ሀገር መጋዘን እንዲደርስ እየተደረገ ያለበት ርብርብም ሌላው ለጉዳዩ የተሰጠው ትኩረት ማሳያ ነው።

እንዲገባ የታቀደው ማዳበሪያ መጠንም ለግዥው የተመደበው ሀብትም ከፍተኛ መሆኑ ሲታይ ባለፈው ዓመት የታየው ችግር እንዳይደገም የተወሰደ ርምጃ ብቻ አይደለም ብሎ መውሰድ ይቻላል። በማዳበሪያ አቅርቦት ላይ ትልቅ እምርታ የታየበት ዘመን ላይ መደረሱን እንዲሁም የግብርናው የምርት ወቅት መጨመርንም ያመለክታል።

ማዳበሪያውን በወቅቱ አርሶ አደሩ ዘንድ ማድረስ የሚያስችል ሁኔታ መፈጠሩ ነው፤ ይህ መሆኑ ባለፈው የመኸር ወቅት በማዳበሪያ አቅርቦት መጓተት ሳቢያ በአርሶ አደሩ የቀረበው ጥያቄ ዘንድሮ እንዳይደገም ያስችላል። የማዳበሪያ ቀበኞች ቀና ቀና የሚሉት እጥረት ሲፈጠር እንደመሆኑ እጥረቱ መፍትሄ ስለተቀመጠለት እርማቸውን ያወጣሉ ብሎ መውሰድ ይቻላል። ለነገሩ አመለኞች እጥረት ሲፈጠር ብቻ አይደለም ሕገወጥ ድርጊቱን የሚፈጽሙት፤ ሰው ሰራሽ እጥረት በመፍጠርም ነው። ይህን ሕገወጥነት ለመቆጣጠር ከወዲሁ መዘጋጀት ያስፈልጋል።

የዘንድሮውን የማዳበሪያ አቅርቦት ከዚህ ሁሉ በላይም ሊነገርለት ባይ ነኝ። የማዳበሪያ አቅርቦቱ ሀገሪቱ የተያያዘችውን የግብርና ሥራ ስፋት ታሳቢ ያደረገ ነው ብሎ መናገር ይቻላል። ከመኸርና በልግ ወቅት በተጨማሪ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት እየተካሄደ ነው። ማዳበሪያው ሀገር ውስጥ የገባበት ወቅትም፣ መጠኑም ይህንን ሁሉ ታሳቢ ነው ማለት ይቻላል።

በበጀት አመቱ ከ800 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የግብርና ምርት ለማምረት ታቅዷል። ይህን ከፍተኛ መጠን ያለው ምርት ለማምረት እንደማዳበሪያ ያሉ ግብዓቶች በስፋትና በፍጥነት መቅረብ ይኖርባቸዋል። ዘንድሮ ለማቅረብ የታቀደውን ማዳበሪያም ሆነ የቀረበበት ፍጥነት የታሰበውን እቅድ ለማሳካት ትልቅ ሚና ይኖረዋል።

እንደሚታወቀው ፤አርሶ አደሩ በመኸር እርሻው ሙሉ አቅሙን አሟጦ እንዲጠቀም እየተደረገ ይገኛል። በምንም አይነት መልኩ ማሳ ጦም እንዳያድር እየተደረገ ነው፤ ርግረጋማ ሥፍራዎች ለግብርና ሥራ እየዋሉ ናቸው፤ የበቆሎ ሰብል በእሸቱ በእጅጉ እንደሚፈለግ ይታወቃል፤ ሰብሉን በእሸቱ ጥቅም ላይ እንዲውል በማድረግና ማሳውን በሌላ ሰብል በመሸፈን ተጨማሪ ምርት እንዲሰጥ እየተሠራ ነው።

በዓመት አንዴ ከማምረት እየተወጣ ነው። ሁለትና ሶስቴ ማምረት ውስጥ ተገብቷል። በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ሰፋፊ ሥራዎች እየተሠሩ ያለበት ሁኔታም ይህን ያመለክታል። የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በተጀመረበት የመጀመሪያው ዓመት ሶስት ነጥብ ስድስት ሚሊዮን ፣ በቀጣዩ ዓመት 25 ሚሊዮን ፣ ባለፈው ዓመት ደግሞ 47 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተገኝቷል።

በልማቱ የሚገኘው ስንዴ በየዓመቱ እየጨመረ የመጣ ሲሆን፣ ዘንድሮ በዚህ የስንዴ ልማት 117 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ታቅዶ እየተሠራ ነው፤ ለእዚህም ሶስት ሚሊዮን ሄክታር ማሳ በዘር እንደሚሸፈን ይጠበቃል። ከበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የሚገኘው ምርትም በዘር የሚሸፈነው ማሳ ብዛትም በየአመቱ እያደገ መጥቶ ነው እዚህ ደረጃ ላይ የደረሰው።

ይህ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ከመኸር በተረፈ ማዳበሪያ የሚሠራ አይነት አይደለም፤ ልማቱ እየሰፋ እንደመምጣቱ ራሱን የቻለ የማዳበሪያ አቅርቦት ይፈልጋል። የማቅረቢያው መንገድም ይህን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል። የዘንድሮ ማዳበሪያ አቅርቦት ብዛትም የመስኖ ልማቱ በሚጀመርበት ወቅት መድረሱ ይህን ልማት በእጅጉ ታሳቢ ያደረገ ነው ብሎ መናገር ይቻላል።

የበጋ መስኖ ስንዴ ልማቱ በየጊዜው እየጨመረ ነው፤ በመኸር ወቅት ለማግኘት የሚታቀደው ምርትም እንዲሁ እየጨመረ ይመጣል፤ በዚህ ላይ የበልግ ወቅት አለ፤ የማዳበሪያ አቅርቦቱም ይህን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ እንዲሆን ዘንድሮ እንደተሠራው ሁሉ በቀጣይም በትኩረት መሥራት ይገባል።

# ወቅታዊ

## "ማንም ይሁን ማን ከውጪ በወረራ መልክ ይምጣ፤ ተቀጥሮ ይምጣ፤ ኃይል አሰባስቦ ታጥቆ በጉልበት ይምጣ ልክ ማስገባት የኛ ሥራ ነው"



- ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ

የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም

**በትናንት እትማችን የጦር ኃይሉች ጠቅላይ ኢታማዦር ሹም ፊልድ ማርሻል ብርሀኑ ጁላ ሰሞኑን አጠቃላይ በሆነው የሀገር ሰላም እና ደህንነት ለጋዜጠኞች የሰጡትን መግለጫ የመጀመሪያ ክፍል አቅርበናል። በዚሁ እትማችን በሕዝብ ተወካዮች ምክርቤት በሸብርተኝነት ከተፈረጀው ሸኔ ጋር የተደረገውን ድርድር ጨምሮ በአማራ ክልል ስለተፈጠረው ግጭት የሰጡትን አስተያየት አቅርበናል።በዛሬው የመጨረሻ እትማችን ፊልድ ማርሻሉ በአማራ ክልል ስላለው እውነታና ሌሎች የጸጥታና የደህንነት ጉዳዮች ዙሪያ የሰጡትን መግለጫ የመጨረሻ ክፍል ይዘን ቀርበናል።**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ -** እኛ መጀመሪያም ያ ግጭት/በአማራክልል የተፈጠረው ግጭት / እንዲፈጠር አልፈለግንም። በጣም ነው ያባበልነው። ያባበልንበት ምክንያትም፤ ፋኖ የሚል ሽፋን ስላለው ነው። መከላከያ ሠራዊትን መምታት ሲጀምር ፋኖ የሚለው ሽፋኑ ተገፈፈ። ፋኖ የሚለው ጭንብል ወለቀ። መከላከያ ሠራዊትን የሚመታ ጸረ ሰላም ኃይል ነው፤ ጽንፈኛ ነው። ከፋኖነት ጋር የሚገናኝ አይደለም የሚለው ነገር ተረጋገጠ።

ከዚያ ሕግን በተከተለ መንገድ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ታውጆ ርምጃ ተወስዷል። አሁን ከባድ ኪሳራ ደርሶባቸዋል። እንደዜጋ ሊደርስባቸው የማይገባ የነበረ፤ ግን ተገደን የገባንበት ኪሳራ ደርሶባቸዋል። አሁን ዋና ኃይሉ ተራግፏል። አሁን ይህን ያቀነባበሩ ለረዥም ጊዜ የሚታወቁ ሽፍቶች እና ከእስር ቤት ያመለጡ ወንጀለኞች ናቸው ። እነዚህ ሽፍቶች ናቸው የእከሌ አካባቢ ፋኖ መሪ ነን የሚሉት።

የሚታወቁ ሽፍቶች የነበሩ ናቸው። ለብዙ ጊዜ። እነሱናቸው አሁን የቡድን መሪ፣ የፋኖ መሪ፣ የጎጃም፣ የምዕራብ ጎጃም፣ ምናምን እያሉ የሚወጡ ያሉት። አንዳንዶቹ ደግሞ ሰው ገለው የታሰሩ፤ በሌላ ወንጀል የታሰሩ፤ ዘርፈው የታሰሩ፤ ከእስር ቤት የወጡ፤ ያመለጡ ናቸው። አንዳንዶቹም ከጸጥታ ኃይል ተወናብደው እዛ የገቡ ናቸው።

አሁን ሠራዊታችን በጣም ጥሩ ሥራ ሠርቷል። በፊት ዞኖች፣ ትላልቅ ከተሞች ስጋት ላይ ወድቀው ነበር። መዋቅሩ "ፓራላይዝድ" ሆኖ ነበር። አሁን መዋቅሩ በሚገባ ተደራጅቷል፣ ተዋቅሯል። የሚታገል መዋቅር መጥቷል። እንደ መዋቅር ማለት ነው። እንደ ግለሰብ እዛም፣ እዚህም እያስመሰለ የሚኖር የለም ማለት አይደለም። ግን እንደ መዋቅር ሙሉ መዋቅሩ ተስተካክሏል።

ከተሞች ሰላም ናቸው። ገጠሮች በአብዛኛው ሰላም ናቸው። አሁን ወደ ሽለቆ፣ ወደ ቆላ ወርዷል። የወረደው ለምንድ ነው? አንደኛ ያለ አቅሙ ነው የገጠመው። ሁለተኛ የገጠመበት ምክንያት የተሳሳተ ነው። ሶስተኛ የራሱን ሀገር ሠራዊት ነው የገጠመው። ይሄ በመሆኑ ምክንያት፤ ሕዝቡም አየ፤ ሕዝቡም ይሄ ኃይል ወደ አደጋ እየወሰደን ነው አለ። የነበረው ልፍስፍስ መዋቅር ተቀየረ።

ለዚህ ያበቃቸው በመዋቅሩ ውስጥ የነበረ በሽታ ነበር። ከባድ፣ መጥፎ ሥራ የሠሩ አሉ "እዳው ገብስ ነው"። አሁን ይሄ አካሄድ የአማራን ሕዝብ ፤በአጠቃላይም ኢትዮጵያንም እንደሚጎዳ ያመኑ የተቀበሉ ሰዎች ወደ ኃላፊነት መጥተው፤ አዲስ መዋቅር አደራጅተው፣ ገምግመው፣ አጥርተው፣ መድበው እየሠሩ ነው። የመከላከያ ሠራዊት ደግሞ ለነሱ ምቹ ሁኔታ በመፍጠር በጣም ትልቅ፣ ሰፊ የሚመሰገን ሥራ ሠርቷል።

ጠላት ደግሞ በእጅጉ ተዳክሟል። የቀሩት ምህረት ሊሰጡኝ አይችሉም የሚሉ ናቸው ፤ ምክንያቱም የኋላ ታሪካቸው ከባድ ወንጀል አለው። ተጨማሪ አሁን ወንጀል ፈጽሙ። "እኔ ምህረት ሊሰጠኝ የሚገባኝ ሰው አይደለሁም" ብለው ያመኑ ሰዎች ናቸው የቀሩት። ወንጀልህ ትልቅ ይሁን ትንሽ ምህረት መንግሥት ካደረገ፣ ምህረት ነው።ምህረት ምህረት ነው። ለእነሱም ምህረት አይደረግም የሚል ነገር የለኝም።

የሄዱበት መንገድ ግን ምንም ለአማራ ሕዝብ ጠብታ የሚጨምርለት የለውም። ያከስረዋል። እስካሁን ባለውም አከስሮታል። ብዙ ሰው ንብረት አጥቷል። የሕዝቡን መኪና ቀምተውታል፤ ብር አምጣ ብለው ቀምተውታል፤ መንገድ ዘግተውበታል፤ እንዳይነግድ አድርገውታል፤ እንዳይገናኝ አድርገውታል፤ ቱሪስት እንዳይገባ አድርገውታል፤ እና የአማራ ሕዝብ አሁን ተጠቀመ? ትክክል አይደለም።

በጣም የሚያሳፍረው ነገር መከላከያ ሠራዊቱን ምንድን ነው ያሉት "እስላም መጣ፣ እስላም መጣብህ፣ ሃይማኖትህን እንትን ሊያደርግ ነው፤ ና ማዳበሪያ ውሰድ፣ መንግሥት የከለከለህን ማዳበሪያ ውሰድ፤ መንገድ ዝጋ፤ ከኛ ጋር ሁን፤ ሴቶች ይደፍርብሃል፤ "ሸኔ ነው" እያሉ ነው የመከላከያ ሠራዊትን ስም ሲያጥላሉና ሲበክሉ የነበሩት።

መከላከያ ሠራዊት ግን በዲሲፐሊን የታነጸ፣ ሕዝባዊ ወገንተኝነት ያለው፣ እሴት ያለው ስለሆነ ወደ አማራ ክልል ገብቶ፤ ለአማራ ክልል ሕዝብ ማንነቱን አሳይቶ፤ ሕዝቡ እንደዚህ አላላቹህም እንዴ? "ዋሽታችሁናል፣ አታላችሁናል፣ አታላቹህ ወደ አልሆነ አዘቅት ውስጥ አስገብታችሁናል" ብሎ አፋጦ ይዟቸዋል። እና ነፃ አውጪ ማለት ይሄ ነው?።

ነፃ አውጪ እኮ ማን ከማን ነጻ እንደሚወጣ አስቀምጦ፣ በትጥቅ ትግል የሚፈታ የፖለቲካ አላማ አስቀምጦ፣እስትራተጂ ነድፎ፣ ጥበብ ነድፎ፣ ማንን እንደሚያቅፍ አስቀምጦ፣ማንን በጠላትነት ፈርጆ እንደሚወጋ አስቀምጦ እንጂ ዝምብለህ አደበላልቀህ ሕዝቦችን ሰድበህ ፤ሌላውን አዋርደህ፤ ሌላውን ከፍ አድርገህ እንደዚህ አይነት ትግል ዓለም ላይ የለም። ስለዚህ አማራ ክልል የተደረገው ነውጥ ለአማራ ክልል በጣም አደገኛ፤ ለአማራ ማኅበረሰብ አደገኛ፤ ለኢትዮጵያም የሚጎዳ፤ ታይቶ የማይታወቅ ነገር ነው።

ይሄን የግድ ማስተካከል ስላለብን እያስተካከልን ነው። በከፍተኛ ደረጃ አስተካክለናል፤ ከፍተኛ የሆነ ሰላማዊ ሁኔታ እየተረጋገጠ ይገኛል፤ የቀረ አለ ፤ይሠራል። እስከአሁን የቆየበት ምክንያት መታወቅ አለበት። እነዚህ ሰዎች እንደዚህ አይነት ጽንፈኞች ግንባር ይዘው አይዋጉም፤ ግንባር ይዘው አይገጥሙም፤ ሕዝቡ ውስጥ ነው የሚደበቁት፤ ከሕዝብ ጋር አትመታቸውም። ከሕዝብ ነጥለህ ነው የምትመታቸው። ከሕዝብ ነጥለህ ለመምታት ጊዜ ይጠይቃል፤ ልፋት ይጠይቃል፤ ይሄ ስለሆነ ነው የቆየው። እራሱ ግንባር ፈጥሮ፣ ምሽግ ይዞ ከመከላከያ ጋር ለመግጠም የሚያስችል አቅም የለውም። ለአቅመ አዳም አልደረሰም።

ስለዚህ ሕዝቡ ውስጥ ነው የሚደበቀው። ቤተክርስቲያን ነው የሚገባው። ቤተክርስቲያን ሲገባ ቤተክርስቲያን አትመታም። እንደዚያ ቢሆን ኖሮ የአማራ ክልል ቤተክርስቲያኖች አልቀው ነበር። ቤተክርስቲያን ይገባል፤ ቄስ ስር ይገባል፤ ይሄን ለይተህ ምን እርምጃ ለመውሰድ በጣም ከባድ ነው። ገበሬ ጋር ይገባል፤ ገበሬ እና እሱን ለመለየት በጣም ያስቸግራል፤ ጊዜ ይጠይቃል። ሕዝብን እንደከለላና ምሽግ ተጠቅመህ እየተዋጋሁ ነው ብለህ መፎከር አግባብ አይደለም። አሁንም ጊዜ ይጠይቃል።

ምክንያቱም ሕዝብና ጽንፈኛው ተለይቶ ነው እርምጃ መወሰድ ያለበት። ሕዝባችን በእነሱ ምክንያት መጠቃት የለበትም። ከባድ ነው፤ ከሕዝብ ውስጥ እንደዚህ አይነት ሰርጎ ገብ፣ ጽንፈኛ ነጥለህ መደምሰስ ከባድ ነው። መደበኛ ጦርነት አይደለም፤ ጊዜ ይወስዳል። አሁን ግን

> ለዚህ ያበቃቸው በመዋቅሩ ውስጥ የነበረ በሽታ ነበር። ከባድ፣ መጥፎ ሥራ የሠሩ አሉ "እዳው ገብስ ነው"

ሕዝቡ እያወቀ ነው፤ ከሕዝቡ እየተነጠሉ ነው፤ ሕዝቡም አላስጠጋ እያለ ነው፤መዋቅሩም እየተጠናከረ ነው። ከባድ ኪሳራ ደርሶበታል፤ አቅሙ ተዳክሟል፤ የሚቀር ሥራ ግን አለ። እሱ ላይ ነው የእኛ ሥራ የሚሆነው።

**ጥያቄ- ከድሮን ጥቃት ጋር በተያያዘ ሠራዊቱ ሕዝቡ መሀል የድሮን ጥቃት ፈጽሟል የሚሉ የተለያዩ ውዥንብሮች እየወጡ ነው፤ ይሄን በተመለከተ ምን የሚሉት አለ?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ -** ድሮን እኮ የተሰራው ለጦርነት ነው። ለውጊያ ነው። የገዛነው ልንዋጋበት ነው፤ እንጂ ድሮን አለን እያልን በሚዲያ ልንገልጸው አይደለም። የጦር መሳሪያ ነው፤ ልክ እንደክላሽ። ክላሽ የአቅሙን ይሰራል፤ ሌላውም የአቅሙን ይሰራል፤ ድሮንም የራሱን ሥራ ይሰራል። ድሮን እኛ የምንጠቀመው ለስብስብ ኢላማ ነው። በወታደራዊ አባባል ስብብስ ኢላማ የሚባል ነገር አለ፤ ስብስብ ኢላማ ማለት የጠላት ጠንካራ ቋጠሮ ማለት ነው።

የጽንፈኛውን ስብስብ ስናገኝ በድሮን እንመታለን። ገጥሟል እኮ፤ እኔ መሳሪያ ልመርጥለት ነው። አይ ድሮን ተውና ክላሽ ለክላሽ እንግጠም እያለ ነው ያለው?! ይሄ በመሆኑ ምክንያት ሕዝብ ላይ ድሮን አንጠቀምም ፤ አይተኮስም። መንደር ላይም አይተኮስም። የጠላት ስብስብ ሲገኝ ግን ይተኮሳል። ደግሞም ድሮን ይሄንን ያህል ተጠቅመናል ብዬ ልወስድ አልችልም። ባለን አቅም ልክ አልተጠቀምንም፤ የተለየ ምርጥ ኢላማ ሲገኝ ግን እንተኩሳለን። እሱንም ለሕዝቡ ጥንቃቄ አድርገን ማለት ነው።

ለሕዝቡ የማሳስበው ነገር አለ። ከጽንፈኛ ጋር አትደባለቁ፣ ልጆቻችሁ የሚፎክር የሚሸልል ጽንፈኛ አይተው እሱ ጋር እንዳይሄዱ፤ ልጆቻችሁን ያዙ። ሰባ፣ ሰማንያ ጽንፈኛ ተሰብስቦ ከተገኘ ወይ ሊያጠቃ፣ወይም ሊማከር ወይም ሲመገብ ካገኘነው እንመታለን። ይሄ ይቀጥላል። ድሮን የጦር መሳሪያ እንጂ የተለየ ነገር አይደለም። የሚተኮስበት ባለቤት አለው፤ ከሕዝብ ጋር የሚያገናኘው ነገር የለውም። እንደውም አንዳንዱ ኢላማ ሕዝቡ ውስጥ በመሆኑ ቤተክርስቲያን በመሆኑ የተውነው አለ፤ እያወቅን ፤እያየን። ይሄ ከሕዝባዊ ባህሪያችን የሚመነጭ ነው።

ከዚህ ባለፈም እኛ የምንገዛበት ሕግ አለን። ዝም ብለን በዘፈቀደ የምንሰራ ሽፍቶች አይደለንም። እነሱ ናቸው በዘፈቀደ የሚሰሩ ሽፍቶች። አሮጊት የሚገሉ፣ ሽማግሌ የሚገሉ። ለምን እኔን አልደገፍከም፤ ለምን እከሌ የሚባል ፓርቲ ትደግፋለህ ብለው ሰው የሚገሉ እነሱ ናቸው። እኛ የእከሌን ፓርቲ ለምን አትደግፍም፣ ለምን የእከሌን ፓርቲ ደገፍክ ብለን ሰው አንገድልም። እኛ ጦርነት የገጠመንን ነው የምንገጥመው። ከገጠምክ በኋላ ደግሞ ቻለው፤ ቻለው ነው። ስለዚህ ኢላማው ከተገኘ ይሄንን በየትኛውም ፀረ ሰላም ኃይል ላይ እንጠቀማለን። ሕዝቡ ግን እንዳይጎዳ እንጠነቀቃለን።

**ጥያቄ፡ ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ እዚህ እዛም የሚነሱ የሰላም እጦቶች መካከል በአሳቤያቸው በጣም ጽንፈኛ በሚባሉ አካላት ሠራዊቱን ኢላማ የማድረግ አዝማሚያዎች ተደጋግመው ታይተዋል ። የዚህ መነሻ ምክንያቱ ምንድን ነው ?ከሰሞኑ እየሰማን እንዳለነው ደግሞ ሠራዊቱ ተበትኗል፤አለመግባባት ውስጥ ነው ያለው። የሚሉና ሠራዊቱ ወደ ካምፕ ይመለስ የሚሉ የሰላማዊ ሰልፍ ጥሪዎች እየቀረቡ ነው።ይህንን እንዴት ያዩታል?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ -** ሠራዊቱ ላይ ዘመቻ የከፈቱ ሰዎች ግማሹ ቅጥረኛ ባንዳ ነው። ምንም ጥያቄ የሌለው። ሠራዊቱ እንደ ኢትዮጵያ ሠራዊት በመሆኑ ምክንያት ሀገሪቷ የመከላከል አቅሟ እንዲዳከም እንዲሸረሸር በማድረግ ለጥቃት የተጋለጠች እንድትሆን የሚሰሩ ኃይሎች አሉ። ዘመቻ የከፈቱት ሰዎች ተልእኮ ተቀብለው ነው።

የኢትዮጵያ ሠራዊት አሁን ያለው ጠንካራ ሠራዊት ነው። ጠንካራ ሠራዊት እንደሆነ ጠላቶቻችንም ያውቃሉ። ስለሚያውቁ ይህ ሠራዊት እንዲዳከም ይፈልጋሉ።ይህንን ለማሳካት መአት ቅጥረኛ ገዝተዋል ፤ደመወዝ ይከፍላሉ፤ ሚዲያ ይሰጣሉ፤ሠራዊቱ ላይም ዘመቻ እንዲከፈት ያደርጋሉ። አንዱ ይሄ ነው።

ሁለተኛው ሀገር ቤት የኛ የሚሏቸው ታጣቂዎችን ልክ በማስገባት ፍላጎታቸው እንዳይሳካ በማድረግ በደንብ የሠራው መከላከያ ነው። እነሱ የሚፈልጉትን በትጥቅ ትግልም ፤በሰላማዊ ሰልፍም፤ በሌላም አድርገው ሀገር ለማፍረስ ለማበጣበጥ የእርስ በእርስ ጦርነት ለመፍጠር የሚያደርጉትን ነገር የመከተው መከላከያ ነው።

ምንም ማድረግ አቃታቸው። ያልሞከሩት እኮ የለም። በመፈንቅለ መንግሥት ሞክረዋል፤ ሰላማዊ ሰልፍ አስመስለው ሞክረዋል፤ ፎክረዋል አደራጅተዋል፤ አስታጥቀዋል መከላከያ ላይ ጥቃት እንዲደረግ አድርገዋል። ሁሉንም መከላከያ ሥርዓት አስይዟል። ምንድነው የኛ ፍላጎት እንዳይሳካ ያደረገው ብለው ጠንካራ ጎን ሲፈልጉ ጠንካራ ጎኑ መከላከያ ነው። ስለዚህ ጠንካራ ጎኑን ፣ጠንካራው ቋጠሮ መመታት አለበት ነው እሳቢያቸው ።

ይሄን ሀገር ያቆመው ፤ይሄን ሀገር በየጊዜው የሚፈጠሩ አጀንዳ እያከሸፈ ለውጡ እንዲቀጥል ያደረገው ማነው ሲባል ጠንካራው ቋጠሮ መከላከያ ነው። ስለዚህ

ወደ ገጽ 8 ዞሯል

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ

## “ማንም ይሁን ማን ከውጪ...

ከገጽ 7 የዞረ



አማራ ክልል የተደረገው ነውጥ ለአማራ ክልል በጣም አደገኛ፤ ለአማራ ማኅበረሰብ አደገኛ፤ ለኢትዮጵያም የሚጎዳ፤ ታይቶ የማይታወቅ ነገር ነው

መከላከያ ካልተመታ የፈለግነው ሀሳብ ሥራ ላይ እየዋለ አይደለም በሚል ነው የሚዘመትበት።

እኛ ደግሞ ተልእኮ አለን። ተልእኮው ከውጭም ይምጣ ከውስጥም ይምጣ በኃይል የሀገሪቷን ሥርዓተ መንግሥት ፤የሀገሪቱን ሕገ መንግሥት ገርስሶ ፤እኔ ነኝ ጉልበተኛ ብሎ በግድ በጠመንጃ ሊጭን የመጣ ኃይል ሁሉ እንዋጋለን። ይሄ የኛ ተልእኮ ነው። ማንም ይሁን ማን ከውጪ በወረራ መልክ ይምጣ ፤ተቀጥሮ ይምጣ፤ ኃይል አሰባስቦ ታጥቆ በጉልበት ይምጣ ልክ ማስገባት የኛ ሥራ ነው።

ልክ እያስገባ ስላስቸገረ የዚህ ሀገር ጠንካራ ቋጠሮ ማነው ሲባል መከላከያ ነው የተገኘው። ስለዚህ ይሄን ማፍረስ ነው ስራቸው። ለዚህ ነው መከላከያ ላይ ዘመቻ የበዛው። ‹ተበትኗል እንደዚህ ሆኗል፤ በጄነራል ተጣልተዋል፤ ጄነራል እከሌ ተቆጥቷል፤ የቁም እስረኛ ሆኗል› የሚለው ምኞት አይከለከል ፤ ምን እናድርግ።

መከላከያ በጠንካራ አለት ላይ የተገነባ ነው። እንደዚህ ፍርክስክስ የሚል አጀንዳ በመጣ ቁጥር የሚጭበረበር ፤ የሚርበተበት ተቋም አይደለም። ጠንካራ መሰረት ላይ የተገነባ በራሱ ዶክተሪን የተገነባ፤ በራሱ ዲስፕሊን የተገነባ፤ አላማውን የሚያውቅ፤ ለምን እንደሚዋጋ የሚያውቅ፤ ማንን እንደሚዋጋ የሚያውቅ፤ መንደርተኝነት የሌለው፤ ኢትዮጵያዊነት የተላበሰ እና ኢትዮጵያን የመጠበቅ ተልእኮ የወሰደ ስለሆነ ወደነፈሰበት የሚነፍስ ተቋም ግለሰብ የለውም።

ይሄ ምኞት ነው። ምኞቱ ምኞት ሆኖ ነው የሚቀረው። ስለ በመከላከያ የተወራው መአት ወሬ አለ፤ አንድም እውነትነት የለውም። መከላከያ ሠራዊት እኮ ነው የአማራን ክልል ሥርዓት እንዲይዝ ያደረገው። መከላከያ ሠራዊት እኮ ነው የሸኔን መፈንጨት ሥርዓት እንዲይዝ ያደረገው። የተጣላ ጄነራል፤ የተበተነ፣ ያኮረፈ ፣እርስ በራሱ የሚባላ ኃይል ይሄንን ሊሰራ አይችልም። ኢትዮጵያ ውስጥ ጠንካራ ተቋም ማነው ብትል መከላከያ ነው ፣ ከመከላከያ የተሻለ የለም። እንደዛ ነው መታየት ያለበት። ወደ ካምፕ ይግባ የሚል ሰሞኑን የወጣው አስቂኝ ነገር ነው።

ወደ ካምፕ ይግባ የሚል ብቻ ሳይሆን ፣ሌላው የሰማሁት ነገር፣ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ዳር ድንበር መጠበቅ ነው እንጂ በውስጥ ግጭት መግባት ስለሌለበት የውስጥ ግጭት ይቀጥል የሚል ነው። የመከላከያ ሠራዊት ተልኮ የሀገሪቷን ሉአላዊነት መጠበቅ ነው። የሚጠብቀው ደግሞ ጠረፍ አጥሮ አይደለም። ጠረፍ አጥሮ ምሽግ ሰርቶ ሰልፍ ሰርቶ እንደዛ አይደለም። መከላከያ ሠራዊት ሀገሪቷን የሚጠብቀው ራሱን እየገነባ ነው። መከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚጠብቀው እራሱን እየገነባ ነው። እየሰለጠነ ነው እየታጠቀ ነው አቅም እያበዛ ነው። እየተደራጀ ነው።

ሁለተኛው የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ከፖሊስ አቅም በላይ የሆነ እና ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን በኃይል ለመናድ የመጣ ማንኛውም የታጠቀ የሀገር ውስጥ ኃይል መቆጣጠር እንዳለበት ተልዕኮ ተሰጥቶታል። የአማራ ፅንፈኛ ትግል ከፖሊስ በላይ አይደለም ብቻ እንዳትለኝ ወይም የሸኔ ትግል ከፖሊስ በላይ አይደለም እንዳትለኝ። ፖሊስ ወንጀል ነው የሚቆጣጠረው። የፖሊስ ሥራ ወንጀል መቆጣጠር፤ወንጀለኛን መያዝ ፤ወንጀለኛን ለፍርድ ማቅረብ ነው።

የተደራጀ የታጠቀ እና ፍላጎቱን በኃይል ለማስፈፀም ታጥቆ የመጣ የሀገር ውስጥ ኃይል ፀረ ሕገመንግሥት ነው። ፀረ መንግሥት ነው። ሀገር አፍራሽ ነው። ሕገመንግሥቱ በሚለው መሰረት መከላከያ ሠራዊት ይመከተዋል፤ ያስታግሰዋል። ይህንን ተረድተው አይደለም የተናገሩት እነዛ ሰልፍ አዘጋጅ ነን ያሉ ሰዎች። የመከላከያ ተልዕኮ ካለማወቅ የመዘበራረቅ ነገር አይቼባቸዋለሁ አንድ እሱ ነው።

ሁለተኛ ከመቼ ወዲህ ነው ፖለቲከኛ ወይም በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ የሚል ቡድን ግለሰብ ፓርቲ ለመከላከያ ሠራዊት ትዕዛዝ የሚሰጠው። ካምፕ ግባ ፤ከካምፕ ውጣ ፤ይሄን ቦታ ያዝ ፤ይሄን ቦታ ልቀቅ የሚለው። የገባኝ ይሄ ኃይል የፅንፈኛው የከተማ አንጃ ነው። የፅንፈኛው የከተማ አንጃ ነው። ፅንፈኛው አከርካሪው ሲመታ ተስፋ ላለመቁረጥ በከተማ ግርግር ሊመጣ የፈለገ ኃይል ነው።

ስለዚህ እኛ ወደ ካምፕ አንገባም። ፀረ ሰላም ኃይሎችን እናስተካክላለን ፤ካስተካከልን በኋላ ወደራሳችን ሥራ እንመለሳለን ብለን ነው የምናስበው እና ትክክል አይደለም። እኔ ሰልፍ አልቃወምም። የሆነ አጀንዳ ፈጥረህ ሰላማዊ ሰልፍ ማድረግ መብት ነው። የሰሞኑ ሰላማዊ ሰልፍ ግን ነውጠኛ የጦርነት አዋጅ እንጂ ሰላማዊ ሰልፍ አይደለም።

መከላከያ ሠራዊትን ወደ ካምፕ የሚያስገባ፤ ጫካ ያለውን ፅንፈኛ የታጠቀ ኃይል ደግሞ ወደ አደባባይ የሚያወጣ ፤ወደ ከተማ የሚያስገባ ፤በሰላማዊ ሰልፍ የተደገፈ ፤ ሀገር የሚያፈርስ ነው። ስለዚህ መንግሥት መከልከሉ ትክክል ነው ብዬ አስባለሁ፤ ይሄ ሰልፍ ተከለከለ ማለት ነገ ሰልፍ አይደረግም ማለት አይደለም። ሕዝብ የሚገዛውን አጀንዳ ፈጥረህ ሰልፍ ማድረግ ትችላለህ ማለት ነው።

ለወሮበላ አምስት አምስት ሺህ ብር እየከፈልክ ከተማ ለማስበጥበጥ ሰልፍ መጥራት አይቻልም። ብሩ ደግሞ ከታሪካዊ ጠላቶቻችን ነው የሚመጣው። ይህንን የማያገናዝብ እና ሥራ ፍለጋ አዲስ አበባ ለመጣ ወጣት ብር እየከፈሉ አዲስ አበባን ለማቃጠል መሞከር ትክክል አይደለም።

ሠራዊቱን ወደ ካምፕ አስገብቶ ፍላጎቱን በኃይል ለመጫን የሚመጣውን ፅንፈኛ ሁሉንም እንዲቆጣጠር ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የሚጠራ ሰልፍ ትክክል አይደለም። ስለዚህ ካምፕም አንገባም ፤ማንም አያገባውም። የእኛን ተልዕኮ እኛ እናውቃለን። የእኛ ተልዕኮ መሰረቱ ሕገመንግሥት ነው።

ማንኛውም የታጠቀ ኃይል በአማራ ክልል፣ በኦሮሚያ ክልል፣ በሶማሌ ክልል፣ በአፋር ክልል በሌላውም ክልል እንደፈለገ ይፈንጭ የሚልና መከላከያ የውጭ ጠላት ካልመጣ በስተቀር ከካምፕ መውጣት የለበትም የሚል ሕገመንግሥቱን ቀይሮ እንደዛ ሊደርግ ይችላል። እስከዛ ግን እኛ ተልዕኳችንን ነው እየፈፀምን ያለነው።

**ጥያቄ፡- ክቡር ፊልድ ማርሻል የኢትዮጵያ ሰላም አሁን በምን ደረጃ ይገኛል? እንደ ሀገር የመከላከያ ሠራዊቱስ የሀገርን ደህንነት በመጠበቅ ረገድ አሁን የሚገኝበት የዝግጁነት ደረጃ ምን ይመስላል?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ፡-** ያው እንደሚታወቀው ቀደም ሲል ሰሜን ዕዝ ከተመታ በኋላ ጦርነት ውስጥ ነበርን፤ ያጦርነት ቀላል ጦርነት አይደለም፤ ከባድ ጦርነት ነው። ሁለቱ ዓመታት ሀገሪቷ ከባድ የፀጥታ ችግር የገጠማት ጊዜ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን ደግሞ ሸኔ በዚህ ግርግር ለመጠቀም ከፍተኛ ርብርብ አድርጓል። ሰሜኑ የአፋር፣ የአማራ ክልል በከፊል ትግራይ ሙሉ በሙሉ፣ ምዕራብ ኦሮሚያ፣ ቤንሻንጉል ጉሙዝ፣ ጋምቤላ ሰፋ ያለ የጸጥታ ችግር ነበር።ቤንሻንጉል ላይ ህዳሴ ግድብ ለመስራት አስቸጋሪ እስከሚሆን ድረስ የደረሰ የፀጥታ ችግር ነበር፣ የትግራይ ያው እንደሚታወቀው ነው። አሁን ግን በከፍተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ የፀጥታ ሁኔታ ተሻሽሏል።

በትግራይ ጦርነቱ ተካሂዶ ጦርነት እንደማያዋጣ ሲታወቅ ወደ ድርድር መጥቶ በሰላም ተፈትቷል፤ አሁን ትግራይን መልሶ የማቋቋምና የቀረው (የDDR ) ፕሮግራም ሥራ ላይ እንዲውል የመስራት ሥራ ነው። ሁለተኛ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ፀጥታ መቶ በመቶ ተስተካክሏል። እዛ ያለው ጠላት በከፍተኛ ደረጃ ተመትቶ የተረፈው ኃይል በሰላም እንዲገባ ተደርጓል። ቤኔን የሚባል ኃይል ቤንሻንጉል ላይ ነበር እሱም በሰላም እንዲገባ ተደርጓል።

ከብዙ መንገራገጭ በኋላ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ሞክረው ሲያቅታቸው ነው ወደ ሰላም የተመለሱት። የጋምቤላ ነፃ አውጪ የሚባለውም በተመሳሳይ በሰላም እታገላለሁ ብሎ ምህረት ተደርጎለት ገብቷል። የአማራ ጽንፈኛ ደብረማርቆስ፤ ጎንደር ፤ደሴ ፤ኮምቦልቻ ለመቆጣጠር ከመፈለግ አልፎ ባህርዳርን የመቆጣጠር ፍላጎት ነበረው። በዚህም ጠቅላላ የአማራ ክልልን መዋቅር “ፓላራይዝ” ለማድረግ ሙሉ በሙሉ በመቆጣጠር የሽፍታ ክልል ማድረግ እና አልፎም ወደፌዴራል አፈሙዝ ማዞር የሚል የጅል እቅድ አውጥቶ ነበር ።

እሱ አሁን አከርካሪው ተመትቷል። ወደመደበቅ፤ ወደሸጥ ፤ወደዋሻ፤ ወደአባይ ለመደበቅ ወርዷል። በአሁኑ ወቅትም ሰው ወደማይኖርባቸው፤መሰረተ ልማት ወዳልገባባቸው ቦታዎች ወርዷል። አብዛኛው ቦታ ላይ የሰላሙ ሁኔታ እየተረጋገጠ ይገኛል። ሕዝቡም ሥራ ጀምሯል። በመሆኑም አማራ ክልል በከፍተኛ ሁኔታ ተቀይሯል።

ኦሮሚያ ክልል ልክ እንደ አማራ ክልሉ ተመሳሳይ ነው። ሸኔ የታንዛኒያ ድርድር ላይ እያለ ድርድሩን መንግሥት ተገዶ እንዲቀበል ያለ የሌለ ኃይላችንን አውጥተን መንግሥትን እናስጨንቀው የሚል የሞኝ ፖለቲካዊ ስትራቴጂ ነድፎ ሠራዊቱን በሙሉ አውጥቶ ከመከላከያ ጋር አጋጨውና ብዙ ዓመት የደከመበት ኃይሉ እንዲመታ ሆኗል። በማሰልጠን፤ በማዘጋጀትና በማለማመድ ብዙ ኃይል ተመትቷል። አሁን ምዕራብም ቢሆን በተነጻጻሪ ጥሩ እንቅስቃሴ ያለበት ነው።

ወታደራዊ ጥበብ እኮ መጀመሪያ እራስህን ትገመግማለህ ፤ከዚያ ጠላትህን ትገመግማለህ። በዚህም የውጊያ ጥንካሬውን ፤ትጥቁን ብዛቱን፤ አደረጃጀቱን ችሎታውን ደካማ ጎኑ ይገመገማል ።ከዚያ በኋላ የውጊያ እቅድ ይወጣል እንጂ ጠመንጃ ስለተያዘ ብቻ እቅድ አይወጣም። የፊልም ተዋናዮችን አለባበስ ለብሶ ስለተንጎራደደ ጦርነት አይከፈትም፤ ውጊያም አይደረግም። ቢያንስ እቅምን ገንብቶና ስትራቴጂ ነድፎ መዘጋጀት ያስፈልጋል። ከዛም አቅም ፈጥሬያለሁ፤ መገዳደር እችላለሁ የሚለው አቋም ላይ ሲደረስ ነው ጦርነት የሚገጠመው።

አሁን ላይ ግማሹ ቆመህ ጠብቀኝ የያዘ ሌላው ክላሽንኮፍና ብሬን የያዘ በጣም አልፎ አልፎ ድሽቃ የያዘ መንግሥትን አስገድጄ የሰላም ድርድሩን እንዲቀበል አደርጋለሁ ብሎ ዘመቻ ይከፈታል? ይህ ሁኔታ ደግሞ በህይወቱ ተሙቶ በማያቀው ልክ በመመታቱ ለማንሰራራት ብዙ ጊዜ እንዲወስድ አስገድዶታል። አሁን ተስፋ ስለቆረጡ ከተሞች ላይ ቦምብ ወደመጣል፤ ግለሰቦችን ወደመግደል ተሸጋግረዋል።በነገራችን ላይ አማራ ክልል ያለውም ይኸው ነው።

ወደ ገጽ 9 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ማንም ይሁን ማን ከውጪ...

ከገጽ 8 የዞረ



**ማንም ይሁን ማን ከውጪ በወረራ መልክ ይምጣ፤ተቀጥሮ ይምጣ፤ ኃይል አሰባስቦ ታጥቆ በጉልበት ይምጣ ልክ ማስገባት የኛ ሥራ ነው**

እኛ እንደ ፖለቲከኛ ቀን በቀን እየወጣን ለሕዝቡ ስለማንናገር ነው እንጂ መከላከያ ሠራዊት የሀገሩን ሰላምና ጸጥታ ለማስከበር በጣም እየሰራና እየለፋ ነው። ኢትዮጵያ ጥሩ ”አክቲቪስቶች” አሏት ፤ጥሩ ዜጎችም አሏት፤ ምናልባትም አብዛኛው ኃይል በዚህ ነው የሚገለጸው። ኢትዮጵያ መሰሪ አደገኛ የሆኑ ተኝተው የማያድሩ ከስልጣን በስተቀር ሌላ ሥራና አላማ የሌላቸው ማንም የሚቀጥራቸው ኤሊቶችና አክቲቪስቶችም አሏት። ሕዝቡን እግዚአብሔር ከእነዚህ ሰዎች ይሰውረው።

የአማራ የኦሮሞ የትግራይ የሶማሌ ጽንፈኛ ሁሉም ተፈለፈለ ከዚያም ተዋጋ ።ቀጥሎም መንግሥት ፈረሰ እንበል፤ ከዛስ ምን ሊያደርጉ ነው? ይህ የማያቋርጥ ሊድን የማይችል የእርስ በእርስ እልቂት አይፈጥርም? ሽምግልና የማያስተካክለው ቁርሾ አይሆንም ? ስለዚህ የየጎጡን ጽንፈኛ በማጀገን መንግሥትን ለመጣል ብቻ እንጂ ከዛስ የሚለውን ነገር ግን አልታሰበም።

ብዙ ተምሬያለሁ የሚል ነገር ግን የማያስብ ሀገሪቱን ወደጨለማ የሚነዳ ኤሊት ፖለቲከኛና አክቲቪስት ነው ያለው። እውነት ለመናገር ብዙ ፖለቲከኞች ፖለቲከኞች ናቸው ወይ ? የሚል ጥያቄ እንድታነሳ ያስገድዳሉ። እየሆነ ያለው ምንድን ነው አላማው? ምንድን ነው የሚፈልገው? እንዴት ነው የፈለገውን ማሳካት የሚፈልገው ?የሚለውን ለማወቅ አያስችልም። ይህ ደግሞ ስሜታዊ ለቀን ለቀኑ ብቻ የሚያስብ ፤ በጉርሻ የሚሰራ ፤ ሲያጎርሱት በደንብ የሚያጣላ ፤ጉርሻ ሲያጣ ዝም የሚል እየበዛ ነው።

እኛ በመረጃ የምናውቃቸው ደመወዝ ተከፍሏቸው ፀረ ኢትዮጵያ የሚሰሩ ምሁራን አሉ።ደመወዝ የሚከፍላቸው ኃይል አላማ አለው። እሱ ግን ደመወዙን ነው የሚያየው።ከዚያ በል የተባለውን ነው የሚለው። ፃፍ የተባለውን ነው የሚጽፈው። አንዳንዱ ነገር አሳፋሪ ነው፤ ወደ ሚዲያ አውጥቶ ለመናገር። እንዲህ ያለውን ኃይል መቼ ነው የፈጠርነው ፤እንዴት ነው የፈጠርነው። የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ምንድነው የሆነው። ምንድነው የገጠመው ብዬ እንዳስብ ያደርገኛል።

የሌላ ሀገር ዲያስፖራ ቴክኖሎጂ እየቀዳ ወደ ሀገሩ ይልካል።ዶላር ወደ ሀገሩ ይልካል።የራሱን ሕዝብና መንግሥት በየሄደበትና በየደረሰበት አያብጠለጥልም።ከተርኪና ከቻይና በላይ ስደተኛ ዲያስፖራ ያለው የለም። ቱርኮች ሀገራቸውን ገናና ያደረጉት ዲያስፖራዎች ናቸው። ከውጭ የሚያገኙትን ገንዘብ ሆነ ብለው ሰብስበው አጠራቅመው ይልካሉ።በየሁለት ወሩ ስቴትስ ዲፓርትመንት በር ላይ አይታዩም።

የኛው ዲያስፖራ ግን ሀገሩን ለማጥፋት የተሰለፈ ይመስላል። እዚህ ውስጥ የሌሉ ሬሚታንስ፣ቴክኖሎጂ ወደ ሀገር የሚልኩ ብር አጠራቅመው ኢትጵያ የተቸገረችበትን ነገር የሚከፍቱ፤የሚሰሩ አሉ። እነዚህ ሰዎች ሥርዓት ያላቸው፣በሥርዓት ያደጉ፣ሥራ የሚሰሩ፣ጨኸት ቦታ የማይውሉ፣ገንዘብ በደንብ የሚያገኙ ትምህርት እዛ የተማሩ፣እውቀት ያካበቱ ናቸው።

በኢንዱስትሪ የሚሰሩ መአት ናቸው።ትላልቅ ፎቅ የሚሰሩ፣ህክምና የሚያመጡም አሉ።ለመከላከያ የሚረዱ አሉ።ግብርና የገቡ አሉ።ለሀገራችን ኢኮኖሚ ህይወት የዘሩ አሉ። ስቴት ዲፓርትመነት በር ላይ አታገኛቸውም። እነዚህ ምርጥ የኢትዮጵያ ዜጎች ናቸው።

ፀረ ኢትዮጵያ ሆነው የሚሰሩ ምሁራን አሉ። የወሬ ገበያ/ ማርኬት ተፈጥሯል። ይሄ የወሬ ማርኬት ኢትዮጵያን እያፈረሳት ነው። ኢትዮጵያን እየጎዳት ነው። የሕዝብ ትስስርን እያላላ ነው። የሕዝብ መተማመንን እየሸረሸረ ነው። ምክር ፣ተስፋ ኤክስፒሪያንስ ነው እንጂ መስጠት የሚገባው ተባላ፣ተጋደል እከሌን አጥፋ ፣አራት ኪሎ ግባ፣የአባትህ ቤተመንግሥት እንዲዚህ አይባልም።እነዚህ ኢትዮጵያን እየጎዱ ነው።

እኛ ግን ማንም እንደዚያ ያድርግ ፣ማንም ይሞክር እስትንፋሳችን እስካለ ድረስ እንታገላለን።ኢትዮጵያ ትሻገራለች ብዬ አስባለሁ። ጥሩ እየሄድን ነው። እብደቱም እየቀነሰ ነው።ሀገሪቱ ምክክርም ይኖራታል ብዬ አስባለሁ እና ትሻገራለች። ሀብት አላት፣ሀብቱን አውጥተን መክበር አቅቶን 60 ዓመት ሙሉ ስለተኩስ ነው እያወራን የኖርነው። ለመተኮስ፣በጉልበት ስለመቆጣጠር፣ሌላውን ስለማፈን ስናስብ ነው የኖርነው። የኢትዮጵያ ሕዝብ ይሄን በደንብ መረዳት አለበት ብዬ አስባለሁ።

**ጥያቄ -አልሻባብ የመከላከያ ሠራዊት ግዳጅ ውስጥ ነው ብሎ ባሰበበት ወቅት የተለያዩ ጥፋቶችን ለመስራት ይሞክራል፤በዚህ ላይ ምን ይላሉ ?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ፦** አልሸባብ እንደምታስቡት አይደለም።አቅም የለውም። አንደኛ እኛ በሙሉ አቅም አይደለም የገባነው። ወደ አማራ ክልል ኦሮሚያ ክልል ያለውን ኃይል ለመቆጣጠር የገባነው በውስን ኃይል ነው። እኛ እዚህ ተጠምደን፣ኃይል አንሶን አልሸባብ እኛን የሚሞክርበት አጋጣሚ/ ፖሲቢሊቲ የለውም። አንደኛው ይሄ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ የኢትዮጵያ ሠራዊት ሌላው ጋር ይከበራል።

የእኛው ስድአደግ ጋር ነው እንጂ የሚብጠለጠለው ሌላው ግን ክብር አለው። ወጣ ብለንም እንዴት ነው የሚያዩን ብለን እንትን እንሰራለን እኮ ፣ታንዛኒያ ነበርኩ። ለእኛ ሠራዊት ያላቸው ክብር፣ምን አለበት እንዲዚህ አይነት ሠራዊት ቢኖረን የሚሉ ናቸው።ሁሉም ያውቃል። አውሮፓ አሜሪካንም ስለእኛ ሠራዊት ያውቃል። ባለፈው በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አማራ ክልል ስንገባ፣የአማራ ሕዝብ ሠራዊታችንን እንዴት እንደተቀበለውና እንዳስተናገደው እናውቃለን። ሕዝቡ ነፍስ አድን እንደመጣለት ነው ያሰበው።

እዚህ ላይ ማንሳት የምፈልገው / ባይዘዌይ/ እዛ አካባቢ የተሰራው የፀጥታ ሥራ የሕዝቡም ሚና ነው። ሁሉ ቦታ እንደዚያ ነው ይምጣልኝ ነው የሚለው። በአማራ ክልል ውስጥ የእኛ ሠራዊት ያለበትና የሌለበት ቦታ አለ። የሌለበት ቦታ ያሉት ጽንፈኛው እንዳይቆጣቸው ተደራጅተው ሌሊት መጥተው እረባካችሁ ለእኛም ሠራዊት መድቡልን ይላሉ። ማን የእነሱን ደህንነትና ፀጥታ ጠብቆ እዚህ እንዳደረሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል።

ሠራዊቱን እንደ ዋስትና ነው የሚያየው።የኢትዮጵያን ሠራዊት እንደዋስትና የማያዩ ኢትዮጵያውያን ካሉ ንቅል ናቸው፤ ስድአደግ ናቸው፤ እንደገና ደግሞ ቅጥረኛ ናቸው። የእኛ ሠራዊት የተከበረ ነው። ለእኛም ሠራዊት መድቡልን ይላሉ። ማን የእርሱን ደህንነትና ጸጥታውን ጠብቆ እዚህ እንዳደረሰው የኢትዮጵያ ሕዝብ ያውቃል።

**የትም ስፍራ ብትሔድ የተከበረ ነው። ዩናይትድ ኔሽን ቢኬድ የተከበረ ነው። አሜሪካ ብትሔድ የተከበረ ነው፤ አረብ ሀገር ብትሔድ የተከበረ ነው። በአፍሪካ በሙሉ ብትሔድ የተከበረ ነው።**

እንዴት ነው የምትገነቡት? ብለውም እየጠየቁን ነው። ይህ ተቋምም ሆነ ወታደር ብርቅዬ የኢትዮጵያ ሀብት ነው። እናም እኛ ሀገር በዚህ አራትና አምስት ዓመት ያጋጠመን አይነት ውጥንቅጥ፣ ችግር፣ እርስ በእርስ መገፋፋት፣ እርስ በእርስ መናናቅ፣ ኹከት፣ ግርግር፣ በአቋራጭ ስልጣን ለመያዝ ምክንያት ተደርጎ የተፈጠሩ ግጭቶች በሙሉ እያንዳንዱን እንደየአመጣጡ አምክኖ እዚህ ያደረሰው የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ነው።

እንደዚህ የምለው እኔ የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት አዛዥ ስለሆንኩ አይደለም። መሬት ላይ ያለው ሐቅ እሱ ነው፤ እሱን መቀበል ነው። ተወው፤ ስለእኛ ምንም አይንገረን። ተበተኑ፤ ተጣሉ ለሚለው ነገር ጆሮ አንሰጥም። ይልቁኑ እኛ የሚመጣው ዘመን የቴክኖሎጂ ነው፤ ሀገራችን ያድጋል፤ ሕዝባችን ይበዛል። ጠላት ሊበዛ ይችላል። ስለዚህ የዛሬ 15 እና 20 ዓመት ማድረግ ያለብን ምንድን ነው በሚለው ላይ ነው ራሳችንን ያስጨነቅነው ፣ ማንም መንገደኛ የሚያወራው ወሬ ስሜት አይሰጠንም። ልካችንን፣ ቦታችንና ችሎታችንን እናውቃለን።

እንደ ኢትዮጵያ አይነት ሠራዊት አሁን ዓለም ላይ አለ ብዬ አላምንም። ብዙ ሚሳዔል፣ ብዙ ጄት፣ ብዙ ትጥቅ፣ ብዙ ደመወዝ የሚከፈለው ወታደር ሊኖር ይችላል። የኢትዮጵያ አይነት ግን ተልዕኮውን በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ መፈጸም የሚችል ፤ ችግር ተቋቁሞ፣ ሀገሩን አስቀድሞ፣ ራሱን አርክሶ የሚሰራ የለም። እኛ ሠራዊታችንን የምንገመግመውና የምንለካው እንደዚህ ነው። እንደገና ደግሞ ሁልጊዜ ስለ ሠራዊታችን ውስጣዊ ሁኔታ እያየን፣ እያስተካከልን፣ እየገነባን፣ እያጠናከርን ስለምንሔድ እነዚህ ሰዎች ሲያምራችሁ ይቅር መባል አለባቸው።

አልሸባብ የኢትዮጵያ ስጋት አይደለም። እንደገና እኛ በጣም ተወጥረን ፣ በጣም ተለጥጠን፣ እንዲያው አቅም አንሶን፣ እዚህ ተጠምደን ሌላው የሚገባብን ሀገር አይደለም። መስጋት አይገባም።

**ጥያቄ ፦ እርስዎን ጨምሮ ሌሎችም ከፍተኛ የጦር መኮንኖች የወታደራዊ ዲፕሎማሲ ጉዞ ላይ ነበራችሁ። የእነዚያ ጉዞዎች ዓላማ ምንድን ነው? የተገኘውስ ውጤት ምን ይመስላል?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ :** - ምን መሰለህ? ቅድም እንዳልኩህ ነው። የኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት በዓለም ላይ በጣም ተፈላጊ ሆኗል። ሰው እኛ ዘንድ ወታደር ማሰልጠን ይፈልጋል። ኦፊሰር ማሰልጠን ይፈልጋል፤ ፓይለት ማሰልጠን ይፈልጋል፤ ከባድ መሳሪያ ምድብተኛ ማሰልጠን ይፈልጋል። የእኛ ሠራዊት የግንባታ እሴት ይፈልጋል።

ከዚህ የተነሳ እኛን ይጋብዙናል ፤ባላቸው ይደግፉናል።

የአንተን ወዳጅነት ፈልጎ፣ ከግማሽ በላይ ሔዶ ሲጠራህ አቤት የማትል ከሆነ ራስህ አትሸጥም ማለት ነው። እኔ በአሁኑ ወቅት እኛ ዘንድ ና፣ እኛም ዘንድ ና፣ ከእኛም ጋር እንነጋገር፣ ከእኛም ጋር እንደራደር፣ ከእኛም ጋር እንፈራረም የሚል ጥሪ በዝቶብኝ ተቸግሬያለሁ። ቁጥር ስፍር የለውም።

ለምንድን ነው? ቢባል ኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ጋር ያለ ነገር ወደእነርሱ እንዲተላለፍ ይፈልጋሉ። ስለዚህ ይጋብዙናል። የታንዛኒያ ጥሪ የተደረገልኝ መስከረም ወር ላይ ነው። አልችልም እያልኩና እያራዘምኩ ሁለቴ ደብዳቤ ጽፈን አራዝመናል። ስናራዝም ቆይተን ባለፈው

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

## “ማንም ይሁን ማን ከውጪ...

ከገጽ 9 የዞረ

ጊዜ ሲመቸን ሔደናል። ሔደንም ጥሩ ስምምነት አድርገናል።

ጥሩ የመተባበር፣ ልምድ የመቀሳሰም እና የመቀያየር፣ የስልጠና ፣ የጥገና ስምምነት አድርገናል። ይበልጥ እነርሱ ከእኛ ይፈልጋሉ። ታንዛኒያ ደግሞ ለኢትዮጵያ በጣም ክብር ያላት ፣ ኢትዮጵያን የምትወድ ሀገር ናት ። ሕዝቡም አመራሩም። ታሪካዊ ነገርም አለው። አቀባበላቸውም ግሩም ነበር። እንደዛ የሚቀበሉት ቺፍ ኦፍ ስታፍ የለም።

እኛ በአሁኑ ጊዜ በጣም ተፈላጊ ነን። መካከለኛው ምሥራቅ ያሉ ሀገሮች ድሮ ከእነርሱ የሚወሰድ ነገር ይኖራል የሚል አተያይ የላቸውም። በአሁኑ ወቅት ግን በወረፋ ማስተናገድ ነው ያቃተን። ሚሊታሪ ዲፕሎማሲው እኛ ከተዘጋጀንበት በላይ ሆነ። ሚሊታሪ ዲፕሎማሲው የሀገር ገጽታ ለመገንባት ያግዛል።

ታሪካችንን ለማሳወቅ፣ ወዳጅ ለማብዛት፣ በዓለም አቀፍ መድረኮች ላይ ከኛ ጋር እንዲቆሙ ለማድረግ ያግዛል። የማትተዋወቅ ከሆነ ዓለም አቀፍ መድረክም ስትሄድ ወዳንተ ጫና ቢመጣ የት ያውቅሀል። ለሚያውቀው ነው እጅ የሚያነሳው። እንዲያውም ብዙ አልሰራንም። እኛ በምንፈልገው ልክ ገና አልሰራንም።

የታንዛኒያ ጉብኝት በጣም ፍሬያማ ነበር። ጥሩ ሥራ ሠርተን ተመልሰናል። እንዲያውም እነርሱ እዚያ እንድንቆይ የፈለጉት ለአስር ቀናት ነበር። እኛ ለአራት ቀናት እንዲያደርጉልን ጠይቀን ነው የመጣነው። ሀገሪቱ እያደገች ፣ ተስፋ ያላት ሀገር እየሆነች ነው። ከእንደዚህ አይነት ተስፋ ካለው ሀገር ጋር መተሳሰር ጥሩ ነው።

ተስፋ ከሌለው ሀገር ጋር መተሳሰር ሊጎዳህ ይችላል። ተስፋ ካለው፣ አንተን ከሚፈልግህ፣ ካንተ የሆነ ነገር አገኛለሁ ብሎ ከሚያስብ፣ ለአንተ እውቅና ሰጥቶ ከሚያስብ ሀገር ጋር የሚሊታሪ ዲፕሎማሲ ማድረግ በጣም ያስፈልጋል፤ ይሄ ደግሞ ለሚሊታሪው ብቻ አይደለም ፤ ለሀገሪቱ በሙሉ የሚጠቅም ነገር ያስገኛል።

አሁን እኛ የገባን ምንድነው፤ አንደኛ ራሳችንን እናውቃለን ፤ ሁለተኛ ብዙ ሀገሮች የኛ ወዳጅ መሆን ፣ ከኛ መማር እንደሚፈልጉ ፣ እነርሱ ጋ እኛ ያላወቅነው የሆነ ነገር እንዳለ ተረድተናል።

**ጥያቄ ፦ ይህን ቃለ ምልልስ እያደረግን ያለነው የኢትዮጵያን የአየር ክልል በሚያስጠብቀው በኢፌዲሪ አየር ኃይል ጠቅላይ መምሪያ ግቢ ውስጥ ነው። እርስዎ እዚህ ግቢ የተገኙበትን አጋጣሚ ምንድን ነው ?**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ፦** ባለፈው የ116 ኛውን የመከላከያ ሠራዊት በዓል ለመጀመሪያ ጊዜ አክብረናል። የኢትዮጵያ ሠራዊት በዚህን ቀን ነው የተመሰረተው፣ የሠራዊቱ እድሜ አሁን 116 ዓመት ደርሷል። ኢትዮጵያ አሁን ተጠፍጥፋ የተሰራች ወይም ኢህአዴግ ጠፍጥፎ የሰራት ሀገር አይደለችም፤ ታሪክ ያላት ሀገር ናት። ሠራዊቱም የተመሰረተበት፣ የጀመረበት ታሪክ አለው።

ሠራዊቱ ከትውልድ እየተወራረሰ የመጣ እሴት ፣ አርበኝነት ያለው ነው ፣ በዚህን ጊዜ የተመሰረተ፣ እየቀጠለ የመጣ፣ ሀገርን እየተከላከለ እዚህ ያደረሰ፣ አባቶቻችን ዋጋ የከፈሉበት ሠራዊት ነው ።ይህን አስተሳሰብ ይዘን፣ ሪፎርም ሰርተን 116ተኛ ዓመቱን ለመጀመሪያ ጊዜ አክብረናል።

በኢህአዴግ ዘመን አዲስ ሕገመንግሥት መጣ። የሠራዊቱም ቀን ሕገመንግሥቱ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ነው መከበር ያለበት ተብሎ ሰባት ዓመት በተከታታይነት በተለያየ መንገድ ሲከበር ነበር። እሱ ልክ አይደለም፤ እሱ ሀገር አይወክልም። የኢትዮጵያ ሠራዊት በ1987 ዓ.ም አይደለም የመጣው።

ከዚያ በፊት የነበረው የኢትዮጵያ ሠራዊት ድክመት ሊኖረው ይችላል። ግን ደግሞ ጥንካሬም አለው፤ ሀገር ጠብቋል፤ ሀገር አቆይቷል፤ እኔ ጋ አድርሷል። አባቴ እኮ ነው እዛ ያለው። አባቴ አያቴ ... ነው እዛ ያለው። ይሄ መታየት አለበት። ይሄ ሀገር ነው፤ ታሪክ አለው፣ ሠራዊት አለው።

የእኛ ሠራዊት ሲፈጠር ዓለም በቅኝ ግዛት ስር ነበር። ያን ጊዜ ከቅኝ ግዛት ነጻ የነበሩ ሀገሮች ናቸው እንጂ ሠራዊት የገነቡት፤ ቅኝ ግዛት ስር የነበሩ ሀገሮች ሠራዊት አልነበረባቸውም። በጣም የተወሰኑ ሀገሮች ናቸው ሠራዊት የነበራቸው። ከዚያ ከተወሰኑ ሀገሮች መሀል አንዷ ኢትዮጵያ ናት። ስለዚህ ይሄ የሠራዊት ግንባታ ሪፎርም ነው።

የአንተ አባት አርበኛ ነው። ኢትዮጵያውያን



አርበኞች ናቸው። አንተ የአርበኛ ልጅ ነህ። ሀገርህን ጠብቅ ፣በአርበኝነት ለልጅህ አስረክብ ልለው ከሆነ ታሪክ መኖር አለበት። ታሪኩ ደግሞ አለ። ታሪኩን ኢግኖር አድርጌ /አላየሁም አልሰማሁም ብዬ/ መሄድ የለብኝም። የመጣ ሁሉ የተገነባውን የሚያፈርስ ከሆነ ልክ አይደለም። ስለዚህ ያከበርነው በዛ ምክንያት ነው። እሱን እንቀጥልበታለን።

መከላከያ ማለት ምን ማለት እንደሆነ ብዙ ሰው አይረዳውም። መከላከያ አራት ኃይሎች አሉት። አንዱ አየር ኃይል ነው። አንዱም ምድር ኃይል ነው። አንዱ ባህር ኃይል ነው ፤ አንዱ የሳይበር ኃይል ነው። ምናልባት ምድር ኃይሉ ደግሞ የተለያየ ነው። ሜካናይዝ ነው፤ ስፔሻል ፎርስ/ ልዩ ኃይል/ ነው፤ ኮማንዶ ነው። እግረኛ ነው፤ ወዘተ.። ኃይሎቹ እንደዛ ናቸው።

አየር ኃይል የመከላከያ አንድ ኃይል ነው። ስለዚህ አየር ኃይልም ታሪክ አለው። ምድር ኃይልም ታሪክ አለው። ባህር ኃይልም ታሪክ አለው። ስለዚህ የመከላከያ ቀንን ካከበርን በኋላ ቶሎ የምስረታ ቀኑ የደረሰው አየር ኃይል ነው። አየር ኃይል ከተመሰረተ ዘንድሮ 88ኛ ዓመቱ ነው። ይህ 88 ዓመት ተከብሮ አያውቅም። ድሮ በንጉሱ ጊዜ ኤይር ፎርስ ዴይ /የአየር ኃይል ቀን / ተብሎ ስለመከበሩ አላውቅም ፤ በዚህ ላይ ብዙ ሰነድ አላገኘንም። ነገር ግን አየር ኃይል የተመሰረተበት ጊዜ ይታወቃል። ታሪክ ፤ሰነድ አለ።

በዚህ መሰረት ለመጀመሪያ ጊዜ በደማቅ ሁኔታ አየር ኃይል የልደት በዓሉን የአየር ኃይል ቀን የሚያከብርበት ቀን ስለደረሰ ለዛ በዓል እየተዘጋጀን ነው። የበዓሉ ዝግጅት የት ደረሰ? በሚለው ላይ ከአየር ኃይል አመራሮች ጋር ለመነጋገርና ዝግጅቱንም ለማየት ነው በአጋጣሚ እዚህ የመጣሁት። ቅዳሜ ነው በዓሉ፤ እናንተም ተገኙ።

**ጥያቄ፦ለአንባቢዎቻችን የሚያስተላልፉት ተጨማሪ መልእክት ካለ**

**ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ ፦** ኢትዮጵያ ብዙ ጠላቶች አሏት። ኢትዮጵያ እንዳታድግ የሚፈልጉ አሉ። ኢትዮጵያ ደግሞ የማደግ ዕድሏ በጣም ከፍተኛ ነው። አሁን ትምህርት እየተስፋፋ ነው። የወጣት ሀገር ናት። ብዙ ሀብት ያላት ሀገር ናት። ከመሬት ያልወጣ ሀብት አላት፤ ይህ ሀብት ሁለገብ /ብዙ አይነት/ ነው፤ አንዳንድ ሀገሮች በማዕድን ብቻ፣ ወይ በእርሻ ብቻ፣ ወይ በኢንዱስትሪ ብቻ፣ ወይ በቱሪዝም ብቻ ሀብት የሚኖሩበት ሁኔታ አለ። እንደዛ አይነት ሀገራት አሉ።

የእኛ ሀገር ግን ሁሉም አላት። በቱሪዝም ብትለው ተመራጭ ናት። ግብርና ብትለው የሚገርም ነው። የውሃ ማማ ናት። የመሬት ጥበት የለባትም። ማዕድንን እግዚአብሔር ሰብስቦ ያስቀመጠባት ትመስላለች።

ይህ ሁኔታ ባለበት ሁሉም ብድግ ብሎ ስልጣን ላይ ጉብ ማለት ይፈልጋል። ከዛ መዝረፍ፤ ሀገር ለማልማት እኮ አይደለም ለመዝረፍ ነው። ኢህአዴግ ያን ሁሉ የጦርነት መከራ አልፎ መጣና ስልጣን ያዘ። በኋላ ምን አደረገ? ሀገሪቱን መዝረፍ ብቻ ሳይሆን አጠባት። ደርግም መጣ፤ እሱስ ምን አደረገ? ከአንዱ ቀውስ ወደ አንዱ ቀውስ ሆነ፤

ፈረንጆች እኮ ታዝበውናል። ይሄ ሕዝብ በቃ የራሱን መንግሥት ከመቃወም ውጪ ሌላ ሙያ የለውም እንዴ ተብለናል፤ ፈረንጆቹኮ ሲያገኙን እንደዛ ነው የሚሉን። ሁል ጊዜ፤ መቼ ነው ይህን አቁመን ዓለም የደረሰበት የምንደርሰው?

እኛ 60 ዓመት ስንዋጋ፣ 60 ዓመት የሚበላው የሌለው ሀገር ዛሬ የት እንደደረሰ አይተናል። የዛሬ 60 ዓመት ኢምሬት የምትባለዋን ሀገር ታሪክ ሰምታችሁ ከሆነ ኢትዮጵያ እርዳታ ትሰጣት ነበር። አሁን ዓለም የሚራኮትበት ሀገር ሆናለች። ይህን 50/ 60 ዓመት እነርሱ እየተጣሉ አይደለም ያሳለፉት፤ እያለሙ፤አዳዲስ ነገር እየፈጠሩ፣ ራሳቸው ብቻ ሳይሆን የዓለም ሕዝብ እንዲያከብራቸው እንዲነግድባቸው ነው ያደረጉት። ግጭት አልነበረም፤ ይሄው አመለጡ።

ቻይና ምንድነው የነበረችው? አሁን ወደዬት ነው እየተንደረደረች ያለችው? እነ ሲንጋፖር፣ እነ ቬትናም ምንድነው የነበሩት? አንዳንዴ የእኛ ሕዝብ ስለምንድነው የሚያስበው ስል አስባለሁ፤ ብቻዬን የሆኑ ሰዎችን አመለካከት ጠባይ እና የመሳሳሉትን አይና ምንድነው እኛን የነካን የሚል ነገር ይሰማኛል።

ምንድነው ይሄ የግጭት አስተሳሰብ የወረረው ማህበረሰብ ? ስለብልጽግና የማያስብ፣ ስለፈጠራ የማያስብ፣ ከሌላው ወደ ኋላ በመቅረቱ የማይናደድና የማይጸጸተው፣ ጫማ የሌላቸውን ዘመዶቹን ገጠር አስቀምጦ እሱኑ እንደገና ወደ ግጭት ለማስገባት የሚሰራው የሚል ነገር ይሰማኛል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ማሰብ መጀመር አለበት። ቆይ እሺ፤ ኃይለስላሴ መጥፎ ሆኑ፤ ቀየርናቸው፤ ደርግ መጣ፤ ፋታ አልሰጠነውም ፤ቀየርነው። ኢህአዴግ መጣ ፤ፋታ አልሰጠነውም፤ ቀየርነው። አሁን ሌላ አዲስ መንግሥት መጣ፤ እንዲያውም ሦስት ዓመት ሳይሰራ ገና በመጀመሪያው ዓመት ለመቀየር ሠራን፤ ይሄው አሁንም እንዋጋለን።

ይህንንም ከቀየርን በኋላ እርግጠኛ ነኝ እንዋጋለን። ተሳክቶ ይህንን መንግሥት ከቀየርነው ሌላም ቢመጣ እንዋጋለን፤ አትጠራጠር። ይሄ ባህሪያችን ሆኗል። የሦስት ሺ ዓመት ታሪክ አለን እንላለን። የሦስት ሺ ዓመት ቀርቶ የ50 ዓመት ታሪክ ያለንም አንመስልም፤ በ50 ዓመት እኮ ነው የተባበሩት ኢሜሬት የተከበረ፣ የበለጸገ የለም ሀገር የሆነችው። ዓመት መቁጠር ምን ይጠቅመናል? እንደ እድሜያችን እኛ እኮ የዓለም መሪ ነው መሆን የነበረብን።

መቀየር ነው በቃ። ቴዎድሮስ መጣ፤ ያልዘመተበት የለም። ዘመነ መሳፍንት ብለን ስንት መቶ ዓመት በጨለማ ስንዋጋ ኖርን። ሁልጊዜ ጦርነት ነው። ኧረ ይብቃ።

እኔ ወታደር ነኝ ፤የሠራዊት አዛዥ ነኝ። በፍጹም ጦርነት አልፈልግም። ምክንያቱም ጦርነት ውስጥ እኔ የማዛቸው ወታደሮቼ ይቆስላሉ፤ ይሞታሉ፤ ይህ ይሰማኛል።

ሀገሬ ሰላም እንድትሆን ሁሉም ሰርቶ እንዲኖር እፈልጋለሁ። ከመጣ ግን የግድ ነው። ሀገር እስኪፈርስ እኔ ቁጭ ብዬ ማየት አልችልም። ግን መቆም አለበት። የደም ነጋዴዎችን የኢትዮጵያ ሕዝብ መቀበል የለበትም፤ መነዳት የለበትም፤ መንጋ መሆን የለበትም። እነሱን እያደፋፈረ ያለው እሱ ነው። ተከታይ ቢያጡ አለቀላቸው። ጀግና ጀግና የሚል፤ የሚያዳንቅለት፣ የሚደጉም ስለበዛ ነው። እና ይሄ ቢበቃው ጥሩ ነው።

ካሁን በኋላ በዚህ ሀገር እንደድሮው እያጋጨሁ የበላይነቴን ይዤ እቀጥላለሁ የሚል እሳቤ አይሰራም። አሁን አወቃቀሩ መጥፎ ነው። አሁን እንደ ድሮው አንዱ ግራዝማች አንዱን ገፍቶ ወደ ሥልጣን መጥቶ ጉብ ሊል አይችልም። እንደዛ ሊሆን አይችልም።ይህ አስተሳሰብ ሀገር ያፈርሳል።

ምክንያቱም እያንዳንዱ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን ሥልጣን እና መብት አግኝቷል። ክልሉን ቀጣናውን ያውቃል። ሁሉም ጠመንጃ አለው፤ እናም ፈራሽ ነው። ካሁን በኋላ በጠመንጃ መጫወት ኢትዮጵያን ብትንትኗን ያወጣታል። ይሄ እንዳይሆን ይበቃል መባል አለበት እላለሁ። ይሄ ኔጌቲቭ ቲንከሩ /አሉታዊ አስተሳሰብ/ አራማጁ ኤሊት በቃህ ሊባል ይገባል። ፖዘቲቭ ቲንከሩ /አዎንታዊ አስተሳሰብ አራማጁ/ ኤሊት ደግሞ ሊደገፍ፣ ሊበረታታ ይገባል የሚል ሃሳብ አለኝ።

እኔ ሰዎችን በራሴ አራት ቦታ እከፍላቸዋለሁ። አንደኛው የዋህ፣ ደግና ጀግና ነው። ይሄ ሰው የዋህ ነው፤ ደግ ነው፤ ጀግና ነው ፤ ሀገሩን ይወዳል፤ ለሀገሩ ይሞታል። እንደዚህ አይነት ሰዎች አሉ። ሁለተኛው ደግነት በመጠኑ፤ ከፋትም ያለው ሰው ነው፤ ወደነፈሰበት እየነፈሰ የሚኖር ሰው ነው። ሶስተኛው ክፉ ሰው አለ። ክፉ፤ ለምንም የማይሆን፤ ነጌቲቭ ቲንከር / አሉታዊ አስተሳሰብ ያለው/ አለ ብዬ እወስዳለሁ። አራተኛ ብልህ ሰው አለ፤ /ቅደም ተከተሉን ልትገለብጠው ትችላለህ።/ ብልህ ሰው፣ ሀገሩን የሚወድ ሰው፤ ለሀገሩ ማንኛውንም ነገር ያደረገ፤ ታሪክ ሰርቶ ያለፈ አለ። እንደነዚህ አይነት ሰዎች እዚህ ሀገር ላይ እንዳሉ ይታየኛል።

ከሁለተኛው ይሁን፤ ከሶስተኛው አይነት ሰው ግን የኢትዮጵያ ሕዝብ መጠበቅ አለበት። ነጌቲቭ ቲንከር/ አሉታዊ አመላካከት ያለው/ የሆነ ሰው ሁልጊዜ ክፋት ይሰራል፤ ይጠራጠራል፣ ያዋጋል፣ ያጣላል፤ አይሞትም፣ ያስገድላል፣ ይበላል፣ ይኖራል፣ ይሞታል። እንደዚህ አይነት ሰዎች አሉ።

መልዕክቴ የኢትዮጵያ ሕዝብ ይበቃናል የሚል ነገር መጀመር አለበት። ይሄ መነዳት መቆም አለበት። ከምላጫ፣ ከአጭበርባሪ፣ ከማይሞት፣ ከሚያስገድል፣ ከምላሰኛ፣ ምንም ከማይችል ራስን መጠበቅ ይገባል። ከየዋሆቹ፣ ከጀግኖቹ በተለይ መጀመሪያ ላይ ያስቀመጥኳቸው ሰዎች ከራሳቸው በላይ አንተ ስትጎዳ ካዩ ልባቸው ይሰበራል። ለሰው፣ ለሀገር የሚኖሩ ናቸው። እንደነዚህ አይነት ሰዎች አሉ። እንደነዚህ አይነቶቹን ያብዛልን መባል አለበት።

ሁለተኛው አይነት ሰው አይጎዳም። በከፊል ነጌቲቭ ቲንከር፣ በከፊል ፖዘቲቭ ቲንከር ስለሆነ ነው። እሱ ደግሞ ነገሮችን ባላንስ አድርገን እንድናይ ይረዳናል። ሶስተኛው አይነት ሰው አደገኛ ነው። እሱ ነው የህብረተሰቡ ዝቃጭ ክፍል የምንለው፤ እሱ ነው፤ ለሀገሩም፣ ለእህቱም፣ ለወንድሙም፣ ለአባቱም፣ ለእናቱም ጠብ የሚል ነገር የማያበረክት። እንዳውም የሚያባላ እሱ ነው። ከእንደዚህ አይነቱ እንጠንቀቅ ። አራተኛው አይነት ሰው ላይ ትኩረት እናድርግ ፤እንደግፈው ፤ ሀገራችን ይበቃታል፤ ከዚህ የጥፋት አዙሪት እንውጣ የሚል መልዕክት አለኝ።

- ክቡር ፊልድ ማርሻል ብርሃኑ ጁላ የጦር ኃይሎች ጠቅላይ ኤታ ማዦር ሹምና ወደር የሌለው የጥቁር አንበሳ ጀግና ሜዳይ ተሸላሚ ካለቦት ከፍተኛ ኃላፊነት አንጻር ለኛ ብለው ጊዜዎትን ሰውተው ከኛ ጋር ቆይታ ስላደረጉ ከልብ እናመሰግናለን።

**ፊልድ ማርሻል ብርሁኑ ጁሳ ፦ እኔም አመሰግናለሁ።**

# ‹‹በከተማዋ የበጎ ፈቃድ ሥራ ባሕል እየሆነና ተጨባጭ ለውጥ እየመጣ ነው››

**- አቶ አብርሃም ታደሰ**
**የአዲስ አበባ የኅብረተሰብ በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር**

**በኃይሉ አበራ**



ኢትዮጵያውያን ከጥንት ጀምሮ የሚታወቁበት አንድ ባሕል አላቸው። እሱም በጎ መዋልና ማኅበረሰብን በቅን ልብ ማገልገል ነው። ሀገርንና ማኅበረሰብን በጋራ ሆኖ በማገዝ እውቀትንና ጉልበትን ሳይሰስቱ በመስጠት ስማቸው ይጠቀሳል። ለእዚህ ጥሩ ማሳያ የሚሆነው በኅብረት መሥራት (ደቦ) ነው። ‹‹ሀምሳ ሎሚ ለአንድ ሰው ሸክሙ፤ ለሀምሳ ሰው ጌጡ ነው›› የሚለው የኢትዮጵያውያን ብሂላቸውም ሌላው የመረዳዳት አስፈላጊነት ማስገንዘቢያቸው ነው።

ባሕሉ ሲወርድ ሲዋረድ እየዳበረ የመጣና ከማኅበረሰቡ ጋር የኖረ ነው። ወገንን በነፃ ማገልገል ብሔራዊ ክብርና ኩራት የሚያሰጥ ትልቅ የክብር ምልክት ነው። መንገድ መሻገር ያቃታቸው አዛውንትን፣ አይነ ስውራንን እንዲሁም የተቸገሩ የማኅበረሰቡ ክፍሎችን በፍፁም ቅንነት ማገዝ ኢትዮጵያ ውስጥ እንደ ብርቅ አይታይም። የቅንነትና የአክብሮት መገለጫ ነው። ይህን መሰሉን በጎነት በልዩ ልዩ አጋጣሚ በማኅበራዊ ሕይወታችን ውስጥ እናገኘዋለን።

በተቋም ደረጃ ብዙም የማይታየው ይህን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አሁን አሁን (በነፃ የማገልገል ስሜት) ተቋማዊ እንዲሆን ለማድረግ እየተሠራ ነው። ከባሕልና ልምድ ባሻገር ጠንካራ አደረጃጀት እንዲኖረውም መንግሥት በተለያየ ጊዜ ጥረት ሲያደርግ ይስተዋላል። ከቅርብ ዓመታት ወዲህም በበጎ ፍቃድ ማኅበረሰቡን የማገልገልና ለወገን በጎ አሻራን ትቶ የማለፍ ተቋማዊ ሥራ ውጤት እያመጣ እንደሆነ መረጃዎች ያሳያሉ። የዝግጅት ክፍላችንም በተቋማዊ አደረጃጀት ውስጥ ወጥ ቅርፅ ይዞ እየተሠራበት ያለው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ለመዳሰስ ወድደናል። ለዚህም ወደ አዲስ አበባ የኅብረተሰብ በጎ ፍቃድ አገልግሎት ማስተባበሪያ ኮሚሽን ጎራ ብለናል።

የአዲስ አበባ የኅብረተሰበ በጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ አብርሐም ታደሰ እንዳብራሩት፤ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች በከተማዋ ሲጀመር በርካታ ተቋማት አቅም ቢኖራቸውም፣ የት ጋ ምን መሥራት እንደሚገባቸው ብዙም ግልጽ አልነበረም። በበጎ ፈቃድ አገልግሎት በተቋም ደረጃ በከተማዋ መሥራት ከተጀመረ 21 ዓመት ሞልቶታል፤ በወቅቱ የሚከናወኑ ተግባሮች ክረምትን ጠብቆ ተማሪዎችን ከዩኒቨርሰቲ በመጡ ተማሪዎች በነፃ ከማስተማር፣ አከባቢን ከማፅዳት፣ ችግኝ ከመትከልና አልፎ አልፎ ደም ከመለገስ ተግባሮች የዘለለ አልነበረም።

በ2011 ዓ.ም በአዲስ አበባ ደረጃ የበጎ ፈቃድ ማስተባበሪያ ቢሮ ሲመሠረት ፕሮግራሞቹም እየበዙ መምጣታቸውን ኮሚሽነሩ ገልጸዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ አበባ የ10 ዓመት ፍኖተ-ካርታ ተዘጋጅቶ በጎ ፈቃደኝነት ባሕል እንዲሆን በየተቋማቱ እየተሠራ ሲሆን፤ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ባሕል እየሆኑ እና ተጨባጭ ለውጥ እየመጡ ናቸው።

አሁን ያለው አሠራር እድገት አሳይቶ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት ጉዳይ በትምህርት ሥርዓት ውስጥ መካተቱንም የማስተባበሪያው ትልቁ ስኬት መሆኑንም አቶ አብርሃም ጠቅሰዋል። ሲቲዘንሺፕ በሚባለው የትምህርት ዓይነት በጎ ፈቃደኝነት እንደ አንድ የትምህርት ክፍል ሆኖ ትምህርት መሰጠት ተጀምሯል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ ይህም የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ ተፅዕኖ እየፈጠረ መምጣቱን እንደሚያመለክት ተናግረዋል።

እንደ አቶ አብርሃም ገለፃ፤ በጎ ፈቃደኞች በበዙበት ከተማ ኢንቨስትመንት፣ ቱሪዝም፣ ሰላማዊ እንቅስቃሴ ይጨምራል። በዚያው ልክ ደግሞ ምክንያታዊ ወጣቶች እየተፈጠሩ ይሄዳሉ። እነዚህም የማኅበረሰብን ችግር ከሩቅ የሚመለከቱ ሳይሆን ውስጡ ሆነው የሚፈቱ፣ በሀሳብ፣ በጉልበታቸው በአቅማቸው ችግር የሚፈቱ ይሆናሉ። በመሆኑም በጎ ፈቃድ ሥራ ለሀገር ግንባታ መሠረታዊ መሆኑን አመላክተዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህም የበጎ ፈቃድ ተሳትፎው በከተማዋ ተቋማት በኩል እየሰፋ መምጣቱን ጠቁመው፣ የጤና ተቋማትም ነፃ ሕክምና በማድረግ በስፋት እየተሳተፉ መምጣታቸውን ጠቅሰዋል። በማኅበራዊ ሚዲያው ያሉ የተቃርኖ ሀሳቦች መበራከትም በወጣቶች በነዋሪው የሚያስከትላቸው በርካታ አፍራሽ ተግባራት አሉ። አሁን ላይም ማኅበራዊ ሚዲያውን ለመልካም ተግባራት እና ዓላማ ለማዋል የበጎ ፈቃድ አካል ዓላማ ተደርጎ ሥልጠና እየተሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል።

በአዲስ ከተማ ከአውቶቡስ ተራ ጀርባ ያሉ ወጣቶች እና በአካባቢው ያሉ የሕክምና ባለሙያዎች ተሰባስበው ለአካባቢያቸው ሰዎች የዓይን ሕክምናን ጨምሮ የተለያዩ ዓይነት ሕክምናዎችን በግብዓት ጭምር ድጋፍ ሲያደርጉ መቆየታቸውን በአብነት ጠቅሰው፣ በጎ ፈቃድ ላይ መሥራት ምን ያህል የሕሊና እርካታ እንዳለው ማኅበረሰቡ እየተረዳ እና ተሳትፎውንም እያሳደገ መምጣቱን ተናግረዋል።

በዚያው ልክ ለበጎ ፈቃድ የሚያደርገው ልግስና በትክክል ለሚመለከተው ሰው እንደሚደርስ ጠቅሰው፣ ይህንንም እየታየ ባለው የሰው ሕይወት መረዳት እንደሚቻል ገልጸዋል። የመኖሪያ ቤት ግንባታዎችም እስከ ሰባተኛ ወለል ድረስ የሚደርሱ፣ በግብዓት የተሟሉ እና በገንዘብ ቢተመኑ ከፍተኛ ሀብት እና አቅም እየፈጠረ ነው። ይህ ሁሉ በሰው አስተሳሰብ ውስጥ የተፈጠረው የበጎ ፈቃድ ግንዛቤ በዚያው ልክ እያደገ መመጣቱን ያሳየ ነው ብለዋል።

የበጎ ፈቃድ ተግባር ከጊዜ ወደ ጊዜ ባሕል እየሆነ መመጣቱን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፣ አጠቃላይ የበጎ ፈቃድ ተግባራቱ እየተፈጸሙ ያሉት በበጎ ፈቃደኞች ተሳትፎ ከባለሀብቶች እየተሰበሰበ በሚገኝ ሀብት መሆኑን ተናግረዋል። በደም ልገሳም በወጣቶች ተሳተፎ የተገኘ ውጤት የላቀ መሆኑን አስታውሰዋል።

በየዓመቱ ያለው የበጎ ፈቃድ ተሳተፎ እያደገ መሆኑን የጠቆሙት ኮሚሽነሩ፣ ከ2011 ዓ.ም በፊት ይሳተፍ የነበረው የበጎ ፈቃደኛ ቁጥር ከ200 ሺህ የማይዘል ነበር ይላሉ። አሁን ግን በየፕሮግራሞቹ ባለው ድግግሞሽ ከሦስት ሚሊዮን የሚበልጥ ቁጥር እየተሳተፈ ይገኛል ሲሉም ጠቅሰዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ከዚህ በፊት በመቶ ሚሊዮኖች ብር የሚጠጋ ሀብት ብቻ በበጎ ፈቃድ ሥራዎች ሲከናወን ነበር። አሁን ላይ በአንድ ዓመት እስከ ሰባት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የሚጠጋ የበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተሰጠ ይገኛል። ይህም በየዓመቱ በሚሰጠው አገልግሎትም፣ ባለው ተሳትፎ እና የበጎ ፈቃድ አገልግሎቱ በኅብረተሰቡ ውስጥ በስፋት እየሰረጸ ከመምጣቱ አኳያ እድገት እንዳለው ማየት የሚያስችል ነው።

በየዓመቱ የነበረው የቤት እድሳት አፈፃፀም ሲታይም ቢዘያው ልክ ዕድገት ያለው ነው። ያለፈውን ክረምት ጨምሮ ባለፉት ስድስት የለውጥ ዓመታት ውስጥ በየጊዜው ለውጥ ታይቷል። በ2011 አንድ ሺህ 75 ቤት ነው ተገንብቶ ለችግረኞች ተላልፎ የተሰጠው። ይህ አኃዝ በ2015 ግን ወደ ስድስት ሺ 415 ቤት ደርሷል። በአጠቃላይ ያለፈውን ክረምት ጨምሮ ወደ 24 ሺ 236 ቤቶች ግንባታ ተፈፅሟል። ከወጪም አንፃር በተመሳሳይ እያደገ መጥቷል።

ባለፈው ዓመት እነዚህን የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ለማከናወን በታቀደው መሠረት ሁሉም ፕሮግራሞች መከናወናቸውን አቶ አብርሃም ገልጸው፣ አንዳንዶች ከእቅድ በላይ የተፈጸሙ እንደነበሩም ጠቅሰዋል። በከተማዋ በሚደረጉ የበጎ ፈቃድ ሥራዎች ውጤታማነት ከከተማ አስተዳደሩ ጀምሮ የበላይ አመራሩ እና በየደረጃው የሚገኘው የአስተባባሪ ኮሚቴ ተሳትፎ እያደረገ ይገኛል። እነዚህ አካላት ከተሳትፎ በዘለለም ተግባራዊ እንቀስቃሴዎችን እያደረጉ ናቸው። በከተማዋም ሆነ በወረዳ የሚገኘው አመራርም ራሱ በበጎ ፈቃድ ከደመወዙ እየቆረጠ ይሳተፋል፤ በዚያው ልክ ደግሞ ኅብረተሰቡን ያስተባብራል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ከዚህም ባሻገር ሴክተር ተቋማት ተጠሪ ተቋሞቻቸውንና ባለድርሻውን በማስተባበር ግንባታውን ያካሂዳሉ፣ ማዕድ ያጋራሉ። ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ደሞዝተኞችም ተቋሞቹ ባሉበት አካባቢ ያሉ ነዋሪዎች የቤት እድሳት፣ ግንባታ፣ ማዕድ ማጋራት እና ሌሎችንም የበጎ ተግባራት ያከናውናሉ።

ከጥራት አንጻር ከተመለከትን በጣም የተሻሉ እና ከጊዜ ወደጊዜ አዳጊ የሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥም ተፅዕኖ ሊፈጥር የሚችል ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በርካታ ውጤቶች እየተመዘገቡ መሆናቸውን አስታውቀዋል።

አቶ አብርሃም እንዳስታወቁት፤ የቤት እድሳትን በተመለከተ አሁን ላይ የሚገነቡ ቤቶች ላይ ጥራት ለድርድር የሚቀርብ ነገር አይደለም። በአፈጻጸም ከ50 በመቶ በላይ ጥገና ካልተደረገላቸው ጥገና ተደርጓል ብለን አንይዝም። በጭቃ የምናካሂዳቸው ግንባታዎች የሉም በሚባል ደረጃ በጣም ጥቂት ናቸው። በአሁኑ ሰዓት ቤቶች የሚሠሩት በብሎኬት በሲሚንቶ ግራውንድ ላይ የሚሠሩ እና ምንም ፎቅ የሌላቸው ከመሆናቸውም በላይ በጥራት የሚሠሩ ናቸው፤ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ሰዎች ከሆኑ ደግሞ እቃ አሟልተንም ጭምር በመስጠት ወደቤቱ እንዲገቡበት ይደረጋል ሲሉ ገልጸዋል።

በከተማ አስተዳደሩ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ ከሚሠራባቸው ጉዳዮች አንዱ ሰው ተኮር ተግባር መሆኑን ኮሚሽነሩ ጠቅሰው፣ በቀጣይም ተቋማዊ አቅምን እያጠናከርን በመሄድ በአሠራር እና በአካሄድ የተደገፈ ቀጣይነቱን ሊያረጋግጥ የሚችል አሠራር ለመፍጠር የሚያስችል ሥራ እንሠራለን ብለዋል።

ኮሚሽነሩ በ2016 ዓ.ም የበጎ ፍቃድ አገልግሎት ዓመቱን ሙሉ እንደሚካሄድም ጠቁመዋል። እሳቸው እንዳሉት የበጋ በጎ ፍቃድ ተጀምሮ ወደ ሥራ ገብቷል። ክረምት ላይ በርካታ ወጣቶች እረፍት ላይ የሚሆኑበት ጊዜ ሲሆን ሌላው ደግሞ ብዙ ሰዎች ወደዚህ ተግባር ለመግባት ፍቃደኝነታቸው የሚጨምርበት ወቅት ነው። በመሆኑም የክረምት በጎ ፍቃድ ከግንቦት ወር ጀምሮ እስከ መስከረም 30 ድረስ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ በማድረግ በስፋት ይሠራል።

ይህ ተግባር በበጋ ወቅት መቋረጥ የለበትም። ከዚህ ቀደም የነበረው በክረምት ወቅት ነበር ፤አሁን ግን 365 ቀን የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንዳይቋረጥ እንሠራለን ሲሉ ይገልጻሉ። ከኅዳር ወር ጀምሮ እስከ ግንቦት ወር ድረስ በምናካሂደው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት አንድ ሚሊዮን በጎ ፍቃደኞችን ለማሳተፍ ታቅዷል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ በዚህም ሁለት ነጥብ ሦስት ቢሊዮን ብር የሚገመት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት እንሰጣለን፤ ወደ 700 ሺህ የሚጠጋ የከተማችን ነዋሪ ደግሞ ከነዚህ ፕሮግራሞች ተጠቃሚ ሆኗል ብለዋል።

እሳቸው እንዳስታወቁት፤ የክህሎት ሥልጠናዎች፣ የልዩ ፍላጎት ሥልጠናዎች፣ የወሰን ተሻጋሪ በጎ ፍቃድ፣ የደም ልገሳ፣ በጎነት በሆስፒታል ነፃ ሕክምና የኤች አይ ቪ መከላከል ላይ የሚሠራ ሲሆን፣ የመንገድ ትራፊክ፣ የአካባቢ ሰላም፣ ኪነ-ጥበብ፣ የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ድጋፍ እና “ሙያዬ ለሀገሬ” የሚሉ እና የአደጋ መከላከል በጎ ፍቃድ አገልግሎቶች በነዚህ መርሐግብሮች ተካተው የሚሰጡ ይሆናል።

በሀገር አቀፍ ደረጃ ራሱን የቻለ ተቋም ያለው አዲስ አበባ ብቻ ነው ያሉት አቶ አብርሐም፣ አሁን በሀገር አቀፍ ደረጃ የበጎ ፍቃድ አገልግሎት በፖሊሲ ለማስደገፍ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውንም ነው ያስታወቁት። ፖሊሲው ከፀደቀ በሕግ ደረጃ ሲቋቋም የተሻለ አቅም ይፈጠራል ይላሉ።

በተቋማት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት የውዴታ ግዴታ እንዲሆን፣ ተማሪዎች በሰፊው እንዲሳተፉ ቀጣይ በሰፊው የሚሠራ መሆኑን አመላከተዋል። የበጎ ፈቃድ ሥራ ተግባራቱ በኢኮኖሚ፣ በሀብት ክፍፍል የምናረጋግጥበት ነው፤ ባለሀብቱ አንድ ፎቅ ሠርቶ 60፣ 70 እና መቶ ሚሊዮን ብር ሲያወጣ ለሌላው ኅብረተሰብ እድል እየፈጠረ ነው። የሥራ እድልም ፈጠራል። ማኅበራዊ ችግር እንፈታለን ሲሉ ያብራራሉ።

ታዳጊዎችም ላይ የምንሠራው ሥራ አለ። በሕጻናት ላይ በምንሠራው ሥራ 400 ሕጻናት ደጋፊ እንዲያገኙ አድርገናል። ዛሬ በበቂ የሚመገቡት አግኝተው መማር ከቻሉ ለነገ ተስፋ መሆን ይችላሉ ማለት ነው። እነዚህ ሕጻናት ድጋፍ ያገኙት የክረምት በጎ ፍቃድ ላይ ሲሆን 100 የሚሆኑትን ሕጻናት አንድ ባለሀብት ሙሉ ለሙሉ ስፖንሰር አድርጓቸዋል። እንደነዚህ አይነት ሥራዎች በደንብ እየቀጠሉ ሲሄዱ በማኅበረሰብ ውስጥ የሚመጣው የመደጋገፍ ልማድ እየጨመረ ይሄዳል። ዋናው አቅም የሚመጣው ከማኅበረሰብ ሲሆን እኛ በሪፖርት ውስጥ የምናካትተው እኛ የሠራነውን ነው። ነገር ግን የሚፈለገው ማኅበረሰቡ ልማድ እያደረገው ከሄደ ሥራው እየሰፋ ይሄዳል።

በሌሎች ሀገራት ለምሳሌ በስዊድን አስፓልት ቢበላሽ የሚጠግኑት የበጎ ፍቃድ ማኅበራት ሥራውን ይሠራሉ፤ የሆነ ቦታ ላይ አደጋ ቢከሰት በበጎ ፍቃድ ከቤታቸው ተነስተው የሚወጡ ሰዎች አሉ። ከዚያም የተፈጥሮ አደጋም ሆነ ሰው ሰራሽ አደጋ ካጋጠመ ይህንን አገልግሎት ሰጥተው ይመለሳሉ። ይህ በገንዘብ አይሸፈንም፤ የሆነ ሰዓት ላይ በጣም ብዙ አቅም የሚጠይቅ ሰው ተቀጥሮ ሊሸፈን የማይችል ጊዜ የማይሰጥ ጉዳይ ሲሆን በጎ ፍቃደኞች ያስፈልጋሉ።

በአደጋ መከላከል ላይ ከ450 በላይ የሚሆኑ ወጣቶች አሰልጥነናል ያሉት ኮሚሽነሩ፣ በቀጣይ አደጋ ሲያጋጥም እነዚህ ልጆች ድጋፍ ይሰጣሉ ብለዋል። እነዚህ ነገሮች እያደጉ ሲሄዱ በጎ ፍቃደኝነት ይቀራል ማለት ሳይሆን ባሕሪው የሚፈልገው አገልግሎት እየሰፋ ይሄዳል። ማንም ሰው የበጎ ፍቃድ አገልግሎት መስጠት ይችላል፤ በገንዘብ በጉልበት ማገዝ ይችላል። ሲሉም አብራርተዋል።

በሐኪም ቤቶች ላይ የሚሠሩ በጎ ፍቃደኞች ከክልል ለሚመጡ ታካሚዎች የሚታዘዝላቸውን መድኃኒት ከተፈለገው ቦታ በመሄድ ይገዙላቸዋል ሲሉ ጠቅሰው፣ ሰዎች በመሆናችን የሆነ ጊዜ ላይ በተለያየ አደጋ ምክንያት በጎ ፍቃደኞች ሊያስፈልጉን ይችላሉ ይላሉ። ‹‹ሰዎች በመንገድ ላይ ሲወድቁ ሰዎች ይሸሻሉ። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ግንዛቤ ላይ በሰፊው በመሥራት የሚረዳውም እርዳታ የሚያስፈልገውም ሰው እንዳይጎዳ እናደርጋለን ሲሉም ኮሚሽነሩ አስታውቀዋል። ሁሉም ሰው የበጎ ፍቃድ ተሳትፎዎችን እንዲያጠናክርም መልዕክት አስተላለፈዋል።

# ወጣቶች

# “ሥራ ፈጣሪ መሆን ለአንድ ችግር መፍትሔ መስጠት መቻል ነው”

- ወጣት ሲሃም ፈይሰል

**ክብረአብ በላቸው**

በኢትዮጵያ በዓመት እስከ ሁለት ሚሊዮን የሚጠጉ ወጣቶች ወደ ሥራ ዓለም ይቀላቀላሉ ። ለዚህን ያህል ዜጋ በመንግሥት ወይም በግል ተቋማት እና ድርጅቶች የሥራ ዕድል መፍጠር ባለመቻሉ ደግሞ አብዛኛዎቹ ለሥራአጥነት ይዳረጋሉ። ይህንን ችግር ለመፍታት ደግሞ ሥራ ጠባቂ ከመሆን ይልቅ ሥራ ፈጣሪ ሆኖ መገኘት የሚጠበቅ ሆኗል።

ሆኖም በኢትዮጵያ በርካታ ወጣቶች የሥራ ፈጠራ ባለሙያዎች ቢሆኑም የፈጠራ ሃሳባቸውን ወደ ተግባር ለማዋል የመሥሪያ ቦታ እጥረት፣ የብድር አቅርቦት አለመመቻቸት፣ የገበያ ትስስር አለመኖር እና የክህሎት ክፍተቶችና መሰል ችግሮች እንቅፋት ሆኖ ሲገጥማቸው ይስተዋላል።

አንድ ሰው የተሳካለት ሥራ ፈጣሪ ወይም ኢንተርፕረነር ለመሆን፣ የያዘው ሃሳብና ሃሳቡን ተግባራዊ ማድረጊያ ገንዘብ ወሳኝ መሆናቸው አይጠረጠርም። ሆኖም፣ እነዚህ ሁለቱ ብቻ ሥራ ፈጣሪው የተሳካለት የቢዝነስ ሰው እንዲሆን አያስችሉትም። ሥራ ፈጣሪው፣ ስኬትን መቀዳጀት እንዲችል ወይም ጉዞው ወደ ስኬት የሚገሰግስ እንዲሆን፣ ዓይነተኛ የሆኑ የሰብዕና መገለጫዎች ያስፈልጉታል። እንደ ሥራ ፈጣሪ፣ እነዚህ የሰብዕና መገለጫዎች ወይም ጠባዮች ካሉት ሊያዳብራቸው፣ ከሌሉት ደግሞ እንደ አዲስ ኮትኩቶ ሊያሳድጋቸው ይገባል።

ወጣት ሲሃም ፈይሰል ትበላለች። ትውልድ እና ዕድገቷ በኢትዮጵያውያን ብሎም በመላው ዓለም ሕዝቦች ዘንድ የፍቅር፣ የመቻቻል የመከባበርና የአንድነት ተምሳሌት ተደርጋ በምትነሳው ታሪካዊቷ ሀረር ከተማ ነው። ከመጀመሪያ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በዛው ተከታትላለች። በትምህርቷ ጠንካራ ከሚባሉ ተማሪዎች መካከል የነበረችው ሲሃም በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና ጥሩ ውጤት በማምጣት ለከፍተኛ ትምህርት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መቀላቀል ችላለች።

ከሀረር አዲስ አበባ የደረሰችው ሲሃም ዩኒቨርስቲው ‹‹ምህንድስና የደረሳችሁ የህንፃ ዲዛይን ወይም የአርክቴክቸር ትምህርት ለመማር መወዳደር ትችላለሁ›› ብሎ ባሳወቀው መሠረት ተወዳድራ በጥሩ ውጤት ፈተናውን በማለፍ አምስት ዓመት ከግማሽ ትምህርቷን ተከታትላ በአርክቴክቸር ምህንድስና የመጀመሪያ ዲግሪ ከአንጋፋው አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ማግኘት ችላለች።

ወጣት ሲሃም በብዙ መልኩ የዩኒቨርሲቲ ቆይታዋ የተሳካ እንደነበር ትገልጻለች። የአርክቴክቸር ትምህርት ከሌላው የትምህርት አይነት በተለየ መልኩ ክብደት እንዳለው የምትናገረው ሲሃም፤ በዚህ ምክንያት ሌሊቱን ሙሉ በጥናት ከጓደኞቿ ጋር ቁጭ ብላ ታሳልፍ እንደነበር ታስታሳውሳለች። የምህንድስና ትምህርት በተለየ መልኩ ደግሞ አምስት አመት ከግማሽ ነበር የሚወሰደው። ሆኖም ከፈጣሪ ጋር ስኬታማ መሆን ስለመቻሏ ትናገራለች።

በመጀመሪያ ወደ ሥራው ዓለም ስትቀላቀል ስለነበረው ሁኔታ ሲሃም ስትናገር፤ በተለያዩ የግልና የመንግሥት ድርጅቶች ውስጥ ተቀጥራ ስለመስረቷ ታስረዳለች፤ “ተቀጥሮ መሥራት ለተወሰነ ጊዜ መጥፎ አይደለም፤ ተቀጥሮ መስራትን አልቃወምም። ምክንያቱም በአካዳሚክ የትምህርት ቆይታ አጠቃላይ የሆነ እውቀት ነው ይዞ መውጣት የሚቻለው። ወደ ተግባር የሥራ ዓለም ስንመጣ ልዩነት አለው። በተለይም ምህንድስና ደግሞ የተለየ ነው። ስለዚህ ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ለመላመድ ተቀጥሮ መሥራት ጠቃሚ ነው። እኔ በግሌ በብዙ መልኩ ያስተማረኝ ልምድ ያገኘሁበት ነበር” ትላለች።

ሲሃም የራሷን ሥራ ለመስራት ከተቀጣሪነት ወጥታ ወደ ግል ሥራዋ ከመግባቷ በፊት የምትሰራውን ሥራ በግማሽ ቀን በማድረግ በቀሪ ሰዓት የግል ቢዝነሷን ማከናወን እንደጀመረች ታስረዳለች። “የራሴ ሥራ ሲኖረኝ ትርፍ ሰዓት አገኛለሁ ብዬ አስብ ነበር የምትለው ወጣቷ ይህ ግን ስህተት ነበር። ተቀጥሬ ስሠራ ከጠዋት 2 ሰዓት እስከ 11 ሰዓት ነበር የምሠራው። ወደ ራሴ ሥራ ከገባሁ ጊዜ ጀምሮ ግን 18 ሰዓት ነው የምሰራው›› ትላለች።




አሁን የተለያዩ ድርጅቶችን መሥርታ እየሠራች የምትገኘው ሲሃም ኢኖቮ የሚል ስያሜ በተሰጠው ድርጅቷ አማካኝነት በቤት ውስጥ ማስዋብ (interior design) ሥራ ታከናውናለች። ከዚህ በተጨማሪ ክሬኤትቪ ጎጆ በተባለ የራሷ ኩባንያ በኩል የወዳደቁ የቆሻሻ ላስቲኮችን፣ ወረቀቶችን እንደገና በማስተካከል በማስዋብ የሚሸጥ ድርጅት እንደሆነ ትናገራለች።

አንድን ነገር ፈጠራ በተሞላበት መልኩ ወይም ከሌላ ሰው በተለየ መልኩ መሥራት ከተቻለ ውጤታማ መሆን ይቻላል የምትለው ሲሃም፤ የምንሠራው ሥራ አዲስ ነገር ያማከለ፤ ጥራት ያለው መሆን ከቻለ በሰፊ ገበያ ውስጥ ተሰማርቶ አሸናፊ መሆን ይቻላል ትላለች። በተለይ የኮንስትራክሽን ሥራ ጥራትን በእጅጉ ስለሚፈልግ ከምንም በላይ ለጥራት ቅድሚያ መስጠት አስፈላጊ ነው “እኔም ውጤታማ መሆን የቻልኩት በዚህ መርህ መጓዝ በመቻሌ ነው” ትላለች።

ወደ ግል ሥራ ለመግባት በዋናነት ምክንያት ስለሆኗት ነገር ወጣት ሲሃም ስትናገር፤ በግማሽ ቀን ሥራ በምትሠራበት ወቅት ማለትም ወረቀት (recycle) በማድረግ በምትሸጥበት ወቅት በመንግሥት ሥራ ከምታገኘው ደሞዝ የተሻለ ገቢ ማግኘት ቻለች። ይህ አዋጭ መንገድ መሆኑን በመረዳት በሙሉ ጊዜ የግል ሥራ ለመስራት እንደወሰነች እና ሁኔታው በራሱ ወደ ግል ሥራ እንደመራት ትናገራለች።

በኮንስትራክሽን ሥራው በዋናነት ችግር ሆኖ ያለው የዕቃ አቅርቦት ችግር እንደሆነ የምትገልጸው ወጣቷ፤ “የኮንስትራክሽን ዕቃ ለመግዛት አንድ ቦታ ስንሄድ የለም ነው የምንባለው በዚህ ምክንያት እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ድርጅቱም ይበልጥ ፈጠራ ላይ ትኩረት አድርጎ ስለሆነ ሥራውን የሚሰራው ሱቅ የማናገኘውን ዕቃ ውበቱን ሳያጣ በሌላ ዕቃ እንዴት መቀየር እንችላለን የሚለውን በመለየት በራሳችን ለመሥራት ጥረት እናደርጋለን በዚህ መልኩ ያጋጠሙ መሰናክሎችን ለመፍታት እየሠራን ነው ያለነው” ትላለች።

ከአስር ለሚበልጡ ሰዎች በድርጅቶቿ በኩል የሥራ ዕድል መፍጠር እንደቻለች የምትናገረው ሲሃም፤ ከዚህ በተጨማሪ አራት እናቶች በቤታቸው ሆነው እየሠሩ ገቢ እንዲያገኙ መደረጉን ትገልጻለች። እናቶች በቤት ሆነው ለተለያዩ የቤት ማሳመሪያ የሚሆን ዕቃዎችን ማለትም ወረቀት፣ ፕላስቲክ የመሳሰሉትን ለድርጅቱ ያቀርባሉ። እነዚህ ዕቃዎች ለቢሮ ማሳመሪያ ለተለያዩ አገልግሎት መዋል እንዲችሉ ተደርገው ይሠራሉ። በዚህም እናቶች ገቢ ማግኘት እየቻሉ ነው ትላለች።

‹‹ሥራ ፈጣሪ ወይም የቢዝነስ ባለቤት መሆን ለአንድ ችግር መፍትሔ መስጠት መቻል ነው ብዬ ነው የሚወስደው›› የምትለው ወጣት ሲሃም፤ መጀመሪያ ከችግሩ ከልተነሳን እና መፍትሔ ለዚያ ችግር መስጠት የማንችል ከሆነ እና ሰው የሚያደርገውን ነገር፣ ሰው የፈጠረውን መፍትሔ የምንደግም ከሆነ ሥራ ፈጣሪ መሆን አንችልም። ውጤታማም አንሆንም፤ ስለዚህ መጀመሪያ መፍታት የምንፈልገው ችግር ምንድነው የሚለውን ከያዝን እና ከእሱ ከጀመርን ስኬታማ መሆን የማንችልበት ምክንያት የለም›› በማለት ወጣቶችም ሥራ ፈጣሪነትን በዚህ መልኩ ሊረዱት እንደሚገባ ትናገራለች።

አንድ ሥራ ፈጣሪ ወደ ስኬት ለመድረስ ቆስቋሽ ሳያስፈልገው የራሱ ተነሳሽነት ሊኖረው ይገባል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የበለጠ ኃላፊነትን መውሰድ ይጠበቅበታል። በዙሪያው የሚያበረታቱ ሰዎች ቢኖሩ መልካም ነው። ባይኖሩም ግን ከማንም በላይ “ለራሳችንን ሞራል የምንሰጠው” እና የምናነሳሳው ራሳችን መሆን እንዳለብን ወጣት ሲሃም ትናገራለች።

ወጣት ሲሃም እንደምትናገረው፤ አደጋን ለመጋፈጥ ፈቃደኛ መሆን የስኬታማ ሥራ ፈጣሪ ቁልፍ መለያ ነው። አዲስ ቢዝነስ ጀምሮ ስኬት ላይ ለመድረስ፣ ወይም ያለንን ቢዝነስ ለማሳደግ እየፈለግን በሌላ በኩል ደግሞ ምንም ዓይነት አደጋ መሰል ነገር ማሰብ አንፈልግም ማለት አብሮ አይሄድም። በሚገባ አሰላስሎ፣ አውጠንጥኖ፣ ግራ ቀኙን ተመልክቶ አዲስን ነገርን የመጀመርና የመሞከር “አደጋን” ለመጋፈጥ ፈቃደኛ መሆን እንደሚያስፈልግ ትናገራለች።

ሲሃም እንደምትናገረው፤ በትምህርት፣ ቴክኖሎጂ፣ በግብርና እና በሌሎችም የኢትዮጵያን ዕድገት በሚያሳልጡ ዘርፎች ሁሉ የኢትዮጵያ ወጣቶች በሥራ ፈጠራ ላይ ተሰማርተው እየሠሩ ቢገኙም ያላቸውን ርዕይ ወደ ተግባር ላይ ለመለወጥ በርካታ ተግዳሮቶች ይጋፈጣሉ። ስለዚህ ችግሮችን ለመፍታት ሁሉም ባለድርሻ አካላት ጥረት ማድረግ እንዳለባቸው ትገልጻለች።

ልንሰማራ ባሰብንበት መስክ፣ አስተማማኝ የሆነ ችሎታ እንዳለን በራሳችን መተማመን ያስፈልገናል የምትለው ሲሃም፤ በጠራ አእምሮ ስናስብ የሚታየን የችሎታ ክፍተት ካለብን፣ ራሳችንን ከማታለል ይልቅ ችሎታችንን ለማዳበር መነሣት ወይም ሌላ የሚስማማንን የሥራ መስክ መምረጥ ይኖርብናል። ነገር ግን፣ ችሎታው እንዳለን ካወቅን በፍፁም ልንዘናጋ እንደማይገባ ትናገራለች።

ስኬታማ ኢንተርፕረነሮች ከዛሬው እንቅፋት፣ ውጣ ውረድ ወይም ጊዜያዊ ድል ይልቅ የወደፊቱ ጊዜና የሚደርሱበት ከፍታ የሚታያቸው ናቸው። ሁልጊዜም ከወራት፣ ከዓመታት በኋላ ሥራችን የት እንደሚደርስ በማሰብ መቃኘት ይኖርብናል። ራዕይና ዓላማችንን ስናስብና የወደፊት ግባችንን መላልሰን የምናስብ ስንሆን፣ ዛሬ የሚገጥሙንን እንቅፋቶችም ሆነ “ማታለያዎች” ለማለፍ አቅም ይኖረናል።

አዲስ ሥራ ስንጀምር፣ እየሠራንም ከሆነ ሥራችንን ለማስፋት ስናስብ ነገሮች ሁሉ አልጋ በአልጋ ይሆኑልናል ብሎ መጠበቅ ዘበት ነው። ያለን ገንዘብ፣ የሰው ኃይል፣ የሥራ ቦታ፣ የገበያ ትስስር ወዘተ በምንፈልገው “ሃሳባዊ” ልክ የመሆን ዕድሉ አነስተኛ ነው። ስለዚህ ያሉንን ነገሮች ቅደም ተከተል በማስያዝና በሁነኛ መንገድ በማቀናጀት መሥራት መቻል አለብን። እንዲህ ማድረግ እንድንችል ደግሞ ነገሮችን የማቀናጀትና ውጤት የማምጣት ክህሎትን ማዳበር ያስፈልገናል።

በእርግጥ አንድ ቢዝነስ ህልውናው ሊቀጥል የሚችለው አትራፊ ከሆነ፣ በሌላ አባባል ከወጪው ይልቅ ገቢው ከበለጠ ነው። የዚህ ዋናው መለኪያ ደግሞ የተስተካከለ የገንዘብ ፍሰት ነው። ይሁን እንጂ፣ አንድ ቢዝነስ ትርፋማ ለመሆንና ላለመክሰር መጠንቀቅ ያለበትን ያህል ዋና ግቡን እንደው ዝም ብሎ ገንዘብ ማጋበስ እንዳይሆን መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ስለዚህም፣ “በፍጥነት” ከምንሰበስበው ገንዘብ ይልቅ፣ በምርታችን ወይም በአገልግሎታችን ለምንጨምረው እሴት ዋጋ መስጠት ይኖርብናል። ለጥራት፣ ለአገልግሎት ርካታና ለመሳሰሉት እሴቶች ከፍተኛ ዋጋ የምንሰጥ ከሆነ፣ ከጊዜ ወደ ጊዜ ተዓማኒነታችን ከፍ እያለና ትርፋችን እየጨመረ መሄዱ አይቀሬ ነው።

ወጣት ሲሃም እንደምትናገረው፤ በፈጠራ ሥራ ውጤታማ ለመሆን በገበያው ውስጥ የቆዩ የንግድ ድርጅቶች ወይም ኢንተርፕራይዞች ከሚሰጡት አገልግሎትና ከሚያቀርቧቸው ምርቶች በመነሳት ምን መሻሻሎች ብናደርግ ብቁ ተወዳዳሪ ሆነን ልንቀርብ እንችላለን? የሚሉና ሌሎች ተመሳሳይ ጥያቄዎችን በአእምሯችን በማምጣት በራሳችን በርካታ አዳዲስ የንግድ አማራጮችን ማመንጨት እንችላለን ትላለች። ከዚህ በተጨማሪ ነባር ምርቶችን ተጨማሪ አገልግሎቶች እንዲሰጡን አድርጎ በማሻሻል አዳዲስ ምርቶችን ወደ ገበያ መምጣት ይቻላል፤ በዙሪያችን የሌሉ ነገር ግን በሌሎች አካባቢዎች የተለመዱ የምርትና የአገልግሎት አይነቶችን በመለየት ለአካባቢው በሚሆን መልኩ በማቅረብ ስኬታማ መሆን እንደሚቻል ትገልጻለች።

በመጨረሻም ወጣት ሲሃም ባስተላለፈችው መልዕክት፤ ወጣቶች ብዙ ፈተና ሊያጋጥማቸው ይችላል። ነገር ግን እጅ ባለመስጠት እስከመጨረሻው መጓዝ አለባቸው። ኢትዮጵያን ጨምሮ ታዳጊ ሀገራት ከወጣት አምራች የሰው ሃይላቸው ብዙ ስለሚጠብቁ ወጣቶች የራሳቸውንና የሀገራቸውን ነገ የተዋጣለት ለማድረግ መሥራት አለባቸው ስትል መልዕክቷን አስተላልፋለች።

# የምድር በረከት

## የሀገር ውስጥ የድንጋይ ከሰል - አዋጩ የኢንዱስትሪዎች የኃይል አማራጭ

ወርቅነሽ ደምሰው

ኢትዮጵያ እንደ ሲሚንቶ፣ ብረትና የመሳሰሉት ፋብሪካዎች ላሉት ኢንዱስትሪዎቿ የሚያስፈልጋትን የድንጋይ ከሰል ምርት ከውጭ በማስመጣት ስትጠቀም ቆይታለች። ለእዚህም ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሪ አውላለች። ይህ እየሆነ ያለው ደግሞ በሀገሪቱ ለድንጋይ ከሰል ምርት የሚያስፈልገው ጥሬ እቃ በበቂ ሁኔታ ባለበት ነው።

ሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል ምርቱን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየሠራች ትገኛለች። በዚህም ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ 186 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ማምረት መቻሉን የማእድን ሚኒስቴር መረጃዎች ያመለክታሉ። በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ የሚገኙ በርካታ የሲሚንቶ ፋብሪካዎች በኢትዮጵያ የሚመረተውን ይህን የድንጋይ ከሰል ሙሉ ለሙሉ እየተጠቀሙ ይገኛሉ።

የማእድን ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ የኢትዮጵያ ጂኦሎጂካል ኢንስቲትዩት ባደረገው ጥናት መሠረት በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ከ360 ሚሊዮን ቶን በላይ የድንጋይ ከሰል ይገኛል። በሌላ መረጃ በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎችም የራሳቸውን ጥናት አድርገው በቂ ክምችት መኖሩን በማረጋገጥ በዘርፉ ልማት መሰማራታቸውን እየገለጹ ናቸው።

በሀገሪቱ የድንጋይ ከሰል ምርት ላይ የጥራት ጉዳይ ሲነሳ ይደመጣል። ይህን ችግር ለመፍታትም የሀገሪቱን የድንጋይ ከሰል ኢነርጂ የማቃጠል አቅም ለማሳደግና የእርጥበት ሁኔታውንም ዓለም አቀፍ ደረጃዎችን የጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ እየተሠራ እንደሚገኝ የማእድን ሚኒስቴር ይገልጻል። የማዕድን ሚኒስትር ኢንጂነር ሀብታሙ ተገኝ ከድንጋይ ከሰል አምራቾች ማህበር ጋር ዘርፉ ያለበትን ደረጃ፣ እያጋጠሙ ያሉ ችግሮችና የመፍትሔ ሃሳቦች ላይ በቅርቡ ተወያይተዋል። በውይይቱ ላይ ዘርፉ ውጤታማ እንዲሆን በሰው ሃይል ሥልጠና እና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም የሀገር ውስጥ ፍላጎትን በማሟላት የህብረተሰቡን ተጠቃሚነት ማረጋገጥ እንደሚገባም ተገልጿል።

በዘርፉ የተሰማሩ ኩባንያዎችም ዓለምአቀፍ ተሞክሮንችንና ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በሳይንሳዊ መንገድ በማምረት የድንጋይ ከሰልን ለተጠቃሚዎች ለማቅረብ በቅንጅት ሊሰሩ እንደሚገባም ነው የተጠቆመው። የድንጋይ ከሰልን በሀገር ውስጥ ምርት ሙሉ በሙሉ በመተካት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሪ ለማስቀረት በትኩረት እየተሠራ ስለመሆኑም ከማዕድን ሚኒስቴር ያገኘነው መረጃ ያመለክታል።

በድንጋይ ከሰል ልማቱ ለመሳተፍ ከስድስት በላይ ኩባንያዎች እየሠሩ እንደሚገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ። ከእነዚህ መካከልም አንዳንዶቹ ወደ ልማቱ የገቡ ሲሆን፣ ሌሎች ደግሞ በፋብሪካ ግንባታና በመሳሰሉት ላይ ናቸው።

በቅርቡ የተካሄደውና ከዘጠና በላይ ኩባንያዎች እንደተሳተፉበት የተነገረለት የማእድን ኤክስፖም የተለያዩ ኩባንያዎች በድንጋይ ከሰል ልማት ላይ መሠማራታቸውን አመላክቷል። ኩባንያዎቹ የድንጋይ ከሰል ምርታቸውን ናሙናም ይዘው ቀርበው ታይተዋል።

ከእነዚህ ኩባንያዎች አንዱ ‹‹ዮ ሆልዲንግ ንግድ እና ማኑፋክቸሪንግ›› የተሰኘው ሀገር በቀል ኩባንያ ነው። ኩባንያው በኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የድንጋይ ከሰል ማምረቻ ፋብሪካ በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል አቋቁሞ እየሠራ ይገኛል።

የኩባንያው የአቅርቦት ሰንሰለት ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ ፍቅሬ ኤክስፖው የኩባንያውን ምርቶች በማስተዋወቅ የገበያ ትስስር ለመፍጠር ማስቻሉን ይናገራሉ። እሳቸው እንዳሉት፤ በዚህም በሀገሪቱ ካሉት ውስን የድንጋይ ከሰል ተጠቃሚ ትልልቅ ፋብሪካዎች ጋር በመነጋገር የገበያ ትስስር ለመፍጠር የሚያስችሉ ምቹ ሁኔታዎች ተፈጥረዋል። እስካሁን የድንጋይ ከሰል የማይጠቀሙ ኩባንያዎች እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ምክረ ሃሳብ መለገስ እና ማሳመን የሚያስችሉ ተግባሮችን ማከናወን ተችሏል።

ከኤክስፖው ጎን ለጎን ከፋብሪካዎች ጋር ከተደረገው ውይይት የተረዳነው የድንጋይ ከሰል ለመጠቀም ብዙ መሥራት እንደሚያስፈልግ ነው ሲሉ ጠቅሰው፣ ለዚህም በቅድሚያ የቴክኖሎጂ ሽግግር ማድረግ እንደሚያስፈልግ አቶ ቴዎድሮስ አስታውቀዋል። የብረት፣ የወረቀትና የጨርቃጨርቅ ፋብሪካዎች እና አዳዲስ ፋብሪካዎች ሁሉም በሚባል ደረጃ የኃይል አቅርቦት ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት ችለናል ይላሉ።

ይህንን ችግር በቀላሉ ለመቅረፍ መጀመሪያ የድንጋይ ከሰል ለመጠቀም የሚያስችሉ ዘዴዎችን መቀየስ እንደሚያስፈልግ ጠቁመው፣ ይህም ሲሆን አንዳንድ ፋብሪካዎች ቴክኖሎጂዎቻቸውን በመቀየር አዳዲስ የቴክኖሎጂ አማራጮች መጠቀም እንደሚጠቅባቸው አመላክተዋል።

አቶ ቴዎድሮስ እንዳሉት፤ እሳቸው በኤክስፖው ላይ ከተሳተፉ የተለያዩ ድርጅቶች ጋር በመነጋገር የድንጋይ ከሰል መጠቀም የተሻለ የኃይል አማራጭ እንደሆነ ለማስረዳት ጥረት አድርገዋል። በነዳጅ እና የድንጋይ ከሰል ዋጋ መካከል ያለው ልዩነት አይገናኝም፤ የድንጋይ ከሰል ዋጋ በጣም ትንሽ መሆኑን መጠቆማቸውን ገልጸው፣ ልዩነቱ ለውድድር እንደማይቀርብም ጠቅሰዋል። ስለድንጋይ ከሰል የጥራት ደረጃም እንዲያውቁ በማድረግ አብሮ ለመሥራት የሚያስችሉ ሥራዎችን በመሥራት የገበያ ትስስሩን ለመፍጠር ተችሏል ብለዋል።

የማዕድን ዘርፉ ገና ያልተነካ ብዙም ያልተሠራበት ነው የሚሉት አቶ ቴዎድሮስ፤ ‹‹ነዳጅንም ሆነ የድንጋይ ከሰልን የምንጠቀመው ለኃይል አገልግሎት ነው። ይህ ሲባል ደግሞ ነዳጅ በፈሳሽ መልኩ ያለ ኃይል ሲሆን የድንጋይ ከሰል ደግሞ በጠጣር መልኩ ያለ ኃይል ነው። በድንጋይ ከሰል ላይ በሀገር ውስጥ ከሠራን በእርግጠኝነት ከውጭ የሚመጣውን ብዙ ፋብሪካዎች የሚጠቀሙትን ለነዳጅ የሚወጣውን ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ ማዳን ይቻላል። ለኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልገውን የሀገሪቷን ነዳጅ ፍጆታ ሙሉ በሙሉ በድንጋይ ከሰል መተካት ይቻላል›› ብለዋል።

እሳቸው እንዳብራሩት፤ ይህ እንዲሆን ከተፈለገ ደግሞ አሁን ያሉት ፋብሪካዎች የሚጠቀሙትን ኃይል ለመቀየር ወደሚያስችላቸው ቴክኖሎጂ መምጣት ያስፈልጋል። የድንጋይ ከሰልን በኃይል አማራጭነት መጠቀም መልመድ አለበት። ለዚህም በኢንዱስትሪው ላይ መሥራት ይኖርበታል። መንግሥትም በዚህ ረገድ የተለያዩ ድጋፎችን በማድረግ ኢንዱስትሪዎቹ ሀገር ውስጥ የሚመረተውን የድንጋይ ከሰል እንዲጠቀሙ ሊያበረታታ ይገባል። ይህ ከተተገበረ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ከተደረገ፣ በመረጃ የተደገፈ አሠራር ሥራ ላይ ከዋለ ፣ ፋብሪካዎች ዘመናዊ አሠራሮች ከተከሉ፣ የሰው ኃይሉ እየበቃ ከመጣ ዘርፉን ወደ ተሻለ ደረጃ ማድረስ ይቻላል። እንደዚህ አይነት ኤክስፖዎች ይህ እንዲፈጠር ያግዛሉ፤ እጅግ በጣም ጥሩና ብቃት የሚፈጥሩ ናቸው።

አምናም ሆነ ዘንድሮ የተካሄደው የማዕድን ኤክስፖ ማዕድናትን ያስተዋወቀ ብቻ ሳይሆን አዳዲስ እይታዎች የተመላከቱበት ነው፤ በቀጣዩም ከዚህ በበለጠ መልኩ ሊዘጋጅ ይገባል ብለዋል። ለምሳሌ የድንጋይ ከሰል ከሀገር አንጻር ያለው አንድምታ ምንድነው? ከውጭ የሚመጣው የድንጋይ ከሰል ምርት መተካት ብቻ ነው ወይስ ነዳጅን መተካት ይችላል የሚለው በሚገባ ተጠንቶ መሥራት እንዳለበት ይጠቁማሉ። እንደዚህ አይነት ኤክስፖዎችን በማስፋት በርካታ ድርጅቶች እና ተቋማት በማሳተፍ ትልቅ ሥራዎች መሥራት እንደሚቻልም አመላክተዋል።

እሳቸው እንዳሉት፤ የኤክስፖው ዋና ዓላማ የመረጃ ልውውጥ እንዲኖር በማድረግ ፣ ቴክኖሎጂዎችን በማስተዋወቅ፣ የልምድ ልውውጥ በማድረግ፣ ድጋፎችን እንዲኖሩ እና አማራጮችን በማስፋት ረገድ ከብዙ ባለድርሻ አካላት ጋር ማገናኘት ነው። ያንን ለማስፋትና ውጤታማ ቴክኖሎጂ ሊያመጣ የሚችለውን ለውጥ ለማምጣት አስቀድሞ ማህበረሰቡ ማወቅ አለበት ፤ በእንደዚህ አይነት ጉዳዮች ላይ ከተሰራ የበለጠ ውጤታማ መሆን ይቻላል።

እሳቸው እንዳሉት፤ በድንጋይ ከሰል ጉዳይ ላይ መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት ይገኛል። በሠለጠነ የሰው ኃይል ላይ ኢንስቲትዩት በማቋቋም ጭምር በተደራጀ መልኩ ሊሠራበት ይገባል። የሌሎች ሀገራት ተሞክሮ እንደሚያሳየው ድንጋይ ከሰል ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው መሆኑን ነው። ሩሲያ፣ ህንድ፣ ቱርክ እና የመሳሳሉት በድንጋይ ከሰል ላይ ይሠራሉ። እነዚህ ሀገሮች በኢንስቲትዩት ደረጃ የተቋቋመ የድንጋይ ከሰልን ጉዳይን የሚመራ ተቋም አላቸው። በሁሉም መልኩ የተደራጁ ናቸው።

በእኛ ሀገርም በዚህ መልኩ ከተሠራ ኢትዮጵያ በድንጋይ ከሰል በኩል ከየትኛውም ሀገር በላቀ ደረጃ ላይ ትደርሳለች ያሉት አቶ ቴዎድሮስ፣ ይህም አንድን ሀገር ከድህነት ለማውጣት፣ በሀገሪቱ የኢንዱስትሪ አብዮት ለማምጣት የሚያስችል መንገድ እንደሆነ ጠቅሰው፣ መንግሥት ትልቁን ትኩረት ሰጥቶ በቴክኖሎጂም፣ በሰው ኃይል በአቅርቦትም ድጋፍ ማድረግ አለበት ሲሉ አመልክተዋል።



በሀገሪቱ ባለፈው ዓመት አንድ ነጥብ 186 ሚሊዮን ቶን የድንጋይ ከሰል ማምረት ተችሏል

በሜድሮክ ኢንቨስትመንት ግሩፕ ስር ከሚተዳደሩ ኩባንያዎች አንዱ የብሔራዊ ማዕድን ኮርፖሬሽን ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበር ነው፤ ኩባንያው በኤክስፖው ተሳትፏል። ኮርፖሬሽኑ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካ ከኦሮሚያ ክልል ነቀምት አርባ ኪሎሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው አርጆ አካባቢ እየገነባ ይገኛል።

የኮርፖሬሽኑ ዋና ፕሮጀክት ሥራ አስኪያጅ አቶ በየነ ጨመዳ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካውን ለመገንባት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ከቱርክ ተገዝተው አገር ውስጥ መግባታቸውን ይገልጻሉ። ፋብሪካው በሰዓት ሁለት መቶ ቶን የድንጋይ ከሰል ለማጠብ እንደሚያስችል ጠቅሰው፣ ግንባታው ሲጠናቀቅ ለ150 ሰዎች በቋሚነት የሥራ እድል እንደሚፈጥር ጠቁመዋል።

ኮርፖሬሽኑ የድንጋይ ከሰል እጥበት ሥራ ለመሰማራት በመንግሥት በኩል ከተመረጡ ኩባንያዎች መካካል አንዱ መሆኑን የጠቆሙት አቶ በየነ፤ በዘርፉ መሠማራቱ በሀገሪቱ በብዛት ያለውን የድንጋይ ከሰል ጥሬ እቃ ውጤታማ በሆነ መልኩ መጠቀም እንደሚችል ገልጸዋል። ይህንንም ኮርፖሬሽኑ ባደረገው ጥናት ማረጋገጡን ጠቁመዋል።

የፋብሪካው ግንባታ ባለፈው ዓመት መጀመሩን ጠቅሰው፤ አሁን የአፈር ሥራው ተጠናቅቆ የሲቪል ሥራው እየተሠራ ነው ይላሉ። በአካባቢው ያለው አለመረጋጋትና የጸጥታ ችግር ግንባታውን በሚፈለገው ፍጥነት አከናወኖ ሥራ ለመጀመር እንቅፋት ፈጥሮ መቆየቱንም ይገልጻሉ። ሌላው ዋና ተግዳሮት የውጭ ምንዛሪ እጥረት እንደነበር ጠቅሰው፤ ይህ ችግር ተቀርፎ ለፋብሪካው ግብዓት የሚያስፈልጉ ቁሳቁስ ወደ ሀገር ውስጥ መግባታቸውን አስታውቀዋል።

የኮርፖሬሽኑ የድንጋይ ከሰል ማጠቢያ ፋብሪካ እየተገነባ ቢሆንም፣ የድንጋይ ከሰል ማምረት የሚቻልበት ማምረቻ ቦታ ማግኘት አለመቻሉም ሌላው ተግዳሮት መሆኑን አቶ በየነ ጠቁመዋል። ‹‹እኛ የድንጋይ ከሰል የማምረቻ ቦታ ስንጠይቅ ክልሎች የሚሰጡት መልስ ቀደም ሲል ፈቃድ የወሰዱ ሰዎች አሉ፤ ከእነርሱ ጋር ሥሩ የሚል ነው። ከግለሰብ ገዝቶ መሥራት ምንም አይነት መተማመኛ አይኖርም። እንደዚህ አይነቶቹ ችግር ቢስተካከሉ ጥሩ ይሆናል ›› ሲሉ አስገንዝበዋል።

ኮርፖሬሽኑ ትልቅ አቅም ይዞ ታምኖበት የድንጋይ ከሰል ለማምረት ፋብሪካ ከገነባ ለፋብሪካው ግብዓት የሚሆነው ጥሬ እቃ የሚመረትበት ቦታ መስጠት የግድ ነው የሚሉት አቶ በየነ፤ ‹‹እንደዚህ አይነት ችግሮች በየክልሉ ስላሉ ችግሩን ማዕድን ሚኒስቴር በሚያዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ ድርጅቱ እያነሳ መሆኑን አስታውቀዋል። ክልሎች የማዕድን ሚኒስቴር የሚሰጠውን አቅጣጫ መፈጸም ላይ ክፍተት እንዳለባቸው አቶ ገመቹ ጠቁመዋል።

ማዕድን ላይ የፌዴራልና የክልሎች ኃላፊነት በተመለከተ የተወሰነ ነገር እንደሌለም ጠቅሰው፣ ክልሎች የፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር የሰጠውን አቅጣጫ ለመቀበል የሚቸገሩበት ሁኔታ እንዳለም ይናገራሉ። የማእድን ጉዳይ ከላይ እስከታች ያለው መዋቅር በደንብ ትኩረት ሰጥቶት ተናብቦ መሥራት ያለበት መሆኑንም አመላክተዋል።

አሁን በማዕድን ልማት ላይ የሚታየው ማዕድን አለማለሁ ብለው የወሰዱትን ፈቃድ ብቻ ይዞ ወደ ሥራ ሳይገቡ መቀመጥ ነው ያሉት አቶ በየነ፣ ለማዕድን ዘርፉ ምንም አይነት አስተዋጽኦ የማያበረክቱ እንደነዚህ አይነት በርካታ አካላት እንዳሉ ጠቁመዋል። ይህም ለድንጋይ ከሰል ልማቱ ቀጣይነት ላይ አሉታዊ ተጽእኖ ሊያሳድር እንደሚችል አስገንዝበዋል።

‹‹ፋብሪካ ገንብተን ለፋብሪካ የሚሆነውን ጥሬ እቃ የሚያቀርበው አካል አላቀርብም ቢል ችግር ውስጥ መግባታችው አይቀርም›› ሲሉ ጠቅሰው፣ ልማቱ ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲሰራ ለፋብሪካዎችና ትልቅ አቅም ለሚፈጠሩ ሰዎች የድንጋይ ከሰል እጥበት ሥራውን እንዲያከናወኑ ማድረግ መልካም ይሆናል ብለዋል። እነዚህ ችግሮች ተቀርፈው ሥራው በሚገባ የሚሠራበት ሁኔታ ከተፈጠረ በድንጋይ ከሰል ውጤታማ መሆን የሚቻልበት ጊዜ ሩቅ እንደማይሆን አቶ በየነ አመልክተዋል።

አቶ በየነ ኮርፖሬሽኑ የማዕድን ሚኒስቴር ባዘጋጀው የማዕድንና ቴክኖሎጂ ኤክስፖ ላይ ባለፈው ዓመትም ዘንድሮም መሳተፉን አስታውሰዋል ። እንደዚህ አይነት ኤክስፖዎች የመዘጋጀታቸው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ የማዕድን ዘርፉን ለማስተዋወቅም ሆነ የተሻለ ደረጃ እንዲደርስ ለማድረግ በእጅጉ ይጠቅማሉ፤ አምራቾችን ከገዥዎች ጋር ያገናኛሉ ብለዋል። እንደ ድርጅት ምርቶቻችን በርካታ ናቸው ያሉት አቶ በየነ፣ መድረኩ ከብዙዎች ጋር እንዲንተዋወቅና የገበያ ትስስር መፍጠር እንድንችል አርጎናል ሲሉ ገልጸዋል።

በኤክስፖ ላይ ከብዙ ድርጅቶች ጋር ተገናኝተናል የገበያ ትስስር ለመፍጠር ችለናል ሲሉ አቶ በየነ ገልጸዋል ፤ እንደዚህ አይነት ኤክስፖዎችን በየዓመቱ ማካሄዱ ጠቀሜታው ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፣ መድረኩ በየዓመቱ እየተሻሻለ እንዲካሄድ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል። የሌሎች ሀገራትን ተሞክሮ በመውሰድ በሀገራችን ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲጣጠም በማድረግ እያሰፋ እንዲሄዱ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ሃሳባቸውን አጠቃለዋል።

መዝናኛ

# የብዕር ጠብታ

## አባ ጎሹ

በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)

ድስት ጠጋኙ አባ ጎሹ የአይኖቻቸውን እዳሪ በእጃቸው እያባበሱ የማለዳዋን ጀምበር ተከትለው ከቤት ወጡ። ለአንድም ቀን ከጎባጣ ጀርባቸው ላይ ወርዶ የማያውቀው አሮጌ ማዳበሪያ በስብርባሪ ብረታ ብረት ተሞልቶ ዛሬም እንደታዘለ ነው። የሁልጊዜም ጸሎታቸው የማዕድ ቤት ድስቶች ሁሉ ተሸንቁረው እሳቸውን እንዲጠብቁ ነው።

አባ ጎሹ ቀይ ናቸው። ቀይነታቸው ግን አይታይም። ወይቧል ። በውብ የሽማግሌ ፊታቸው ላይ እድሜ የተጫነው የደስ ደስ ይታያል። የእድሜያቸውን አኀዝ ባያውቁትም በነሉሲ ዘመን እንደነበሩ ግን ገጻቸው ምስክር ነበር። ቁመታቸው ረጅም ነው... ከለግላጋነታቸው የተነሳ ከእግዜር ጋር በቅርበት የሚነጋገሩ ብቸኛው ፍጡር አስመስሏቸዋልከ። የሰፈራቸውን አቧራማ መንገድ ጨርሰው ... ራቅ ካለ መንደር ደረሱ።... ከጎዳናው ግራና ቀኝ ካለው ቤት ላይ አይኖቻቸውን እያንቀዋለሉ፤

“ቀዳዳ ድስት ያለው... ቀዳዳ ድስት ያለው... አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ። እያሉ ከአንዱ ሰፈር ወደ አንዱ ሰፈር ኳተኑ ። እሳቸው የእለት ጎርሳቸውን የሚሸፍኑበትን አንድም የጥገና ሥራ ሳያገኙ አብራቸው የወጣችው የማለዳ ጀንበር ጥላቸው ሸሸች። አባ ጎሹ በየመንገዱ የሚያገኙትን የሰው ቤት በቅልውጥና እያማተሩ “ቀዳዳ ድስት ያለው ... ሰባራ ድስት ያለው አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ”። በማለት እንደ እድር ለፋፊ ጉሮሮአቸው እስኪንጣጣ ጮሁ ። ይህ የራሳቸው ግጥም ነው... በእድሜ የተማሩት ... በዘመን ያጠኑት የእንጀራ ገመድ ። የደንበኞቻቸውን ቀልብ ለመሳብ የዘየዱት መላ።

በሰፈሩ ውስጥ ድስትና ወይዘሮ የሌለ እስኪመስል ድረስ ጥሪያቸውን የሰማ አንድም ሰው አልነበረም። ሆዳቸውም መራቡን ሊያስታውቅ እንደ ሰኔ ሰማይ አጉረመረመ። እውነት ለመናገር የዘመናቸውን ገሚሱን ያሳለፉት በጾም ነው። ሁሉም ቀን ለእሳቸው የጾም ቀን ነው።...የድህነት ጾም። አሁንም አልበሉም። ትናንት የባቄላ አሹቅ እንደቀመሱ ነው ። ሁሌም ጾመኛ ሁሌም ምኞተኛ ናቸው... ሽማግሌው አባ ጎሹ።

በአዋጃቸው መሃል አንድ የተስፋ ድምጽ ሰሙ። አንዲት ወይዘሮ ሴት ‹‹ወዲህ ይግቡ›› ስትል ጠራቻቸው። ከመግባታቸው ወስፋት የሚቀሰቅስ የምግብ ሽታ ተቀበላቸው ። በአምሮት ወስፋታቸው ተንጫጫ።

ወይዘሮዋ ከወደመአድ ቤት በኩል ሁለት እኩል መጠን ያላቸውን መናኛ ድስቶች ይዛ ተመለሰች።

“ይሄውሎት በደንብ አድርገው ይስሩት” ስትል አቀበለቻቸው። ብዙም ጎልማሳነት ባልሸሻቸው አይኖቿ ስታያቸው ቆይታ ካጠገባቸው እብስ አለች። ስትራመድ ዳሌዋ ይደንሳል... ወጣትነት ከድቶት በጉልምስና እድሜ ላይ ቢሆንም ወንድ ልጅ ለማነሁለል ሃይል ነበረው።

አባ ጎሹ ሁለቱን ድስቶች አገላብጠው ካዩ በኋላ ከማዳበሪያው ውስጥ መዶሻና መጠገኛ ብረት በማውጣት መቀጥቀጥ ጀመሩ። ቀጥቅጠው ካቆነጇቿቸው መንትያ ድስቶች የሚያገኟትን አስር ብር በምን እንደሚያጠፏት በልባቸው እቅድ ጀመሩ። እንዲህ በደከማቸውና ሕይወት ባስመረቻቸው ሰአት የመጠጣት... ጠጥቶም የመስከር አመል አለባቸው። በዚህም በሚያገኟት አስር ብር ሊጎነጩ እቅድ ያዙ። ቀጥቅጠው ያሳመሩትን አሮጌ ድስት ለወይዘሮዋ ሊሰጡ... ድምጽ አሰሙ ... እሜቴ የሚል ።

የጥሪ ድምጽ የሰማችው ወይዘሮ ከለስላሳ ጸጉሯ ላይ የተንሸራተተ ሻሽዋን በእጇ እያጠበቀች ወደ ውጪ ወጣች።

“ይሄውልሽ ኩችም አድርጌ አበጅቼልሻለው። የፈለግሽውን ነገር ልታበስይበት ትችያለሽ” ሲሉ አቀበሏት።

ወይዘሮዋ የድስቶቹን ቂጥና ሆድ ካየች በኋላ ስንት ነው? ስትል ጠየቀች።

‹አስር ብር ይበቃኛል › መለሱላት።

በሻሿ ጠቅልላ ጆሮ ግንዷ ስር የደበቀችውን አስር ብር አውጥታ ሰጠቻቸው ።

አባ ጎሹ ብርቅ የሆነችባቸውን አስር ብር ሰባት ጊዜ አጣጥፈው ከሱሪያቸው ስር ካለ ሌላ ኪስ ውስጥ በመክተት ወይዘሮዋን አመስግነው ሄዱ። ቀዳዳ ድስት ያለው፣ አሮጌ ድስት አዳሹ መጥቷል አባ ጎሹ ከማለታቸው ከወጡበት ቤት ቀጥሎ ካለው ሶስተኛው ጊቢ ውስጥ ጥሪ ሰምተው ወደዛው አመሩ። የጎረቤት ሰዎች እርስ በእርስ እየተጠራሩ ለአባ ጎሹ የገቢ ምንጭ ሆኑ። ጀምበር ከጠለቀች ጀምሮ አባ ጎሹ አምስት አሮጌ ድስቶችን አደሱ። እንዳሰቡት ርሃብና ድካማቸውን ሊረሱ ቀን ሙሉ ተንከራተው ያገኟትን ሃያ አምስት ብር ጨብጠው ብረት የሞላውን አሮጌ ማዳበሪያ እንደተሸከሙ ወደ መሸታ ቤት አቀኑ። ገና በር ከመድረሳቸው የአረቄው ሽታ ሠነፈጣቸው። የጀርባቸውን ሸክም ሰዋራ ቦታ ደብቀው ወደ ውስጥ ገቡ። ሃያ አምስት ብሯን ዳግመኛ ቆጥረው ለማውጣት እንዲመቻቸው በማሰብ ከደረ ኪሳቸው ውስጥ ከተቱት።

ከፊት ለፊታቸው አንድ ወጣት ጨለምለም ካለ ቦታ ላይ ተቀምጦ እያያቸው እንደሆነ አልተረዱም ነበር። ወጣቱ የጎፈረ ጸጉሩን በእጁ እያፍተለተለ የአባ ጎሹን ሃያ አምስት ብር እንዴት መውሰድ እዳለበት ሲያሰላስል ነበር።

አባ ጎሹ ገና ቂጣቸው መሬት ከመንካቱ አረቄ አዘዙ። የናፈቁትን መጠጥ በአንድ ትንፋሽ ጨለጡት። ሆዳቸው ቅጥል፣ አንጀታቸው እርር አለ። ደግመው ጠረጴዛውን ቆረቆሩ እስከ አፍጢሙ ተሞላላቸው። አባ ጎሹ ያለወትሯቸው ቶሎ ሰከሩ። ደክመው የለ?... ተርበው የለ?

ወጣቱ ከዚህ በላይ ጊዜ ማጥፋት አልፈለገም። የአባ ጎሹ ስካር የፈለገውን እንዲያደርግ እድል ስለሰጠው ከተቀመጠበት ተነሳ። በዘየደው መላ የደረት ኪሳቸውን ፍራንክ ሊወስድባቸው የቅርብ ዘመዱን ያገኘ ያህል ደስ በሚል ፈገግታ ተንደርድሮ አቀፋቸው ። ‹እንዴት ኖት?... ሰላም ኖት ? ጠፉ እኮ... በሰላም ነው ? ሠላምታው ማብቂያ አልነበረውም። ወጣት ትከሻውን ስንት ነገር የተሸከመ አዛውንት ትከሻቸው ላይ እያጋጨ የሰላምታ መዓት አወረደባቸው ።

አባ ጎሹ በወጣቱ ሠላምታ ተደስተው አቅፈው አገላብጠው ሳሙት። ቢያውቀኝ ነው እንጂ በሚል የደግነት ስሜት ሣያውቁት አጻፋቸውን መለሱለት።

ወጣቱ እንዳሰበው የአባ ጎሹን ሃያ አምስት ብር ከደረት ኪሳቸው ውስጥ ሞጭልፎ ተሰወረ። ደማቸውን ፣ የሽማግሌ ወዘናቸውን ነጥቆ እብስ አለ። አባ ጎሹ ሀገር ሰላም ብለው አረቄያቸውን ይኮመኩማሉ። በአንድ ትንፋሽ ጭልጥ፣ ሌላ ሙልት እሱንም ፉት... ጭልጥ... ጠረጴዛ መቆርቆር። አፍና ብርጭቆአቸው ሳይለያይ ሰአቱ ነጎደ። ፈጣኖቹ አስተናጋጅ ከአባ ጎሹ ፊት ሣይሸሹ በአፍ... በአፉ ይሞሉላቸዋል። አባ ጎሹ የደረታቸውን ሃያ አምስት ብር ተማምነው ዶሮ እስኪጮህ ድረስ ጠጡ።

# ዓለም አቀፍ

## ሶማሊያ ከዓለም ባንክ እና አይኤምኤፍ የ4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ብድር ተሰረዘላት

በጋዜጣው ሪፖርተር

ሶማሊያ ከዚህ በፊት ከዓለም ባንክ እና አይኤምኤፍ ለተለያዩ ስራዎቿ የተበደረቻቸው ብድሮች መክፈያ ጊዜ ደርሶባት ነበር። ሀገሪቱ በኮሮና ቫይረስ፣ ለዓመታት በዘለቀው ጦርነት እና በድርቅ ምክንያት ብድሮቿን መክፈል እንደማትችል አስታውቃም ነበር።

የዓለም ባንክ እና አይኤምኤፍ ሶማሊያ ያለባትን የ4 ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር ብድር ምህረት ማድረጉን ቢቢሲ ዘግቧል። የሶማሊያ ጠቅላይ ሚኒስትር ሀምዛ አብዲ ባሬ እንዳሉት የአራት ነጥብ 5 ቢሊዮን ዶላር የሀገሪቱን ዓመታዊ እድገት ከ60 በመቶ በላይ ድርሻ ነበረው ብለዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አክለውም የሁለቱ የገንዘብ አበዳሪ ተቋማት እዳ ስረዛ እያንዳንዱ ሶማሊያዊ 300 ዶላር እዳ እንደተሰረዘለት ያስረዳል ሲሉም ተናግረዋል። ሶማሊያ በከፍተኛ እዳ ጫና ምክንያት ውስጥ ካሉ የዓለማችን ሀገራት መካከል አንዷ የነበረች ስትሆን አሁን ላይ ያለባት እዳ ከዓመታዊ ምርቷ ወይም ጂዲፒ ጋር ሲነጻጸር 8 በመቶ ብቻ ሆኗል።



የብድር ስረዛውን ተከትሎ ሶማሊያ በደስታ ጭፈራ ሳይ ናት ተብሏል

ጠቅላይ ሚኒስትሩ "አሁን ሶማሊያ በቂ ገንዘብ እጇ ላይ ይኖራታል፣ የውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንት መሳብ ትችላለች ለዜጎቿም የሥራ እድል መፍጠር ትችላለች” ብለዋል። ሶማሊያ ከፈረንጆቹ 1996 ጀምሮ ዓለም ባንክ እና አይኤምኤፍን ጨምሮ ከሌሎች ሀገራት የተበደረችው ብድር የነበረባት ሲሆን ከ90 በመቶ በላይ የነበረባት ብድር ተነስቶላታል።

የእዳ ስረዛውን ተከትሎ በሶማሊያ መዲና ሞቃዲሾ እና ሌሎች ከተሞች ደስታ እና ጭፈራ እንደደራ ተገልጿል።

## በአራት ልጆቿ ግድያ ተጠርጥራ የታሰረችው እናት ከ20 ዓመት በኋላ ነጻ ወጥታለች

በጋዜጣው ሪፖርተር

“የአውስትራሊያ ጨካኟ እናት” የሚል ቅጽል ስም ተሰጥቷት የነበረችው እናት ከ20 ዓመት እስር በኋላ ነጻ ወጥታለች።

ካትሊን ፎልቢግ ከ1989 እስከ 1999 ድረስ ባሉት ዓመታት አራት ልጆቿን ገድላለች በሚል በ2003 ለእስር የተዳረገችው። ልጆቹ ከ18 ቀን እስከ 18 ወራት ቆይተው ይህቺን ዓለም የመሰናበታቸው ጉዳይም ከግድያ ጋር የተያያዘ ነው የሚለውን ክስ አጠናክሮት ነበር።

እናት ፎልቢግ ግን ካሌብ፣ ፓትሪክ፣ ሳራህ እና ላውራ የሚል ስም የነበራቸው ልጆቿ በተፈጥሯዊ መንገድ ሕይወታቸው ማለፉን ብትገልጽም ሰሚ አላገኘችም። የየእለት ውሎዋን የምትጽፍበት (ዲያሪ)ም “የተረጋጋ ሕይወት የላትም፤ ልጆቿን የገደለቻቸው እሷ ናት” ለሚለው ጉዳይ ማስረጃ ሆኖ በ2003 የ40 ዓመት እስራት አስፈርዶባት ነበር።

እስራቱ በይግባኝ ወደ 30 ዓመት ዝቅ እንዲልላት ቢደረግም “ማንም ሊሰማኝ አልቻለም ነበር” የምትለው ፎልቢንግ ባለፈው ዓመት ከ20 ዓመት እስር በኋላ በምህረት ተለቃለች። የ56 አመቷ እናት በዛሬው እለትም ከኒው ሳውዝ ዌልስ ከፍተኛ ፍርድቤት መልካም ዜና ሰምታለች።

ፍርድ ቤቱ ካትሊን ፎልቢግ ለእስር የተዳረገችበት ማስረጃ “አሳማኝ አይደለም” የሚል ውሳኔ ማሳለፉን ነው ቢቢሲ የዘገበው። ከዚህ ውሳኔ ላይ ለመድረስም ለልጆቹ ግድያ መንስኤው ተፈጥሯዊ የበራሂ (ጂን) ችግር ሊሆን ስለሚችል ምርመራ ይደረግ የሚለው የፎልቢግ ጥያቄ ነው።

በዚህም መሠረት የተደረገው ምርመራ ሁለቱ ሕጻናት በአጭር ጊዜ ሕይወታቸው እንዲያልፍ ምክንያት የሚሆን



“ሳይንስ ነጻ ስላወጣኝ አመሰግናለሁ” ያለችው እናት ካሳ ለመጠየቅ ተዘጋጅታለች

የበራሂ (ጂን) መለዋወጥ ሰለባ መሆናቸው መረጋገጡ ነው የተገለጸው። ውጤቱ “የአውስትራሊያ ጨካኟ እናት” የሚለውን ተቀጽላ የሚያስፍቅና ሙሉ በሙሉ ከወንጀል ተጠያቂነት ነጻ እንድትሆን የሚያደርጋት ነው ብሏል የኒው ሳውዝ ዌልስ ጠቅላይ ፍርድ ቤት።

ፎልቢግ በሲድኒ ሳግ እየተናነቃት “የበራሂ (ጂን) ሳይንስ መዘመን ልጆቼን እንዳልገደልኩ አረጋግጦልኝ ነጻ ወጥቻለሁ፤ ከ1999 ጀምሮ ነጻ የምሆንበት ሕጋዊ አግባብ ቢኖርም ሰሚ አልነበረኝም” ብላለች።

“ህጻናት በድንገት እና ልብ በሚሰብር ሁኔታ ሕይወታቸው እንደሚያልፍ ከማሰብ ይልቅ እኔን ተጠያቂ ማድረጉ ስለተመረጠ 20 ዓመታትን ያለጥፋቴ ታስሬያለው፤ የእኔን ስቃይ ማንም እንዲደግመው አልፈልግም” ስትልም ተናግራለች። ጠበቃዋም የ56 አመቷ እናት በስህተት ለተፈጸመው እስር ካሳ ለመጠየቅ መዘጋጀቷን አስታውቀዋል።

የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፦ www.press.et
ፌስቡክ፦ Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ዓርብ
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን የስፖርት ቁሳቁሶች ድጋፍ አበረከተ

**ቦጋለ አበበ**

የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ለአዲስ ከበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን የፑል ቦይ እና የኪክ ቦርድ የስፖርት ቁሳቁሶችን ድጋፍ አደረገ።

ፌዴሬሽኑ ለውሃ ዋና ሥልጠና መሠረታዊ የሆኑ የስፖርት ቁሳቁሶችን ከዓለም አቀፉ ውሃ ዋና ማህበር ጋር በመተባበር ለክልሎችና ለከተማ አስተዳደሮች ድጋፍ ማድረጉን አጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጿል።

የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ወይዘሮ መሠረት ደምሱ የአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን ባደረገው ከፍተኛ እንቅስቃሴ ድጋፍ እንደተደረገለት ገልጸዋል።

‹‹ታዳጊዎች ላይ በመሥራታችን በአፍሪካ የሚወዳደሩ ታዳጊዎችን ማፍራት ችለናል›› ያሉት ፕሬዚዳንቷ አሁን ያበረከቱት የስፖርት ቁሳቁሶቹ ከዚህ በፊት ከውጭ ሀገራት በውጭ ምንዛሬ ወደ ሀገር ውስጥ የገቡና ዋጋቸውም ውድ እንደነበር አስታውሰዋል። ከዓምና ጀምሮ ግን እነዚህን ቁሳቁሶች በሀገር ውስጥ ያሉ ፋብሪካዎችን በማነጋገር እየተመረቱ የውጭ ምንዛሬን በማዳን አበረታች ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ ተናግረዋል።

ፌዴሬሽኑ ለተለያዩ ክልሎች የስፖርት ቁሳቁስ ድጋፍ ሲያደርግ የአሁኑ ለሦስተኛ ጊዜ መሆኑን የገለፁት ፕሬዚዳንቷ፣ የፌዴሬሽኑ አዲስ ሥራ አስፈፃሚ ወደ ኃላፊነት ከመጣ በኋላ ባለፉት ሦስት ዓመታት ለተለያዩ የታዳጊ ወጣቶች ፕሮጀክት ድጋፎችን እያደረገ እንደሚገኝ አብራርተዋል። ‹‹ድጋፉን የምናደርገው ታዳጊዎችን ማፍራት ለነገ የምንተወው የቤት ሥራ አለመሆኑን በሥራ አስፈፃሚ ቦርድ ከተወሰነ በኋላ ተተኪ ስፖርተኞች የሚያስፈልጋቸው ምን እንደሆነ በመለየት ነው›› ያሉት ፕሬዚዳንቷ ወጣትና ታዳጊ ስፖርተኞች የሚሰለጥኑበት ቁሳቁስ እጥረት እንዳለባቸው ገልፀዋል። ይህን ችግር ለመቅረፍ ፌዴሬሽኑ ከዓለም አቀፉ ውሃ ስፖርቶች ማህበር ጋር ግንኙነቱን በማጠናከር ፕሮጀክቶችን ቀርፆ የተለያዩ ሥራዎችን በማከናወን ባገኘው የገንዘብ ድጋፍ የቁሳቁስ ርዳታውን ማድረግ ችሏል። ከዓለም አቀፍ ማህበሩ የሚገኘው የገንዘብ ድጋፍ ለትክክለኛው ዓላማ እንዲውልም ፌዴሬሽኑ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል። ከዚህ ቀደም የተደረጉ ድጋፎች ምን ላይ እንደደረሱም ከክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ጋር በመነጋገር ክትትል እየተደረገ ይገኛል።


ፌዴሬሽኑ ለውሃ ዋና ስፖርት ዕድገት የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥል ቃል ገብቷል፣

‹‹የውሃ ስፖርት ውድ ስፖርት ነው፣ ቢዚያው ልክም ተወዳጅ ነው፣ ኢትዮጵያ በዚህ ስፖርት በሚገባት ልክ በዓለም አቀፍ መድረክ አልተወከለችም፣ ስፖርቱም በዚያ ልክ አድጓል ብለን አናምንም›› ያሉት ፕሬዚዳንቷ ይህንን ለመቀየር ፌዴሬሽኑ ከሚያገኘው ገንዘብ ላይ ለታዳጊዎች በማዋል ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል።

ፌዴሬሽኑ ዓምና ለመጀመሪያ ጊዜ የታዳጊ ወጣት ፕሮጀክቶች ውድድር ያደረገ ሲሆን በዚያ ውድድር የተገኙ ስፖርተኞች በአፍሪካ ደረጃ በሚካሄዱ ውድድሮች ኢትዮጵያን ወክለው እንዲወዳደሩ እያደረገ ይገኛል። በቀጣይም በዓለም አቀፍ ውድድሮች የሚሳተፉበትን እቅድና ራዕይ በመያዝ እየተሠራ ነው።

ፌዴሬሽኑ ባለፈው ህዳር 19/2016 በጊዮን ሆቴል ባካሄደው ውድድር ኢትዮጵያን በዓለም አቀፍ መድረኮች የሚወክሉ ዋናተኞችን መርጧል። እነዚህ ዋናተኞች በዋናነት በ2024 በኳታር ዶሃ በሚካሄደው የዓለም የውሃ ስፖርቶች ቻምፒዮና የሚወክሉ ሲሆን ከወራት በኋላ በሚካሄደው የፓሪስ ኦሊምፒክም የሚሳተፉ ይሆናል። ጊዜው ሲደርስም ዋናተኞቹ ሆቴል ገብተው ዝግጅት እንደሚያደርጉ ወይዘሮ መሠረት በመጠቆም፣ ከኢትዮጵያ ኦሊምፒክ ኮሚቴ ጋርም በቅርበት እየሠሩ እንደሚገኙ አብራርተዋል።

በድጋፍ እርክክቡ ወቅት የተገኙት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ውሃ ዋና ፌዴሬሽን ፕሬዚዳንት ኢንጅነር ዳዊት እምሩ፣ የኢትዮጵያ ውሃ ስፖርቶች ፌዴሬሽን ላደረገው ድጋፍ አመስግነው ድጋፉ በፕሮጀክት ለሚሠሩ የውሃ ዋና ስፖርቶች እግዛ ከማድረጉ ባሻገር ለውሃ ዋና ስፖርት ሁለንተናዊ እድገት ከፍተኛ አስተዋፅኦ እንዳለው ገልጸዋል።

የስፖርት ቁሳቁሶችን የተረከቡት የአዲስ አበባ ከተማ ውሃ ዋና ፌዴሬሽን ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ተስፋዬ ደመቀ በበኩላቸው፣ የተደረገው ድጋፍ ታዳጊ ወጣቶችን ለማሠልጠን የሚረዳና ተተኪዎችን ለማፍራት ፌዴሬሽኑ እያደረገ ላለው ጥረት አጋዥ እንደሚሆን ተናግረዋል።